# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 81ኛ ዓመት ቁጥር 360 ነሐሴ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







ፎቶ፡ ሀዱሽ አብርሀ

# «በጎነት በትውልዶች መካከል ጠንካራ ድልድይ መገንባት ነው»

- ሳህለወርቅ ዘውዴ
የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፕሬዚዳንት

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በጎነት በትውልዶች መካከል ጠንካራ ድልድይ መገንባት ነው ሲሉ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ተናገሩ። አሥረኛው የዓመቱ በጎ ሰው ሽልማት በትናንትናው ዕለት ተካሂዷል።

ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ለዘንድሮው የበጎ ሰው ተሸላሚዎች የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት ሲያስተላልፉ እንደገለጹት፤ በጎዎች የዘመንና የትውልድ ድልድዮች ናቸው፤ በጎነትም በትውልዶች መካከል ጠንካራ ድልድይ መገንባት ነው።

«በጎነት በትውልዶች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





ወ/ሮ ብርሃኔ ቤካ

# የአሸባሪውን ሕወሓት ወረራ በመቃወም ዳያስፖራው የትዊተር ዘመቻና ሰላማዊ ሰልፎች ሲያካሂድ ነው

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዲስ አበባ፡- ዳያስፖራው የተለያዩ አገራዊ ጉዳዮችን በማንገብ በተለይም አሸባሪው ሕወሓት ለሦስተኛ ጊዜ የቀሰቀሰውን ጦርነት በማውገዝ የትዊተር ዘመቻ፣ ሰላማዊ ሰልፎች እንዲሁም የአገር መከላከያ ሠራዊት ድጋፍ የማድረግ መርሃ ግብር ሊያከናወን መሆኑ ተገለጸ። ዳያስፖራው የኢትዮጵያውያን እውነት እንዲገለጥ እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ ጠንክሮ እየሠራ መሆኑም ተመላክቷል።

በአሜሪካ የዳያስፖራው አስተባባሪ ወ/ሮ ብርሃኔ ቤካ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የዳያስፖራው ማኅበረሰብ

የአሸባሪውን ሕወሓት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# «የልጄን ልደት በግዳጅ ቀጣና ሆኜ ባሳልፍም አልከፋም፤ ሁሉም ለአገር ነው»

- ወታደር ሰሚራ ይማም
ከግዳጅ ቀጣና

**ጌትነት ተስፋማርያም**

ትናንት ልጇ ሦስተኛ ዓመቷን አከብራለች። እናት ግን በዕለቱ ኬክ አሊያም የልደት ሻማ ይዛ ወደቤቷ አልሄደችም፤ ይልቁንም ከመከላከያ የተሰጣትን ግዳጅ ለመፈጸም ጭነቷን አስተካክላ በልበ ሙሉነት ጉዞዋን ወደግንባር አድርጋለች።

የመከላከያ ከባድ ተሽከርካሪ ሾፌሯ ሰሚራ ይማም የሁለት ልጆች እናት ነች። አንዱ ልጇ አስር ዓመቱ ሲሆን ትንሿ ልጇ ደግሞ ትናንትና ነው ሦስተኛ ዓመቷን ያከበረችው።

እናት በሰሜን ወሎ ግንባር ለተሰለፈው ጥምር ጦር አስፈላጊውን ስንቅና ትጥቅ በማመላለስ ሥራ ላይ ተጠምዳለች። «ስካኒያ» የተሰኘውን ተሳቢ ተሽከርካሪ በልበ ሙሉነት እያሽከረከረች ከግንባር ድረስ ዘልቃ አስፈላጊውን ግብዓት ታደርሳለች።

ሴት ልጄን አቅፌ እየሳምኩ ልደቷን ላከብርላት ባልችልም፤ ለአገርና ለሕዝብ ፍቅር አስፈላጊውን መስዋዕትነት ለመክፈል በሙያዬ እያገለገልኩ በመሆኑ ግን ደስተኛ ነኝ ብላለች።

«የልጄን ልደት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ፎቶ - ዳኒ አበራ







# አሸባሪው ሕወሓት በሕፃናትና አዛውንቶች ላይ በከባድ መሣሪያ ጥቃት ፈጽሟል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በቆቦ ወረዳ ሕፃናትና አዛውንቶች ላይ በከባድ መሣሪያ ጥቃት መፈጸሙን የጥቃቱ ተጎጂዎችና ቤተሰቦቻቸው ገለጹ።

የሽብር ቡድኑ ለሰላም የተሰጠውን ዕድል ወደጎን በመጣል ጦርነት በከፈተባቸው የአማራ እና አፋር ክልል ወረዳዎች በንፁሃን ዜጎች ላይ ጥቃት በማድረስ የሽብር ተግባር መፈጸሙን አሁንም ቀጥሏል።

የትግራይ ሕፃናትና ወጣቶችን በሕዝብ ማዕበል አሰልፎ ወረራ የፈጸመው የሽብር ቡድኑ በአማራ ክልል ሰሜን ወሎ ዞን ቆቦ ወረዳ በሚገኙ ንጹሃን ዜጎች ላይ ከቀናት በፊት በከባድ መሣሪያ የታገዘ ጥቃት ፈጽሟል።

ንፁሃንን በመጉዳት የተካነው የሽብር ቡድኑ በቆቦ ወረዳ የአርሶ አደሮችን ቤት በመድፍ በመደብደብ በሕፃናትና አዛውንቶች ላይ ጉዳት አድርሷል።

የሽብር ቡድኑ ነሐሴ 19 ቀን 2014 በግለሰቦች መኖሪያ ቤት ላይ በፈጸመው የከባድ መሣሪያ ድብደባ አቶ ደሳለ ትኩየ የተባሉ የ60 ዓመት አዛውንትና ቤተሰቦቻቸው ላይ ከባድ ጉዳት አድርሷል።

የከባድ መሣሪያ ድብደባ በመፈጸም ከብቶችን በመጠበቅ ላይ የነበሩ ታዳጊዎችን ለከባድ የአካል ጉዳት ዳርጓል።

ህክምና እየተከታተሉ ያገኘናቸው ተጎጂዎችና ቤተሰቦቻቸው የሽብር ቡድኑ ሕፃናትን ወደ ጦርነት በንጹሃን አርሶ አደሮችና በታዳጊዎች ላይ ለከባድ የአካል ጉዳት የዳረገ ጥቃት እንደፈጸመባቸው ተናግረዋል።



አቶ ደሳለ ትኩየ

«እኛ አርሶ አደሮች ነን፤ የሽብር ቡድኑ በማዕበል ወረራ ፈፅሞ ዘረፋ መፈጸሙ ሳያንስ በከባድ መሣሪያ ደብድቦናል» ይላሉ።

ምንም የማያውቁ ሕፃናት ከብቶችን እየጠበቁ ባለበት ወቅት በከባድ መሣሪያ ድብደባ በመፈጸም ለሕፃናት የሚራራ ልብ እንኳ እንደሌለው በተግባር ማሳየቱንም እንዲሁ።

እንደ ኢዜአ ዘገባ፤ የሽብር ቡድኑ ያደረሰባቸው ጉዳት መቼም የማይሽር ጠባሳ መሆኑን የገለጹት ተጎጂዎቹ፤ በአሁኑ ወቅት ተገቢ ህክምና እየተደረገላቸው መሆኑን ጠቅሰዋል።

ሆኖም በሽብር ቡድኑ ወረራ ውስጥ ያሉ ቤተሰቦቻቸውን በሕይወት የመኖርና አለመኖር ሁኔታ አለማወቃቸው በእጅጉ እንዳሳሰባቸውም ነው የተናገሩት።

አሸባሪው የሕወሓት ቡድን የትግራይን ሕፃናት ለደም ግብሩ ከፊት በማዕበል በማሰለፍ ወረራ እየፈጸመ በንጹሃን ላይ ጥቃት በመፈፀም በዚህም በዓለም አቀፍ የጦር ወንጀል የሚያስጠይቅ የሽብር ወንጀሉን ቀጥሎበታል።



አቶ አንድነት ሽፈራው

## ቡድኑ ሕፃናትን በጦርነት መማገዱ ስፖለቲካዊ ትርፍ የማይፈጽመው ጭካኔ እንደሌለ ማሳያ ነው

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው የሕወሓት ቡድን ሕፃናትን ጨምሮ በርካታ ንፁሀንን በጦርነት መማገዱ ፖለቲካዊ ትርፍ እስካስገኘለት ድረስ ምንም ዓይነት ጭካኔ ከመፈጸም እንደማይመለስ ማሳያ መሆኑን የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል አቶ አንድነት ሽፈራው ገለጹ።

አቶ አንድነት ሽፈራው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አሸባሪው የሕወሓት ቡድን ራሱን ነፃ አውጪ ብሎ ከተደራጀበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ እኩይ ድርጊቶችን ሲፈጽም ቆይቷል። በተከታታይ በሚፈጽማቸው ወረራዎች ሕፃናትን ጨምሮ በርካታ ንፁሀንን በጦርነት መማገዱ ቡድኑ ፖለቲካዊ ትርፍ እስካስገኘለት ድረስ ምንም ዓይነት ጭካኔ ከመፈጸም እንደማይመለስ ማሳያ መሆኑን አስረድተዋል።

አሸባሪው የሕወሓት ቡድን የተመሠረተው ማንነትን መሠረት አድርጎ ስለሆነ ለትግራይ ሕዝብ ቆሜለታለሁ እንደሚል አስታውሰው፤ በ2010 ዓ.ም በሕዝብ ግፊትና በውስጥ በነበሩ ለውጥ ፈላጊዎች ከማዕከላዊ መንግሥት ተገፍቶ መቀሌ ላይ ከከተመ በኋላ ሌሎች የፖለቲካ ኃይሎች ጋር ያለውን ልዩነት በጠቅላላ በትግራይ ሕዝብ ላይ የተደቀነ አደጋ አድርጎ ሲያቀርብ ቆይቷል ብለዋል።

በመከላከያ ሠራዊቱ ላይ ያደረሰውን ጥቃት ተከትሎ በነበረው የሕግ ማስከበር እንቅስቃሴም ሆነ በአፋርና አማራ ክልሎች ላይ ወረራ ፈጽሞ በተካሄደው የሕልውና ጦርነት የትግራይን ሕዝብ ሕልውና አደጋ ላይ ለመጣል አስመስሎ ፕሮፓጋንዳ ሲሠራ መቆየቱንም አስታውሰዋል።

ቡድኑ እየሠራ ባለው የተሳሳተ ፕሮፓጋንዳ ሰብአዊነት በጎደለው መልኩ በርካታ ወጣቶችንና ሕፃናትን ሳይቀር ወደ ጦርነት እየማገደ መሆኑን አመልክተው፤ ይህም ቡድኑ በፖለቲካው ውስጥ ለመቆየት እስካስቻለውና ፖለቲካዊ ትርፍ እስካስገኘለት ድረስ ቆሜለታለሁ ለሚለው ሕዝብ ምንም ደንታ በባለመስጠት ምንም ዓይነት ጭካኔ ከመፈጸም እንደማይመለስ ማሳያ ነው ብለዋል።

አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በስልጣን ላይ ሳለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ላይ ያልፈጸመው በደልና ግፍ እንደሌለ ያስታወሱት አቶ አንድነት፤ የፖለቲካ ምህዳሩን ለማስፋትና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለማጠናከር በሚል ሕዝብና መንግሥት በሆደ ሰፊነት ይቅርታ አድርጎላቸው ነበር። ሆኖም ያገኙትን የይቅርታ ዕድል ወደ ጎን በመተው በመላ አገሪቱ ኢትዮጵያን ሰላም የሚነሱና እነርሱን ወደ ማዕከላዊ ስልጣን ይመልሰናል ብለው ያሰቧቸውን እኩይ ድርጊቶች ሲፈጽሙ መቆየታቸውን አስታውሰዋል።

ቡድኑ አሁንም ራሱን ከተጠያቂነት ለማዳንና ፖለቲካዊ ትርፍ ለማግኘት ሦስተኛ ዙር ጦርነት ከፍቷል ያሉት አቶ አንድነት፤ መንግሥት ያለበትን የአገርን ሉአላዊነትና የሕዝብን ደህንነት የማስጠበቅ ግንባር ቀደም ኃላፊነት ለመወጣት ጥረት እያደረገ ይገኛል። መላው ኢትዮጵያውያንም ያለምንም ልዩነት ኢትዮጵያን በማስቀደም የአገርን ሕልውና ለማስጠበቅና ቡድኑ ለትግራይ ሕዝብና ለተቀረውም ኢትዮጵያዊ ስጋት መሆን ከማይችልበት ደረጃ ለማድረስ መረባረብ እንዳለባቸው ጥሪ አቅርበዋል።

ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ የቡድኑን አረመኔያዊ ድርጊት ለማውገዝና ጫና ለማሳደር ፍላጎት አለማሳየቱ የሚያሳዝን መሆኑን ጠቁመው፤ አሁንም በገለልተኝነት ቡድኑ የሚፈጽማቸውን ኢሰብአዊ ድርጊቶች ሊያወግዝና ከንፁሃን ጎን ሊቆም እንደሚገባ ጠቁመዋል።



# ጳጉሜን ዓለምአቀፋዊ ብራንድ ለማድረግ እየተሠራ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የአገራችንን 13ተኛ ወር ጳጉሜን በዓለም ቱሪዝም ገበያ ውስጥ ዓለምአቀፋዊ ብራንድ ለማድረግ እየሠራ መሆኑን አእላፍ ደጀን ኔትወርክ አስታወቀ።

በዳያስፖራው ጥምረት የሚቋቋመው የአእላፍ ደጀን ኔትወርክ ጳጉሜ 1፣ 2014ዓ.ም የኒኦ ሶሳይቲ የምስረታ በዓል ያካሂዳል።

የአእላፍ ደጀን ኔትወርክ አስተባባሪ የሆኑት ዶክተር ማስረሻ ኤራጎ እንደተናገሩት፣ የአገራችንን 13ተኛ ወር ጳጉሜን በዓለም ቱሪዝም ገበያ ውስጥ ለማስገባትና ዓለም አቀፋዊ ብራንድ ለማድረግ እየሠራን ነው። በመሆኑም «ለዘመናት ለኖረ የኢትዮጵያውያን ጥሪ፤ ከኢትዮጵያውያን ቀጥታ ምላሽ» ለማስገኘት አዕላፍ ለመሆን ቆርጠን ተነስተናል።

እንደ ዶክተር ማስረሻ ገለፃ፣ ኢትዮጵያዊ ለወገኑ፤ ተገን እና ደጀን ነው። ስለዚህ የየአገር ቤትና የውጭ ነዋሪ ኢትዮጵያውያንን የማሰባሰብና የማደራጀት ሥራ ሠርተናል። በዚህም አእላፍ ደጀን ኔትወርክ ጳጉሜን ዓለምአቀፋዊ ብራንድ ለማድረግ ዋነኛ እቅድ አድርጎ ይዟል።

ለዚህ ታላቅ አላማ መሳካት በአእላፍ ደጀን ኔትወርክ አሳሳቢነትና አደራጅነት አንድ መቶ ሺህ አባላት ያሉበት «ኒኦ ሶሳይቲ» መመስረት ነው ያሉት ዶክተር ማስረሻ፣ በዚህ ኒኦ ሶሳይቲ አማካኝነት ስምንት ታላላቅና ሜጋ ፕሮጀክቶችን ወደ ተግባር ለመለወጥ አስበናል ብለዋል።

የአእላፍ ደጀን ኔትወርክ አስተባባሪ ዶክተር ሻምበል ሳህሉ በበኩላቸው፣ አእላፍ ደጀን በአካባቢ ጥበቃ፣ በቱሪዝም ማስፋፋት፣ በማህበራዊ ለውጥ፣ በባህላዊ መሻሻል፣ በኢኮኖሚያዊ እድገት፣ በስነ ልቦናና ጥበቃ አገልግሎት፣ በወዳጅነት ግንባታ፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሽግግር፣ በሥራ ፈጠራ፣ በትብብርና በቅንጅት እንቅስቃሴ፣ በሰላም ማስፈን ዘርፍ፣ በማንነት ጥናትና ምርምር፣ በሚዲያና በመዝናኛ ማዕከላት፣ ግንባታዎች ላይ በጥናትና በምርምር ውጤቶች በመታገዝ የተሻለች ኢትዮጵያን የመገንባት እንቅስቃሴ ላይ ነው።

ሌላው ታላላቅ ራዕያችንን የሚያጨናግፉ ሾተላዮች በተመሳሳይ ሁኔታ ለአገራዊ እንቅስቃሴ ዐይነ ጥላ መሆናቸው ነው ያሉት ዶክተር ሻምበል፣ ይህ የፈጠራ አዕምሮ ያላቸውን ዜጎች ጎድቷል ብለዋል። ትክክለኛ ዜጎች አገራዊ ተሳትፏቸውን እንዳያበለጽግ አድርጓልም ብለዋል።

እንደ ዶክተር ሻምበል ገለጻ፣ አእላፍ ደጀን ኔትወርክ ለመደራጀት በቂ ምክንያቶች አሉት። ከ21ኛ ክፍለ ዘመን ጋራ የሚራመዱ ሰዎችን በማሰባሰብና በማኅበረሰብ ማዕቀፍ በማደራጀት በተለያዩ የሙያ፣ የሥራና የጥናት ዘርፎች ላይ በተግባር እንዲሰማሩ በማድረግ የድርሻቸውን አገራዊ አስተዋጽኦ እንዲደርሱ እያደረገ ነው።



የድሬዳዋ ሞተር ኢንዱስትሪ ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር የስምምነት ፊርማ ሲያካሂዱ

# የአገር ውስጥ ምርት አጠቃቀምን 60 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- አገርን ከውጭ ተጽዕኖ ለማላቀቅ እና ሉአላዊነትን ለማስከበር በቀጣይ 10 አመት ውስጥ የአገር ውስጥ ምርት አጠቃቀምን 60 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የድሬዳዋ ሞተር ኢንዱስትሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚነት መሸጋገሩን አስመልክቶ ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር የስምምነት ፊርማ ባከናወነበት ወቅት ንግግር ያደረጉት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የእድገትና ተወዳዳሪነት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ታረቀኝ ቡሉልታ እንደገለጹት፤ በአሁኑ ጊዜ የአገር ምርት አጠቃቀም ከ30 በመቶ የዘለለ አይደለም።

አብዛኛው የምግብ፣ የጨርቃጨርቅና የብረታብረት ፍጆታ ከውጭ የሚገባ ነው ያሉት አቶ ታረቀኝ፤ በቀጣይ 10 አመት ውስጥ ይህንን በእጥፍ በማሳደግ የአገር ውስጥ ምርት አጠቃቀምን ወደ 60 በመቶ የማድረስ እቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው ብለዋል።

የአገር ውስጥ ምርቶችን የመጠቀም ልምድን ማሳደግ ካልተቻለ በውጭ አገራት ተጽዕኖ ውስጥ እንድንወድቅና የአገራችን ሉአላዊነትን ማስከበር እንዳንችል ያደርገናልም ብለዋል።

የውጭ ምርትን በስፋት መጠቀም አገርንና ሕዝብን ማሽማቀቅ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ እንዲሁም ሉአላዊነትን አሳልፎ የመስጠት ሂደት ስለሆነ ለአገር ውስጥ ምርት ትልቅ ትኩረት ተሰጥቷል ብለዋል።

አቶ ታረቀኝ እንዳሉት፤ የኢንዱስትሪው ዘርፍ መዋቅራዊ ሽግግር እንዲመጣ በልዩ ትኩረት እየተሠራበት ነው፤ የማዕድንና የቱሪዝም ዘርፎችም ትኩረት ከተሰጠባቸው መካከል ይገኙበታል። በተለይ የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ዘላቂ ተወዳዳሪነትን ከማረጋገጥ አኳያ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት በመሠራት ላይ ይገኛል።

እንደ አቶ ታረቀኝ ገለጻ፤ የአገር ውስጥ ምርትን ለማሳደግ የአስር አመት እቅድ በማውጣት ተግባራዊ እየሆነ ይገኛል። እቅዱን ልዩ የሚያደርገው ከዚህ ቀደም እንደነበረው አንድ ሴክተር ተኮር ከመሆን ወጥቶ ብዙ ሴክተሮችን የማሳደግ እቅድ ያለው ነው። ይህም በአጭር ጊዜ ውስጥ የአገር ውስጥ ምርቶችን በማሳደግ እንደ አገር ለመለወጥ ይረዳል።

የአገር ውስጥ ምርትን ለማሳደግ በ2014 ዓ.ም የተጀመረው ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› ንቅናቄ ከፍተኛ ለውጥ እያመጣ ነው ያሉት አቶ ታረቀኝ፤ በሁሉም ዘርፍ አገራዊ ምርቶችን በማሳደግ በራሳችን ምርት ማተኮር አለብን ብለዋል። ግብርናውና ኢንዱስትሪው እንዲመጋገቡ በማድረግ ምርታማነትን ማሳደግ ትልቅ ሥራ የሚፈልግ ነው። ምርታማነትን በመጨመር ራስን መቻል ካልተቻለ በዘላቂነት ተወዳዳሪና እንደ አገር ኩሩ ሕዝቦች መሆን አንችልም ሲሉም ተናግረዋል።

ድሬዳዋ ሞተርስ የመጀመሪያው የግል ኢንዱስትሪ ፓርክ ሆኖ ሲመሠረት ድሬዳዋ እንደ ሁልጊዜው የእድገትና የኢንዱስትሪ መንደር የመሆን ዕድል አላት ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በቅርብ ጊዜ የተመሠረተው ነፃ የንግድ ቀጣና ለዚህ ትልቅ እገዛ ያደርጋል፤ መንግሥትም ለግሉ ዘርፍ የሚያደርገውን እገዛ አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አቶ ዳንኤል ተሬሳ በበኩላቸው፤ አገራችን ዘላቂና ሁሉን አቀፍ የኢኮኖሚ እድገት ለማምጣት በርካታ የሕግ ማዕቀፍና የፖሊሲ ማሻሻያ ሥራዎችን በመሥራት ትገኛለች። ማሻሻያዎች አዳዲስ የአገር ውስጥ አምራቾችን በዘርፉ እንዲሰማሩና የነባሮችን አቅም በማሳደግ ትልቅ ሚና እየተጫወተ ይገኛል። በዚህም በአፍሪካ ደረጃ ከፍተኛ የውጭ ኢንቨስተርን ከሚስቡ አገሮች ተርታ መሰለፏን አስታውቀዋል። የድሬዳዋ ኢንዱስትሪ ቀጣይ ጉዞ የተሳካና ለአገር እድገት ትልቅ ሚና የሚኖረው ሁሉም ሲተባበር መሆኑን አሳስበዋል።

የድሬዳዋ ሞተርስ ኢንዱስትሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ዋና ሥራ አስፈጻሚ ኢንጅነር ታደሰ አድማሱ ኢንዱስትሪው ከኢንዱስትሪ ፓርክነት ባለፈ በቀጣይ አገራችን ለምትጠቀማቸው ሰፋፊ የኢንዱስትሪ ልማቶች ፈር ቀዳጅ የሆኑ ባህሪያት አሉት ብለዋል።

ፓርኩ ከአምስት ቢሊዮን ብር በላይ ኢንቨስት የተደረገበትና በ116 ሄክታር መሬት ላይ በመገንባት ያለ ሲሆን በቀጣይ ሙሉ ለሙሉ ሲጠናቀቅ ከ23 በላይ ኢንዱስትሪዎች በውስጡ ይካተታሉ ብለዋል። ባለ አራት እግር ተሽከርካሪ፣ የኮንስትራክሽን ማቴሪያል፣ የታሸገ ውሃና ሌሎች ምርቶችን በጥቅሉ ወደ አራት የሚሆኑ ኢንዱስትሪዎች ቦታቸውን ይዘው ምርት በማምረት ላይ እንደሚገኙም ገልጸዋል።

ባለሀብቱ አቅሙ በቻለው መጠን የልማት አቅጣጫዎችን ተከትሎ የአገሪቷ ልማት እንዲፋጠን መሥራት አለበት። በዚህ ረገድ ድሬዳዋ ሞተርስ ኢንዱስትሪ ላለፉት ተከታታይ አመታት በከፍተኛ ግብር ከፋይነት በመንግሥት ሲሸለም የቆየ ለአገር እድገት ሁሉን አቀፍ ድጋፍ ያደረገና ወደፊትም አጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል።

# ጦርነቱ ለወደሙ መሠረተ ልማቶች መልሶ ግንባታ መሰናክል ሆኗል

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- ሕወሓት ለሦስተኛ ጊዜ የቀሰቀሰው ጦርነት ለወደሙ መሠረተ ልማቶች መልሶ ግንባታ መሰናክል መሆኑን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አስታወቀ። በጦርነቱ ከአንድ ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር በላይ ውድመት በኤሌክትሪክ ኃይል መሠረተ ልማት ላይ መድረሱ ተጠቁሟል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሞገስ መኮንን ለቪኦኤ እንደገለፁት፣ የሰሜን ኢትዮጵያው ጦርነት ትግራይ ክልል የገጠመውን ውድመት ሳይጨምር በአፋር እና በአማራ ክልል በገንዘብ ሲገመት በመሠረተ ልማት ላይ ከአንድ ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር በላይ የሚገመት ጉዳት አድርሷል።

ከጥቅምት 2013 ጀምሮ በሽብር ቡድኑ ሕወሓት የወደመውን የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት መንግሥት አካባቢውን መልሶ ከተቆጣጠረ በኋላ ከታኅሣሥ ወር 2013 ጀምሮ መልሶ የመጠገን ሥራ ሲሠራ መቆየቱንም አስታውሰዋል።

ጦርነት እና የተኩስ ልውውጥ ሲኖር የጉዳት መጠኑን ለመገመት ቢያስቸግርም የመሠረተ ልማት ጉዳት ሊኖር እንደሚችል ግን ስጋቶች አሉ ብለዋል።

አሁንም ግጭቱ ባለበት አካባቢ ተመሳሳይ የመሠረተ ልማት ውድመት እና ስርቆት ሊኖር እንደሚችልም ግምቶች አሉ ብለዋል።

አሁን ለሦስተኛ ጊዜ ግጭቱ የተቀሰቀሰበት አካባቢ ከዓመት በላይ ኤሌክትሪክ ያላገኙ አካባቢዎች ጭምር ያሉበት በመሆኑ ኤሌክትሪክ አካባቢዎቹን በኤሌክትሪክ ለማገናኘት በሚደረገው ጥረት ላይ እንቅፋት ይሆናል ያሉት አቶ ሞገስ፣ ኤሌክትሪክ ሲያገኙ የነበሩ አካባቢዎችም እንዲያጡ ምክንያት እንደሚሆን ጠቁመዋል።

በጦርነቱ ውድመት ከደረሰባቸው የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ መሣሪያዎች እና የማከፋፈያ ጣቢያዎች በተጨማሪ በመሠረተ ልማት ላይ ከፍተኛ ዝርፊያ ተፈፅሟል ሲሉ አቶ ሞገስ ተናግረዋል።

በጦርነት ወቅት ባለ የተኩስ ልውውጥ በሚከሰት ውድመት እና ግጭቱን ተከትለው በሚፈጸሙ የዘረፋ ተግባራት በኤሌክትሪክ ኃይል መሠረተ ልማት ላይ ጉዳት እንደሚደርስ ገልጸዋል።

ግጭቱን ሽፋን አድርገውና መሠረተ-ልማትን ዒላማ አድርገው የሚንቀሳቀሱ መኖራቸውንም ጠቁመዋል።

ከ2013 ሐምሌ ወር ጀምሮ በነበረው ግጭት በምሥራቅ አማራ እና በአፋር ክልል ከነበሩ የኤሌክትሪክ ኃይል መሠረተ ልማቶች ግማሽ ያህሉ ወድሟል፤ የክልል ቢሮዎች መገልገያ ቁሳቁሶች ተዘርፈዋል፣ ወይም ወድመዋል ያሉት አቶ ሞገስ በማከፋፈያ ጣቢያዎች ያሉ እና በጥገና ሥራዎች ወቅት ለመለዋወጫ የሚያገለግሉ ዕቃዎች መወሰዳቸውን አስታውሰዋል።

የኃይል እጥረት ችግር ለመቅረፍ በጊዜያዊነት የሚያገለግሉና ዘላቂ ጣቢያ ሲዘረጋ ወደ ሌሎች በማዘዋወር የሚያገለግሉ የነበሩ ተንቀሳቃሽ የማከፋፈያ ጣቢያዎች ተነቅለው መወሰዳቸውንም ተናግረዋል።

ድርጊቱም ተቋሙን ለመልሶ ጥገና ከፍተኛ ወጪ የሚዳርጉ እና በኃይል መቋረጥ ምክንያት ይገባ የነበረውን ገቢ በማሳጣት ረገድ ከፍተኛ ኪሳራ ያስከተለ ነው ብለዋል።

አሁን ዳግም ያገረሸው ጦርነትም በመሠረተ ልማት ላይ ተመሳሳይ ችግር ሊያስከትል እንደሚችል ጠቅሰው፣ ግጭቱ ቀደም ሲል ጉዳት ለደረሰባቸው አካባቢዎች ኃይል ለማቅረብ የሚደረግን ጥረት ያሰናክላል ብለዋል።



አቶ አብዲ ኡመድ

# ኅብረት ሥራ ማኅበራት ከ35 ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል አስመዘገቡ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ኅብረት ሥራ ማኅበራት በ2014 በጀት ዓመት 35 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር ካፒታል ማስመዝገባቸውን የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አብዲ ኡመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ በአጠቃላይ ከ26 ነጥብ 4 ሚሊዮን በላይ አባላትን ያፈሩ ከ105 ሺህ በላይ መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበራት አሉ። ኅብረት ሥራ ማኅበራቱ በ2014 በጀት ዓመት ካፒታላቸው 35 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር ደርሷል።

ኮሚሽኑ፣ የ2014 በጀት ዓመት የኅብረት ሥራ ማኅበራትን የካፒታል መጠን 2 ነጥብ 28 ቢሊዮን ብር ካፒታል ተጨማሪ ለማግኘት አቅዶ ሲሠራ እንደነበር የተናገሩት አቶ አብዲ፤ ጠንካራ ሥራዎች በመሠራታቸው 4 ነጥብ 33 ቢሊዮን ብር ካፒታል ማፍራት መቻሉን አብራርተዋል።

በዚህም በ2013 በጀት ዓመት 31 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር የተመዘገበ ካፒታል ወደ 35 ነጥብ 7 ማሳደግ ተችሏል ብለዋል።

በበጀት ዓመቱ ከሁለት ሺህ በላይ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራትን ማቋቋም መቻሉንና ሁለት ሚሊዮን የሚጠጉ አዳዲስ አባላት ወደ ማህበራቱ መቀላቀላቸውንም አክለው ገልፀዋል።

አባላትን እና ካፒታልን በማፍራት ረገድ ኦሮሚያ፣ አማራ እና ሲዳማ በቅደም ተከተል የተሻለ አፈፃፀም አስመዝግበዋል ያሉት ምክትል ኮሚሽነሩ ኅብረት ሥራ ማኅበራት የልማት አቅም እየሆኑ መምጣታቸውን ጠቁመዋል።

ኅብረት ሥራ ማኅበራት ከተቋቋሙበት ከ1991 ዓ.ም ጊዜ አንስቶ ከ31 ነጥብ 6 ቢሊዮን በላይ ብር ብድር ማቅረብ መቻሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት የልማት አቅም እየሆኑ ለመምጣታቸው እና የዜጎችን ሕይወት በማሻሻል ረገድ ያላቸውን የጎላ ሚና ለማሳየት እንደ አብነት አንስተው አስረድተዋል።

የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ከዚህ የበለጠ በማጠናከር እና በማደራጀት ከዚህ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚቻል የጠቆሙት ምክትል ኮሚሽነር አብዲ፤ ባለፉት ዓመታት በተከናወኑ የማጠናከርና የማደራጀት ሥራዎች ውጤቶች እየታዩ መሆናቸውን አብራርተዋል።

እንደ አቶ አብዲ ገለፃ፤ ማኅበራቱ፣ ለአባላት የተሻለ አገልግሎት በመስጠት ተጠቃሚነታቸውን እያረጋገጡ መምጣታቸው የመደራጀትና አባል የመሆን ፍላጎት እያደገ መጥቷል። የአባላት ቁጥር እና የካፒታል መጠንም በየጊዜው እያደገ መሆኑ በተግባር ተረጋግጧል። ሕግን የተከተለ የአሠራር ሥርዓት ዘርግተው ተግባራዊ በማድረግ የሥራ አፈፃፀማቸውን ያሳደጉ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ቁጥርም ጨምሯል።

ኅብረት ሥራ ማኅበራት በሂሳብ አያያዝ፤ በፋይናንስ አስተዳደራቸው፣ በሰነዶችንና መዛግብቶች አሠራር ሥርዓት ከስርቆት እና ከብልሽት መጠበቅ የሚያስችል አቀማመጥና አያያዝ እንዲኖራቸው ማድረግ ጀምረዋል ያሉት ምክትል ኮሚሽነሩ በዘርፉ የወጣቶች እና የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት እያደገ መምጣቱ የሚበረታታ መሆኑን ጠቁመዋል።

ዜና

# የጭና ጭፍጨፋ የአሸባሪው ሕወሓት የአረመኔያዊነት ባህርይ ማሳያ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ሕወሓት በጭና የፈፀመው ጭፍጨፋ የቡድኑን የአረመኔያዊነት ባህርይ የሚያሳይ ነው ሲሉ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ ገለጹ። አሸባሪው ሕወሓት የፈጸመውን ጭፍጨፋ እና ወረራውን ለመቀልበስ የተከፈለውን መስዋእትነት የሚዘክር ዝክረ ጭና አንደኛ ዓመት ትናንት ተከብሯል።

በሥነ ሥርዓቱ ላይ የአማራ ክልል ርእሰ መስተዳድር ይልቃል ከፋለ (ዶ/ር) እንዳሉት ዝክረ ጭና የአሸባሪው ሕወሓት ዘግናኝ ጭፍጨፋ እና የሽብር ቡድኑን ለመደምሰስ የጀግኖች ኢትዮጵያውያን ጀግንነት እና ክቡር መስዋእትነት የሚታሰብበት ነው ብለዋል።

ወረራው ኢትዮጵያን ለማፍረስ ያለመ ቢሆንም በጀግኖች ኢትዮጵያውያን ጀግንነት እና ክቡር መስዋእትነት ተቀልብሷል ብለዋል።

«ህልውና እና ነፃነት በመስዋእትነት ነው የሚከበሩት» ያሉት ርእሰ መስተዳድሩ ጀግኖቹ የከፈሉት መስዋእትነት ሁሌም ሲታሰብ ይኖራል ብለዋል።

አሸባሪው ሕወሓት የተሰጠውን የሰላም አማራጭ በመተው አሁንም በአማራ እና አፋር ክልሎች የፈጸመውን ወረራ ለመቀልበስ በጋራ መነሳት እንደሚገባም ነው ርእሰ መስተዳድሩ ያሳሰቡት። አሸባሪው ቡድን ያለጦርነት እና ጥፋት መኖር የማይችል መሆኑን በተግባር አሳይቷል ብለዋል።

አሁንም የፈጸመውን ወረራ ለመመከት ጀግናው የወገን ጦር በጀግንነት እየተፋለመ በመሆኑ ሕዝቡ ሁሉን አቀፍ ድጋፉን አጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል ያሉት ዶክተር ይልቃል፤ ወረራውን ለመቀልበስ ሁሉም በጋራ መነሳት እንዳለበትም አሳስበዋል።

ሁሉም ኢትዮጵያዊ በጋራ በመሆን የሽብር ቡድኑን ወረራ ለመቀልበስ በግንባር ለሚፋለመው የወገን ጦር ሁሉን አቀፍ ድጋፍ እንዲያደርግም ጥሪ አቅርበዋል ሲል አሚኮ ዘግቧል።

ዶክተር ይልቃል በአንድነት እና በጽናት በመቆም የአገርን ሉዓላዊነት ማስከበር እንደሚገባም አሳስበዋል።

የሽብር ቡድኑ በተደጋጋሚ በፈጸማቸው ወረራዎች በማይካድራ፣ በጋሊኮማ፣ አጋምሳ ፣ ካሳጊታ፤ ቆቦ እና



ውጫሌን ጨምሮ በተለያዩ የአማራና የአፋር አካባቢዎች ከፍተኛ የሆነ የሰብአዊ እና ቁሳዊ ውድመቶችን መፈጸሙ ይታወሳል። በከፈተው ጦርነት ምክንያትም በርካታ ሰዎች ለሞት ተዳርዋል፤ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎችም ከአካባቢያቸው ተፈናቅለዋል።

# «የልጄን ልደት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ባለችበት ግንባር አስፈላጊውን ጭነት ካመላለሰች በኋላ አረፍ ባለችበት ወቅት «እናትሽ ሰሚራ ትወድሻለች፤ ልጄ መልካም ልደት እመኝልሻለሁ፤ አገር ሰላም ስትሆን ደግሞ አብረን በጋራ እናከብራለን» ስትል ለልጇ መልዕክቷን አስተላልፋለች።

«አሁን ላይ ስለልጆቼ ሳይሆን ይበልጥ ስለአገር የማስብበት ጊዜ ላይ ነኝ» የምትለው ሰሚራ፤ ልጆቼ አገር ሰላም ስትሆን የበለጠ ደስተኛ ሆነው ያድጋሉ። እስከዚያው ድረስ ግን እኔም በሙያዬ የበኩሌን መወጣት አለብኝ ስትል ትናገራለች።

ወደመከላከያ የገባሁት መንግሥት በየሙያችሁ የምታገለግሉ ብሎ ጥሪ ሲያቀርብ ነው የምትለው ሰሚራ፤ በወቅቱ በፍቃደኝነት መቀላቀሏን ታስታውሳለች። በዚህ ምርጫዋ ምክንያት ግን ጥለሽኝ አትሄጂም ይላት ከነበረው ባለቤቷ ጋርም መጋጨቷን ነው የተናገረችው።

በአቋሟ የጸናችው ሰሚራ ግን ልጆቿን ለእህቷ ልጅ እንድትንከባከባቸው ሰጥታ የቤት ኪራይና አስፈላጊውን ወጪ እየሸፈነች ታስተዳድራለች። በተጨማሪነት አንድ የእህቷን ልጅም ከልጆቿ ጋር አብራ ታሳድጋለች።

መከላከያን ከተቀላቀለች አንድ ዓመት የሞላት የከባድ መኪና አሽከርካሪዋ፤ በሙያዋ በተለያዩ ክልሎች በሚገኙ ግንባሮች ላይ መሰማራቷን ነው የምትገልጸው።

በሴትነቷ ተሳቢ ይዛ ስትንቀሳቀስ ብዙዎች አይተው እንደሚያበረታቷት የምትናገረው አሽከርካሪዋ፤ ሴት ልጅ በማንኛውም ሙያ ተሰማርታ ውጤት ማምጣት እንደምትችል ማሳያዋ ነኝ ስትልም ተናግራለች።

ብዙዎች ሴት ልጅ ማሳደግ ብቻ ኃላፊነቷ እንደሆነ ያስባሉ፤ ከዚያም በላይ ትልቅ ኃላፊነት መወጣት እንደምንችል ግን ማሳየት አለብን ብላለች።

«እኔ በረሃውም ሆነ ችግሩ አይበግረኝም። መኪናዬ ውስጥ አልጋ አዘጋጅቼ አድራለሁ፤ ተሽከርካሪዬም ከተበላሸ ቀላል ጥገና እየሰጠሁ ነው የምጓዘው፤ ከዚህ ባለፈ ልጆቼንም ባለሁበት ሆኜ በስልክ እየተከታተልኩ የሚያስፈልጋቸውን ለማሟላት ቦዝኜ አላውቅም» ስትል ከሙያዋ ጎን ለጎን ያለባትን የቤተሰብ ኃላፊነትም አስረድታለች።

ምክትል መቶ አለቃ መስፍን ቆጪቶ የሰሚራን ጥንካሬ ከሚመሰክሩ የመከላከያ ሠራዊት አባሎች አንዱ ነው። «ለግዳጅ በተሰማራችበት ሁሉ ከምንም በላይ የተሠጣትን ኃላፊነት ለመወጣትና የሠራዊቱን ውጤታማነት ለማሳደግ በሙያዋ የምትጥር እንስት ነች» ሲል ይገልጻታል።

ለአንድ ዓመት ያክል በከባድ መኪና አሽከርካሪነቷ መከላከያ ውስጥ አውቃታለሁ የሚለው ምክትል መቶ አለቃ መስፍን በስነምግባሯም ሆነ በሥራ ብቃቷ የተመሠከረላት ነች፤ግዳጇንም ያለምንም ችግር እየተወጣች ትገኛለች ብሏል።

የልጆቿ ጉዳይ ሳይፈትናት እንደማንኛውም የመከላከያ አባል ለአገሯ ክብር መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ በመሆኗ ለሌሎቹም ብርታት መሆኗን ይናገራል። ከወንድ እኩል ሴትም ግዳጇን መወጣት እንደምትችል ብቻ ሳይሆን የበለጠም መሥራት እንደምትችል ሰሚራ አንዷ ማሳያ ነች ሲል ነው የገለጻት።

# አሸባሪው ሕወሓት ወደ ሰላማዊ አማራጭ እንዲመለስ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ጫና እንዲያደርግ ምክር ቤቱ ጠየቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ዳግም ጦርነት የቀሰቀሰው አሸባሪው ሕወሓት ወደ ሰላማዊ አማራጭ እንዲመለስ ዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ ጫና እንዲያደርግ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ጠየቀ።

አንዳንድ የውጭ ኃይሎች የሽብር ቡድኑን በመደገፍ በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ከሚያደርጉት ጣልቃገብነት እጃቸውን በመሰብሰብ የሰላም መንገድን እንዲደግፉም ጥሪ አቅርቧል።

53 ፓርቲዎችን በአባልነት ያቀፈው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ዳግም የተቀሰቀሰው ጦርነት ቆሞ ሰላማዊ አማራጮች እንዲቀጥሉ ሲል የአቋም መግለጫ አውጥቷል።

በአቋም መግለጫው እንደተገለጸው፤ ለረጅም ዘመን በዘለቀ ጦርነት ሥልጣኔና ዕድገቷ የተገታው ኢትዮጵያ አሁንም ከጦርነት አዙሪት አልወጣችም።

ባለፉት 22 ወራት ገደማ በሰሜን ኢትዮጵያ የተቀሰቀሰው ግጭት ከፍተኛ ሰብዓዊ፣ አኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ሥነ ልቦናዊ ጉዳቶች አስከትሏል። ይህ አውዳሚ ጦርነት በሰላማዊ መንገድ እንዲቋጭ የሕዝብ ጽኑ ፍላጎት እንደነበርም ተናግረዋል።

የጦርነቱ ተጎጂዎችን መልሶ ለማቋቋምና መሠረተ ልማት መልሶ ለመገንባት መጠነ ሰፊ ሥራዎች ቢከናወኑም ከጉዳቱ ስፋትና ክብደት አንጻር በዘላቂነት መልሶ የማቋቋም ሥራው የሚፈለገውን ያክል አለመሆኑም ተጠቁሟል።

መንግሥት ለወሰደው የተናጠል የተኩስ አቁም ውሳኔና ጦርነቱ ሰላማዊ እልባት እንዲሰጠው በአፍሪካ ኅብረት በኩል የተጀመረው ጥረት ትልቅ ተስፋ ተጥሎበት እንደነበርም መግለጫው አንስቷል።

ሰላማዊ አማራጩ እያለ በወርሃ ነሐሴ በአሸባሪው ሕወሓት ኃይሎች በተከፈተው ጥቃት ሳቢያ ዳግም የተቀሰቀሰው ጦርነት ምክር ቤቱን ያሳዘነ ድርጊት ነው።

«ለኢትዮጵያ የሚበጀው ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ በውይይት መፍታት ነው» ያለው መግለጫው፤ አሁንም ቢሆን በሰላማዊ ውይይት፣ ምክክርና መግባባት ችግሮች እንዲፈቱ ምክር ቤቱ ጠይቋል።

ምክር ቤቱ ባወጣው ባለ ሰባት ነጥብ የአቋም መግለጫ ጥቃቱን የጀመሩት የአሸባሪው ሕወሓት ኃይሎች መንግሥት በወሰደው የተኩስ አቁም እርምጃ መሠረት ወደ ሠላም አማራጭ እንዲመለሱ ጠይቋል።

አሸባሪው ሕወሓት ለትግራይ ሕዝብ ሰብዓዊ ዕርዳታ የቀረበን ከግማሽ ሚሊዮን ሊትር በላይ ነዳጅ ከዓለም የምግብ ፕሮግራም መዝረፉ የትግራይን ሕዝብ ለችግር የሚዳርግ ነውረኛ ተግባር መሆኑን ጠቅሶ አውግዟል።

የውጭ ኃይሎች በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ከሚያደርጉት ጣልቃገብነት እጃቸውን እንዲሰበስቡ፣ ይልቁንም የሰላም መንገድን እንዲደግፉ ጥሪ አቅርቧል።

መንግሥት የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት የመጠበቅ ኃላፊነት ስላለው በቅርቡ የኢትዮጵያን አየር ክልል ጥሶ በገባ የጠላት አውሮፕላን ላይ የተወሰደውን እርምጃ ምክር ቤቱ አድንቋል።

ለኢትዮጵያ ሰላምና ሁለንተናዊ ዕድገት ሁሉም የሚዲያ ተቋማትና ዜጎች ጦርነትን ከሚያባብሱ መልዕክቶችና ተግባራት ተቆጥበው በሠላም አማራጭ ላይ እንዲሠሩም ጥሪ አቅርቧል።

የዓለም አቀፉ የዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ የችግሩን አሳሳቢነት ተገንዝቦ ጦርነቱ እንዲቆም፣ ሰላማዊ ውይይትና ንግግር በሚጀምርበት ሁኔታ በገለልተኝነት አጋርነታቸውን እንዲያሳዩና በአሸባሪው ሕወሓት ኃይሎች ላይ ጫና እንዲያድርጉ ጠይቋል።

ምክር ቤቱ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት በአገር ደረጃ እንደመፍትሄ የተጀመረው አገራዊ ምክክር እንዲጠናከርም አሳስቧል።

# «በጎነት በትውልዶች...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

እንደ ፕሬዚዳንቷ ገለጻ፤ በጎ ሰው የሚባለው በንግግሩ ሳይሆን በተግባሩ የሚያስመሰክር ነው። በጎ ሰው በጎነቱን በሚናገረው ነገር ሳይሆን በሚሠራው ሥራ የሚያስመስክር ነው። የዘንድሮው የበጎ ሰው ሽልማት የሴቶች ተሳትፎ መጨመሩም ትልቅ ደስታ የሚፈጥር ነው።

በጎነት ለተወሰነ ሰው፣ ፆታ፣ ኃይማኖት፣ ዘር አልያም ለተወሰነ የሥራ ዘርፍ የተከለለ አይደለም ያሉት ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ፣ ለተወሰነ ግለሰብ እና ባለስልጣንም የተከለለም አይደለም፤ በጎ ሰው ለእኔ የሚል ሳይሆን ሌላውንም የሚያበረታ ነው ሲሉ አስገንዝበዋል።

ኢትዮጵያውያን በምንም ሁኔታ ቢሆን ከኢትዮጵያዊነት እንደማይነጠሉ የዲያስፖራ ተሸላሚዎች ማሳያዎቻችን ናቸው ነው ያሉት ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ፤ በአገራችን የመመሰጋገን ችግር መኖሩን ተናግረው እንዲህ ዓይነት መድረኮች መፈጠራቸው ተስፋ ሰጪ መሆኑንም ጠቁመዋል።

በጎ ሰው በጎነትን ለዝናውና ለክብሩ ሲል የሚያደርገው አይደለም ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ ለእኔ ብቻ የሚለውን ስሜቱን አስወግዶ ትላልቅ አስመስጋኝ ሥራዎችን ሲያከናውን ነው ሰው በጎ የሚባለው ሲሉ ገልፀዋል። በጎ ሰው በጎ የሚባለው ለሌላው በር ሲከፍትና ሌላውን ሲያበረታታ እንዲሁም ሌላው እንዲያድግ የሚያደርጉ ተግባራትን ሲፈፅም ነው ሲሉም አክለዋል።

ሰው በጎ ሰው የሚባለው የሚሠራውን ሥራ በትጋት፣ በንፅህና እና በታማኝነት ሲፈፅም እንደሆነ አብራርተው፤ የበጎ ሰው ተሸላሚዎች ከኅብረተሰቡ መጠቆማቸው ይህንን የሥራ ትጋታቸውን፣ በንፅህና መሥራታቸውንና ታማኝነታቸውን የሚያረጋግጥ ነው ብለዋል። እነዚህን ዕሴቶች ይዘን ለሌላው እንዲሠርፅ ማድረግ መቻል ይኖርብናልም ሲሉ ተናግረዋል።

የዓመቱ በጎ ሰው በበጎ ሰው ሽልማት በጎ አድራጎት ድርጅት የሚከናወን ለአገርና ለሕዝብ ውለታ የዋሉ ሰዎችን የሚሸልም መርሃግብር ነው። ዘንድሮ ለአሥረኛ ጊዜ የተካሄደ ሲሆን ከዚህ በፊት ባከናወናቸው ዘጠኝ ዙሮች 187 በጎ ሰዎችን መርጦ ዕውቅና እና ሽልማት ሰጥቷል። ዘንድሮም በአሥረኛ ዙሩ አንድ ልዩ ተሸላሚ እና 27 ተሸላሚዎችን በዘጠኝ ዘርፎች ሽልማትና ዕውቅና ሰጥቷል።

# የአሸባሪውን ሕወሓት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ሕወሓት ለሦስተኛ ጊዜ በቀሰቀሰው ጦርነት ላይም ሆነ በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ላይ በአንድነት በመቆም የዓለም ማኅበረሰብ የኢትዮጵያን እውነታ እንዲገነዘብ እየሠራ እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

የዳያስፖራው ማኅበረሰብ በነገው ዕለት ታላቅ ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ አሸባሪው ሕወሓት የቀሰቀሰውን ጦርነት በማስመልከት ድምፃቸውን እንደሚያሰሙ ገልፀዋል።

ከዚህ ቀደም ‘#በቃ’ ወይም ‘#No more’ በሚል የተለያዩ ዘመቻዎችና ድጋፎች ሲደረጉ የቆዩ ሲሆን አሁንም የተለያዩ አገራዊ ጉዳዮችን በማንገብ በተለይም አሸባሪው ሕወሓት ለሦስተኛ ጊዜ የቀሰቀሰውን ጦርነት በማውገዝ የትዊተር ዘመቻ፣ ሰላማዊ ሰልፎች እንዲሁም የአገር መከላከያ ሠራዊት ድጋፍ የማድረግ መርሃ ግብር የሚከናወን መሆኑን ተናግረዋል።

በተጨማሪም ዳያስፖራው ለተለያዩ ዓላማዎች የሚውሉ የገንዘብ ማሰባሰቢያ መርሃ ግብሮችና ድጋፎች ለማድረግ ዝግጅት ላይ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

እንደ ወ/ሮ ብርሃኔ ገለፃ መንግሥት ሰላም የማስከበር ሙሉ ኃላፊነት አለበት። ይህን የሽብር ቡድን ሴራና አገር የማተራመስ ድርጊት ለመላው የዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ የማሰማትና የማጋለጥ ተግባራት ሲከናወኑ የቆዩና አሁንም ዘመቻዎቹ የሚቀጥሉ ይሆናል።

የአሸባሪውን ሕወሓት ዓላማ ደግፈው የሚንቀሳቀሱ የዳያስፖራ አባላት የቡድኑን ድርጊት በመገንዘብና እውነታውን በመረዳት እኩይ እንቅስቃሴውን ለመግታት እንዲንቀሳቀሱ ጥሪ አቅርበዋል።

አገር ውስጥ ያሉ ዜጎች ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ እውነታውን ለማሳወቅ ባሉበት ሆነው የትዊተር ዘመቻዎችን በመቀላቀል መሳተፍና የአገር መከላከያ ሠራዊትን በማንኛውም ረገድ በመደገፍ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል ብለዋል።

በእስከ አሁኑ ሂደት የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአሸባሪው ቡድን የሰጠው ዕድል እናሳ ባለመሆኑና የሽብር ቡድኑ ዕድሉን ሳይጠቀም በመቅረቱ የሁሉም ችግሮች ምንጭ የሆነውን አሸባሪ ኃይል ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሁሉም ሊዘምትበት ይገባል ብለዋል።

መንግሥት የእያንዳንዱን ዜጋ ቀዬ ሊጠብቅና ሊደርስ ባለመቻሉ ማኅበረሰቡ በራሱ አደረጃጀት በመገንባት ከመንግሥት ጋር በመሆን ሊጠብቅ የሚገባው መሆኑን ገልፀው፣ የዳያስፖራው ማኅበረሰብም በዚህ ረገድ የራሱን አስተዋፅዖ እያደረገ መሆኑን አመልክተዋል።

በውጭ አገር የሚኖረው ማኅበረሰብ ከራሱ የሕይወት ውጣ ውረድ አልፎ በዚህ መልኩ ለአገር እየሠራ በመሆኑ በመንግሥትና በዳያስፖራው መካከል ያለው ግንኙነት መጠናከር አለበት ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሳረጁ የክፋት ፖለቲከኞች ከንቱ ቅዠት የትግራይ ሕፃናትን ሕይወት መገበር ይብቃ!

«እስካሁን ባካሄድከው ጦርነት ከሕዝብ እልቂት፣ ከረሀብና ችግር ውጪ ምን አተረፍክ፤ ልጆቻችን የታሉ» ለሚለው የትግራዋይ እናቶች ጥያቄ የሚሰጠው ምላሽ የሌለው አሸባሪው ሕወሓት ከመንግሥት በተደጋጋሚ ጊዜ የቀረበለትን የሰላም አማራጭ ወደ ጎን ብሎ ለሦስተኛ ጊዜ ጦርነት አውጆ ወደ ጥፋት ተግባሩ ከተሰማራ ቀናት ተቆጥረዋል።

ትምህርት ቤቶችን ዘግቶ ዕድሜያቸው ለውትድርና ያልበቁ ለጋ ሕፃናት አንድም በተራ ፕሮፖጋንዳ በማወናበድ ከዚያም አለፍ ሲል በቤተሰቦቻቸው ላይ «የልጅ አዋጡ» አስገዳጅ ኮታ በመጣል እድሜውን ለማርዘም በለኮሰው ጦርነት በርካታ የትግራይ ተወላጆችን ለእልቂት እየዳረገ ይገኛል።

ሕፃናትን ለጦርነት ማሰለፍ ሰብአዊነት የጎደለው የጭካኔ ተግባር ከመሆን ባለፈ፤ በዓለምአቀፍ ሕግ የሚያስጠይቅ ከፍ ያለ ወንጀል ቢሆንም፤ ይህንን እኩይ ተግባር ዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ አይቶ እንዳላየ፤ ሰምቶ እንዳልሰማ በመሆኑ ቡድኑ ዛሬም ድረስ በወንጀሉ ተግባሩ እንደገፋበት ይገኛል።

ይኸው አሸባሪ ድርጅት ቀደም ባለው ጊዜ በአፋርና አማራ ክልሎች ባካሄደው ወረራ በተመሳሳይ መልኩ ሕፃናትን ያለ አቅማቸው መሣሪያ አስታጥቆ ባዘመተበት ወቅት፤ አንዳንድ ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን ድርጊቱን ከማውገዝ ይልቅ እንደ ጀብዱ በመተረክ በጦርነቱ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሕፃናት ለእልቂት እንዲዳረጉ ምክንያት ሆነዋል።

በሕፃናቱ ላይ ትናንት በአደባባይ ለተፈጸመው ወንጀል ዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ ተገቢውን ምላሽ ባለመስጠቱ፤ ቡድኑ በማያቆመው የጭካኔ ተግባሩ ዛሬ ላይ ከቀደመው ጦርነት የተረፉትን ሕፃናት ለዳግም ጦርነት አሰልፏቸዋል። ትግራይን ትውልድ አልባ በሚያደርግ ክፋት ውስጥም እየዳከረ ይገኛል።

በዚህም «ጦርነቱን በሕዝብ ማዕበል እወጣዋለሁ» ብሎ በአደባባይ እየተናገረና እየፎከረ ሕፃናት፣ ወጣቶችና ሴቶችን ከፊት ከፊት በገፍ በማሰለፍ የጥይት ማብረጃ እያደረጋቸው ነው። ገና ቦርቀውና ተጫውተው ያልጠገቡ፣ ደብተር ጨብጠው የትምህርት ቤት ደጃፍ መርገጥ የናፈቃቸውን ልጆች ምንም በማያውቁት ጦርነት በማሰለፍ ግፍ እየፈጸምም ይገኛል።

የሸብር ቡድኑ ትውልዱ የነገ አገር ተረካቢ፣ የወላጆቻቸው አለኝታና መከታ፤ ጧሪና ቀባሪ እንዳይሆኑ፤ ከዚህ ይልቅ ሳረጁ የክፋት ፖለቲካ አራማጆች ዕድሜ ማራዘሚያ የፖለቲካ ቁማር የዕድል ካርድ አድርጎ እየሄደበት ያለው የጥፋት መንገድ የሚያስከትለው ችግር ትውልድ ተሻጋሪ እንደሚሆን ይታመናል።

ይህን እኩይ ተግባሩ እንዲቆምና ትውልዱ ለራሱ፣ ለቤተሰቡና ለአገሩ ተስፋ እንዲሆን ከሁሉም በላይ የትግራይ ሕዝብ፤ በተለይም የትግራይ እናቶች ልጆቻችንን አንሰጥም እምቢ ሊሉና ልጆቻቸውን ካላስፈላጊ ሞት ሊታደጉ ይገባል።

የቡድኑ አመራሮች የራሳቸውን ልጆች ምቾት ባለባቸው፣ ደህንነታቸውና ጤንነታቸው በሚጠበቅባቸው ከፍተኛ ወጪን በሚጠይቁ የውጭ አገራት ትምህርት ቤቶች ያስተምራሉ። የራሳቸውን ልጆች ከአደጋ አርቀው በቅንጦት ለትልቅ ደረጃ ለማብቃት ሳይታክቱ ይሠራሉ፤ በዘረፋትም የአገር ሀብት ቅንጡ ኑሮ እንዲኖሩ እና እንዲማሩ ያደርጋሉ። በተቃራኒው ደግሞ ምግብ በልቶ ያልጠገበውን የደሃዋን የትግራይ እናት ልጆች በጦርነት ይማግዳሉ።

የእነሱ ልጆች ከታዋቂ የውጭ አገር ዩኒቨርሲቲዎች ሲመረቁና በዚህ ሲፈነድቁ አንዴ በዘረፋ ሌላ ጊዜ ደግሞ ትርጉም በሌለው ጦርነት ልጆቿን እየነጠቁ የደሃዋን የትግራይ እናት መርዶ አንድትሰማ ያደርጋሉ። ይሄ አሳዛኝ እውነት የዓለም አቀፉን ማኅበረሰብ በተለይ በሕፃናት ላይ እንሠራለን የሚሉ ተቋማትን ሊያስቆጭና ሊያስጮህ ይገባል።

መላው ዓለም ቡድኑ በተለያዩ ማደናገሪያዎችና በአስገዳጅ ሁኔታ ያለዕድሜያቸው በውትድርና አሰልፎ በጦርነቱ ስለሚማግዳቸው ሕፃናት ድምጽ ለመሆን ወቅቱ አሁን ነው። ከሁሉም በላይ የትግራይ እናቶች የሕፃናት ልጆቻችንን ለጥይት መገበርና፣ የልጅ ኀዘን መረረን በቃን ሊሉ ይገባል።

ቡድኑ እየፈጸመ ያለውን ዓለም አቀፍ ወንጀል ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃንም ሆኑ የሕፃናት መብቶች ላይ የሚሠሩ ዓለምአቀፍ ተቋማት አይተው እንዳላየ፤ ሰምተው እንዳልሰማ ከመሆንና የህሊና ፍርድ ተጠያቂዎች ከመሆን ሊርቁ ይገባል። ምክንያቱም ጉዳዩ ከሞያ ስነ ምግባር፤ ከሰብአዊነትና ከተቋማዊ ኃላፊነት አንጻር ከፍ ያለ ተጠያቂነት የሚስከትል ነውና ።

በአጠቃላይ ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን እና የሕፃናት መብቶች ላይ የሚሠሩ ዓለምአቀፍ ተቋማት ከዝምታቸው ወጥተው የሸብር ቡድኑን እኩይ ተግባር በማውገዝ ለትግራይ ሕፃናትና እናቶች ድምጽ ሊሆኑ ይገባል!


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ሁሉም ለአገሩ ዘብ - ለሠራዊቱ ደጀን ይሁን

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

እነሆ ! የዝናቡ ፣ የክረምቱ ወቅት ሊያልፍ አሁን ጊዜው ቀርቧል። ከወንዝ ጅረቱ፣ ከጭቃው ብርዱ፣ ከነጎድጓድ መብረቁ ጀርባም አዲስ ቀን ሊብት መስከረም ሊጠባ ግድ ነው። ይህ እውነት ዕውን ይሆን ዘንድ የተፈጥሮ ህግጋት ያስገድዳሉ። በተፈጥሮ ህግ እውነታዎች አይዛቡም፣ መሰረቶች አይናጉም። የነበረው በሂደቱ ይቀጥላል፣ የሚሄደው በሚመጣው ይተካል።

የጽሁፌን መነሻ በተፈጥሮ ህግ ላይ መመሰሌ ያለምክንያት አይደለም። ተፈጥሮን ከባህሪውና ከህጉ ጋር ለማዛመድ የመሻቴ እውነት አሁንም በምክንያት ነው። በእኔ እሳቤ ልክ እንደተፈጥሮ ሁሉ ጉዳዮቻችንን ሳናዛባ ከያዝን ዒላማችን ግቡን አይስትም። ከመነሻ እስከ መድረሻ የሚኖረው መስመር ሳይንጋደድ፣ሳይጣመም ከታሰበው ይደርሳል።

ከጥንት እስከዛሬ ስንመሰክረው የኖርነው ኢትዮያዊነት መሰረቱ የጠበቀ ፣ ውሉ የተገመደ ህብር ነው። ይህን ሀቅ ደግሞ በየዘመናቱ ሊያጠቁን የቀረቡን ጠላቶቻችን ጭምር ሲመሰክሩት ኖረዋል። እኛም ይህ የዜግነት ጥምር ድር በየምክንያቱ ሲገለጥ አይተናል።

ሀገር በርሀብና ድርቅ ከስጋት በወደቀች ጊዜ ማንነታችን በተግባር ተረጋግጧል። በተፈጥሮ አደጋና መሰል ችግሮች በጽኑ ስትፈተንም አንድነታችን ከእኛው ጋር ነበር። ኮቪድን በመሰሉ ክፉ ወረርሽኞች በተጠቃን ጊዜም ወገን የወገኑን እጆች ጨብጦ ክፉውን ዘመን ተሻግሯል።

ይህ ብቻ አይደለም ። አብሮን በኖረው የመተጋገዝ፣ መረዳዳት ባህላችን የብዘዎችን ዕንባ ማበስ ልማዳችን ነው። አውደ ዓመት በደረሰ ጊዜ በርካቶቻችን ያጣ ፣ የነጣ ጎረቤታችን ላይ ጀርባ አዙረን በር ዘግተን አንበላም። ያለንን ካለው ተካፍለን ፣ በጎደለው ሞልተን ኑሮን መምሰላችን ብርቃችን አይደለም። ይህ የኢትዮጵያዊነት ልዩ መገለጫ ከቃል በላይ መለያችን እንደሆነ ዘመናትን ዋጅቷል።

ወደቀደመው ሃሳቤ ልመለስ። ወደማይዛባው የተፈጥሮ ህግና ግዴታዎቹ። አዎ!አሁን የክረምቱ ዝናብ ለበጋው ፀሀይ ተራውን ሊያስረክብ ጊዜው ደርሷል። እንዲህ በሆነ ጊዜ የሞሉ ወንዞች ሊጎድሉ፣በውሀ የራሱ መስኮች በአቧራ ሊሸፈኑ ግድ ይላል። የክረምቱ ብርድ በሙቀት ሲተካ፣ ፀሀይ ሀሩሩ ቦታውን ይይዛል ለምን? ካሉ የውል አይስቴው ተፈጥሮ ግዴታ በመሆኑ ። ይህ አይነቱን እውነት ወደ ራሳችን ወስደን እንኑረው ካልን የኢትጵያዊነትን የተጋመደ ህብር በዚህ ምሳሌ ማጣመር እንችላለን።

አዎ ! ኢትዮጵያዊነት በዘመናት መፈራረቅ ስሪቱን በማይስተው ተፈጥሯዊ ፀጋ ይመሰላል። ኢትዮጵያዊነት የዜግነት ክብሩና ስያሜው በቀላሉ የማይላላ ጥብቅ ሰንሰለት ነው። አንዱ በአንዱ ማንነት ተሳስሮ ባሳለፈው ታሪክም በርካታ ቁምነገሮች ተቀምረው ጥቂት የማይ ባሉ ክፉ ቀናት አልፈዋል።

«እሾህን በእሾህ» እንዲሉ አንድነታችንን ሊበትኑ የወረሩን ባዕዳን ሽንፈትን የቀመሱት በዚሁ የአንድነታችን ግማድ ነው። ይህ የማንነታችን መለያ ክብራችንን አስመልሶ ስማችንን በከፍታ አድምቋል። ይህ ጠንካ ራው ክንዳችን ድንበራችንን በማይፈርስ ግንብ አጥሮ ጥንካሬችንን አውጇል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከሁለት ዓመታት በፊት በጀመረ ችው ሕልውናን የማስከበር ዘመቻ በርካታ ችግሮችን ተሻግራለች። ሰላምን «ዕምቢኝ» ሲል ጦርነትን ምርጫ ባደረገው ወራሪ ሀይልም ዕልፍ ልጆቿ ለሞት ፣ በቀላሉ የማይተኩ ሀብቶቿ ለውድመት ተዳርገዋል። ይህ ብቻ አይደለም አስከፊው ጦርነት ያስከተለው ክፉ ጠባሳ በሺዎች የሚቆጠሩ ወገኖቻችንን ለመፈናቀል ዳርጎ ከድህነት አዘቅት ጥሏል።

በኢትዮጵያ መንግስት በኩል የተኩስ አቁም ውሳኔ ከተደረገ በኋላ እንደ ክፉ አውሬ አድብቶ የከረመው የወያኔ ቡድን ዛሬም የጥፋት እሳቱን ማቀጣጠል ጀምሯል። ለሰላም የተዘረጉ እጆችን ገፍቶ ለሶስተኛ ጊዜ በፈጸመው ጠብ አጫሪነትም ንጹሀንን በማስጨፍጨፍ ፣ ትውልድን ማስጨረሱን ይዟል።

ሽብርተኛው የወያኔ ቡድን «እሞትልሀለሁ» የሚለውን የትግራይ ህዝብ አስቀድሞ መግደል የጀመረው በጦርነቱ ብቻ አይደለም። የሰላም እጦቱን ተከትሎ በተከሰተው ችግር በእርዳታ የሚገባ እህልን ሳይቀር ከአፉ በማስጣል ለርሀብ ጥማት ዳርጎታል። ዛሬ የትግራይ እናቶች ልጆቻቸውን ለጦርነት ማግደው ይልሱት ይቀምሱትን ናፍቀዋል።

አሁን በትግራይ ምድር ከጦርነት ያለፈ ሌላ ህይወት አይታሰበም። ትምህርት፣ ጤና፣መብራትና ባንክ ይሏቸው መሰረታዊ ጉዳዮች የቅንጦት ያህል ተዘንግተዋል። ህዝቡ ለሚሆንበት ግፍና በደል ሁሉ ስለምን ? ሲል መጠየቅ መብት የለውም።

ሃሳብ ጥያቄውን ልሞክረው ቢል ምላሹን አሳምሮ ያውቀዋል። ራሱንና መላ ቤተሰቡን ለጦርነት ከመገበር ውጭ ምርጫ አልተሰጠውም። በግል ፍላጎትና በውጭ ሀይሎች ተላላኪነት ሀገር ለማፍረስ የተነሳው ቡድን ዛሬም ከነዕብሪቱ ቀጥሏል።

በትግራይ ምድር ያሉ ህጻናትና አረጋውያን ፣ሴቶችና ወጣቶች፣ ሌሎች ወገኖቻቸውን ጦር ይዘው እንዲወጉ ግዳጅ ተጥሎባቸዋል። በጥላቻ ፖለቲካ የተሞላው ቡድንም አገርን በማተራመስ ስትራቴጂው ዛሬም ድረስ በንጹሀን ደም መታጠቡን ይዟል።

ጦርነት መቅሰፍት ነው። ክቡር ህይወትን ይነጥቃል፣ አካል አዕምሮን አጉድሎ ሀብት ንብረትን ያወድማል። የጦርነት ሂሳብን የቀመሩ ሀገራት መቼም ቢሆን አትርፈው አያውቁም። ህዝባቸውን ለሞትና ስደት ዳርገው፣ ምድራቸውን ለጥፋት ውሀ አሳልፈው ሰጥተዋል።

እስከዛሬ በነበሩ ታሪኮቻችን አንድ የመሆንን ጥቅም ደጋግመን አይተነዋል። ኢትዮጵያዊነት በእኩል ሲጋመድ፤ ክንደ ብርቱነት ያይላል። ዜጎች በሀገር ጉዳይ በእኩል ሲመከሩ፤ ሃሳብ አይነጥፍም፣ ቃል አይታጠፍም። ሁሉም ወገን «ያገባኛል» ብሎ «አለሁ» ማለትን ሲያውቅ ፈተናዎች ይቀላሉ።

ሀገራችን በባዕዳን ወረራ በተፈተነችባቸው ዘመናት ሁሉ የነጻነቷን ብርሀን ያገኘችው በልጇቿ ብርቱ ትግል ነበር። የዛኔ ከተከፈለው የህይወት መስዋዕትነት ባለፈ ሁሉም በጽኑ አቋም ለሀገሩ ዘብ ቆሞ ደጀን መሆኑን አስመስክሯል። እንዲህ የመሆኑ እውነትም የተገኘውን ድል የመላው አፍሪካ አድርጎታል።

ዛሬም ልክ እንደተፈጥሮ ህግ ውሉን የማይስተው ኢትዮጵያዊ አንድነት በወጉ ተጋምዶ ደጀንነቱን ሊያስመሰክር ይገባል። በህዝብ አንድነትና ህልውና ላይ የተሰካውን የዘመኑን አሜኬላ ከስሩ ለመንቀል የህብረ ብሄራዊነት ጊዜው አሁን ይሆናል።

ኢትዮጵያዊነት « የፀና አንድነት» ነው ስንል አሁንም በምክንያት ነው። የኢትዮጵያዊነት መልክ በብዙ ገጽ ይገለጣል። ህዝቡ ሁሌም ችግር መከራን በአንድ ይሻገራል፣ የጦርነት ወረራን በእኩል ይመከታል፣ ክፉ ወረርሽኙኝ ተደጋግፎ ያልፋል።

የትናንቱ ኢትዮጵያዊነት ዛሬም ቢሆን ነበልባሉ ነዲድ ነው። ህዝቡ በማንነቱ ህብር ለሀገሩ ዘብ ሊቆም ዝግጁነቱን ያሳያል። ደጀን መከታ ሆኖም ወገኑን ከማንኛውም ስጋት ሊታደግ ዘብ ይቆማል። ሁሉም ኢትዮጵያዊ የአንድነት መገለጫዎቹን በተግባር ሲመነዝር ከልቡ ነው።

ሀገር በጠላት ስትወረር አዋጅ ነጋሪት ጎሽሞ፣ በጽኑ ቃል ተማምሎ ደጀን የመሆን ታሪክ ለአበሻ ህዝብ አዲስ አይደለም። ቀፎው እንደተነካ ንብ በቁጣ መትመሙ ለሀገሩ ክብር የሚያሳየው ልዩ ምልክት ነው። ይህ እውነታ ደግሞ ዛሬም በቆምንበት ፈታኝ ዘመን ሊታይና ሊመሰከር የግድ ይላል። ሀገር ከሌለች ወልዶ መሳም፣ ዘርቶ መቃም አይታሰብም። ሀገር በክብር ካልቆመች ተምሮ መለወጥ በነጻነት መተንፈስ አይሞከርም። ሀዘንና ደስታ፣ ሰርግና ሞት ይሉት ወግ መነሻ መድረሻው የሀገር በክብር ጸንቶ መኖር ብቻ ነው።

ዛሬም ኢትዮጵያውያን የአንድነታችን ድር ጠብቆ የማንነታችን ስም ደምቆ እንዲዘልቅ ለሀገራችን ዘብ ልንቆም ይገባል። ለወገናችን ክብር፣ ለመኖራችን ህልውና ስንልም የሚጠበቅብንን ግዴታ በተግባር ልናስመሰክር ግድ ይላል። እንግዲህ እኛ ማለት እንዲህ ነን። ስንተባበር እንበረታለን። ስንጠላለፍ እንወድቃለን።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## የመጀመሪያው የተማሪዎች የጎዳና ላይ የፋሽን ትርኢት በባህርዳር

**ቦጋለ አበበ**

የኢትዮጵያን የፋሽን ኢንደስትሪ ለማሳደግ የተለያዩ የፋሽን ትርኢቶች የሚጫወቱት ሚና ትልቅ ነው። የፋሽን ትርኢቶች በዘርፉ የተሰማሩ የተለያዩ ባለሙያዎች ስራዎቻቸውን ለሕዝብ የሚያስተዋውቁባቸው መድረኮች ናቸው። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ የመድረኮቹ በስፋት አለመኖር በኢንደስትሪው አዝጋሚ እድገት ላይ የራሱን ተፅዕኖ እንዳሳረፈ የዘርፉ ባለሙያዎች ይስማማሉ።

በዚህ ረገድ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቴክስታይልና ፋሽን ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የተለያዩ የፋሽን ትርኢት መድረኮችን በማመቻቸት ያሳየው አበረታች ጅምር ተጠናክሮ መቀጠል ከቻለ ትልቅ ተስፋ እንዳለው እያሳየ ነው።

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቴክስታይልና ፋሽን ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የ2014 ዓ.ም ተመራቂ ተማሪዎች ከሰባት በላይ በሆኑ የፈጠራ ዲዛይኖች የተሰሩ አልባሳትና በልዩ ልዩ ማስጌጫዎች የተዘጋጀ እና በአገራችን የመጀመሪያ የሆነ የተማሪዎች የጎዳና ላይ ፋሽን ትርኢት በባሕር ዳር ከተማ አቅርበዋል፡፡ ባለፈው ነሐሴ 21/2014 ዓም የባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ 60ኛ ዓመት የአልማዝ ኢዮቤልዩ በዓል እና የ2014ዓ.ም የምረቃ ቀንን በማስመልከት የጎዳና ላይ የፋሽን ትርኢቱ ሲካሄድ በዩኒቨርሲቲው ታሪክ የመጀመሪያ መሆኑ ታውቀል።

አዘጋጆቹ የትርዒቱን ስያሜ አዲስ ገፅ ያሉት ሲሆን የባሕርዳር ከተማ እና የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ እንዲሁም በእለቱ በባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ የሚመረቁ ተማሪዎች እስከ ቤተሰቦቻቸው ተገኝተው መመልከት ችለዋል።

ዝግጅቱን በንግግር የከፈቱት የኢትዮጵያ ቴክስታይልና ፋሽን ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ቦርድ ሰብሳቢ አቶ ብርሃን ሀይሉ፣ ተቋሙ በአይነቱ የመጀመሪያ የሆነውን ትርኢት ማዘጋጀቱ ለከተማውም ሆነ በዘርፉ ላሉ አካላት ትልቅ ምዕራፍ መክፈቱን ተናግረዋል። ኩነቱም በፋሽን ቴክኖሎጂ ላይ



**የጎዳና ላይ የፋሽን ትርኢቱ ሲካሄድ በዩኒቨርሲቲው ታሪክ የመጀመሪያ መሆኑ ታውቋል፣**

ያተኮረ በመሆኑ የአገራችንን ቴክስታይልና አልባሳት ኢንዱስትሪን በማሳደግ ረገድና የስራ ዕድል በመፍጠር ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው መናገራቸውን ከዩኒቨርሲቲው የማህበራዊ ገፅ ትስስር የተገኘው መረጃ ያስረዳል።

የኢትዮጵያ ቴክስታይልና ፋሽን ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ሳይንቲፊክ ዳይሬክተር ዶ/ር ታምራት ተስፋዬ በበኩላቸው፣ የኢትዮጵያ ቴክስታይልና ፋሽን ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በ24 ፕሮግራሞች የፒኤች ዲ፣ የሁለተኛ ዲግሪ እና በመጀመሪያ ዲግሪ ደረጃ በማስተማር የባሕር ዳር ከተማን የፋሽን ከተማ ለማድረግ አልሞ እየሰራ እንደሚገኝ ገልፀዋል።

ዶ/ር ታምራት አክለውም፣ ትርኢቱን ያቀረቡት የዩኒቨርሲቲው ተመራቂ ተማሪዎች በሀገሪቱ ውስጥ ተሰማርተው የፋሽን ቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪን ለማዘመን የሚሰሩ መሆናቸውን አስረድተዋል። በዚህም ኢንስቲትዩቱ ከሚያስመርቃቸው 26% የራሳቸውን ስራ ፈጥረው የሚሰሩ ሲሆን ከ85% በላይ የሚሆኑት ደግሞ በተመረቁበት ሙያ የስራ ዕድል ማግኘታቸው እንደ ሀገር የመጀመሪያው ኢንስቲትዩት እንደሚያደርገው ጠቁመዋል።

የዕለቱን ፕሮግራም ያስተባበሩት የፋሽን ዲዛይን ትምህርት ክፍል ኃላፊ መምህር ሰላማዊት መላኩ፣ ተመራቂ ተማሪዎች ሀገር በቀል የሆኑ እና የውጪውን አልባሳት በማቀናጀት ያላቸውን የፈጠራ ስራ በማሳየታቸው ተቋሙንም ሆነ ዩኒቨርሲቲውን ለማህበረሰቡ በማስተዋወቅ ረገድ ፋይዳው የጎላ መሆኑን ተናግረዋል።

በፋሽን ትርኢት ስነ-ስርዓቱ ላይ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ቦርድ አባላት እና የዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ አመራሮችና ሰራተኞች እንዲሁም የከተማው ማህበረሰብ ታድመውበታል። የፋሽን ትርኢቱም ከስካይ ላይት ሆቴል እስከ ዩኒሰን ሆቴል ባለው የጎዳና መንገድ ላይ የተካሄደ ነበር።

ዩኒቨርሲቲው በቅርቡም ለ10ኛ ጊዜ በጥጥ፣ ጨርቃጨርቅ እና አልባሳት የእሴት ሰንሰለት በአፍሪካ በሚል ርዕስ ጉዳይ ዓለም አቀፍ አውደ ጥናት በቴክስታይልና ፋሽን ቴክኖሎጂ ትምህርት ክፍሉ አዘጋጅነት ባቀረበበት ወቅት ደማቅ የፋሽን ትርዒት ማዘጋጀቱ ይታወቃል።

የኢትዮጵያ ቴክስታይልና ፋሽን ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት አገራዊ የኢንደስትሪ ልማት ግባችን ለማሳካት በሚደረገው ጥረት እያሳየ ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ሲሆን፣ ይህን ለማሳደግም የተለያዩ ጥረቶችን በማድረግ ላይ ይገኛል።

የኢትዮጵያ ቴክስታይል እና ፋሽን ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በቴክስታይል ኬሚካል ፕሮሰስ ምህንድስና ፤ በቴክስታይል ምህንድስና፣ በፋሽን ዲዛይን፤ በጋርመንት ምህንድስና ፤ በቴክስታይል እና አፓራል መርቻን ዳይዚንግ እና በሌዘር ምህንድስና የትምህርት መስኮች ላይ ኢንዱስትሪ መር ስርዓተ-ትምህርት በመቅረፅ በተግባር የታገዘ ትምህርት በማስተማር በዘርፉ በርካታ ባለሙያዎችን በመጀመሪያ ዲግሪ፤ በሁለተኛ እና ሶስተኛ ዲግሪ የትምህርት ደረጃ እያስተማረ ይገኛል። በመሆኑም አሁን ላይ ኢንስቲትዩታችን በቴክስታይል ዘርፍ ያሉ የምርምርና ማስተማሪያ ቤተ-ሙከራዎች አደረጃጀትን እያዘመነ ይገኛል።

በISO/IEC 17025:2017 አለማቀፋዊ ይዘት ይዘው ተማሪዎች እና ተመራማሪዎች የምርምር ስራቸውን እንዲያከናውኑባቸው ከማድረግ አንፃር ኢንስቲትዩቱ በቴክስታይል ፊዚካል (Textile physical testing laboratory) እና የቴክስታይል ኬሚካል (Textile chemical testing laboratory) የፍተሻ ቤተ-ሙከራዎች ላይ የጥራት ደረጃ በኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽ/ቤት እውቅና እንዲያገኙ ለማድረግ በርካታ ስራዎችን ሲሰራ ቆይቷል። በዚህም የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽ/ቤት ባደረገው የመጀመሪያ ደረጃ ምዘና የቴክስታይል ፊዚካል እና ኬሚካል የፍተሻ ቤተ-ሙከራዎች (Textile physical and chemical testing laboratory) የሚጠበቅባቸውን የጥራት ደረጃ መመዘኛዎች አሟልተው የመጀመሪያ ዙር ሂደት አልፈዋል። ከዚህ ምዘና በኋላም እነዚህ ላብራቶሪዎች በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለውን ISO/IEC 17025:2017 የላብራቶሪ አደረጃጀት አሟልተው እውቅና የሚያገኙ ይሆናል። ኢንስቲትዩቱ በቀጣይ በሌሎች ቤተሙከራዎች ላይም በተመሳሳይ አለማቀፋዊ እውቅና እንዲኖራቸው የማድረጉን ስራ በስፋት እንደሚሰራም ከዩኒቨርሲቲው የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ነገረ ስብሰባ

**አቤል ገ/ኪዳን**

የእኛ ሀገር የስብሰባ ባህል ሁሌም ያስቀኛል። ስብሰባ እንደመውደዳችን መጠን አሁንም ችግራችን አለመቀነሱ ይገርመኛል። የስብሰባ ፍቅራችን ከፍተኛ ነው። ነገር ግን ስብሰባችን ወደ መፍትሄ አይወስደንም። ከተሰበሰብን በኋላ ስንወጣ ውጊያችችንን እንቀጥላለን።እንደ ስብሰባ ወዳድነታችን እንኳን የእኛን የቀረውን አለም ችግርም መፍታት ይገባን ነበር።ነገር ግን እስካሁን በንግግር የፈታነው ብዙ ነገር የለም።ብዙው ችግራችን አሁንም መፍትሄው እየተፈለገ ያለው በጉልበት ውስጥ ነው።

ስለ ስብሰባ ለማውሳት የፈለግኩት ሰሞኑን ከገጠመኝ ነገር በመነሳት ነው።አንድ ወዳጄ ሰሞኑን ለአንድ ጉዳይ እንደምፈልገው እና አጭር ስብሰባ እንደሚኖረን ነገርኩት። የሰጠኝ መልስ አስገረመኝ። ስንት ይከፈለኛል አለ።እንዲህ አይነት መልስ ሰምቼ ስለማላውቅ ደነገጥኩ። ይህ ወዳጄ ረዘም ላለ ጊዜ በርከት ባሉ የውጭ ሀገራት በስራ የተዘዋወረ በመሆኑ ምናልባትም የእነሱ ተጽእኖ ሊኖርበት እንደሚችል ጠረጠርኩ። ከዚያም ለምን እንደዚህ እንዳለኝ ጠየቅኩት። የእሱ ስራው በቀን ውስጥ በርካታ ስብሰባዎችን ማካሄድ የሚፈልግ ነው። ስለዚህም ስብሰባዎችን የሚለካቸው እና ውጤታማ መሆናቸውን የሚለካው ባለቸው ውጤታማነት እንደሆነ አስረዳኝ። ከእያንዳንዱ ስብሰባም የሆነ አይነት ትርፍ ይዞ መውጣት እንዳለበት እና ይህ ደግሞ አለምአቀፍ ልማድ እንደሆነ ነገረኝ።

የእኛን ስብሰባ መልሼ አስተዋልኩት።ስብሰባችን በአብዛኛው አላማው ምን እንደሆነ አይታወቅም። የብዙው ስብሰባ ግብ ራሱ ስብሰባው መካሄዱ ብቻ ነው። ከስብሰባው ምን ውጤት እንደሚጠበቅ አይታወቅም። እንዲሁ ሰብሳቢው የልቡ እስኪደርስ ድረስ የፈለገውን ያወራል ከዚያ ተሳታፊዎች ደግሞ የመሰላቸውን ይጨምሩበታል፤ በመጨረሻ ስብሰባው በመታከት ያልቃል። ምናልባትም በነዚህ ስብሰባዎች አትራፊ የሚሆነው ለተሳትፎ የሚከፈለው ሆቴል ብቻ ነው።

አንዳንዴ ስብሰባዎቻችን ላይ የምናየው ነገር ከማሳዘን አልፎ ያስቃል። ለምሳሌ አንዳንዱ ተሳታፊ እድል ሲሰጥ ተሻምቶ እድል ይወስድና ከአጀንዳ ውጪ የግል ጉዳዩን ይዘበዝባል። ሌላው ደግሞ ይነሳና የስብሰባው መዘጋጀት በጣም ጠቃሚ እንደሆነ እንዲሁም አቅራቢው ጥሩ አድርጎ እንዳቀረበው፤ መሰል ስብሰባዎች በቀጣይም መዘጋጀት እንዳለባቸው ይዘበዝብና ፍሬ ጉዳዩን ሳያወራ ይጨርሳል። አንዳንዱ ደግሞ ምን አስተያየት መስጠት እንደፈለገ ማሰብ የሚጀምረው ማይክራፎን ከተቀበለ በኋላ ነው። አስቦ ሳይሆን የሚያወራው እያወራ ነው የሚያስበው። ስለዚህም ንግግሩ ፍሬ ጉዳዩም ሆነ መጨረሻው አይታወቅም።

> **ስብሰባዎቻችን በቀናት እና በሰአታት ሳይሆን በደቂቃዎች መለካት አለባቸው። በተሳታፊ ብዛት ሳይሆን በተሳታፊዎች አግባብነት መመዘን አለባቸው**

አዘጋጆቹስ ቢባል የባሰው አስቂኝ አይደሉ እንዴ። አብዛኞቹ ስብሰባውን የሚያዘጋጁት እቅድ ላይ ስላለ ነው እንጂ በጣም አስፈላጊ ስለሆነ አይደለም።እንዲያው በጀቱ ከሚባክን እንጠቀመው ተብሎ ነው ስብሰባው የሚዘጋጀው። በዚያ ላይ ስብሰባው ላይ የሚታደመው ሰው ከስብሰባው ላይ ምንም ግንኙነት የሌለው ነው። ስለ ስፖርት በሚካሄድ ስብሰባ ላይ የሚጠሩት የሸማቾች አባላት ይሆናሉ። በዚህም የተነሳ ከተሳታፊው ህዝብ አብዛኛው ስብሰባው ስለ ምን እንደሆነ ሳይገባቸው እና የረባ ተሳትፎ ሳያደርጉ እንዲሁ አጨብጭበው አበል ተቀብለው ይሄዳሉ።አንዳንዴ ደግሞ ስብሰባው ላይ የቀረበውን ሃሳብ ብቻ በአድናቆት የሚቀበሉ ሰዎችን ብቻ መርጠው ይጠሩና ስብሰባውን የቤተ ዘመድ ጉባኤ ያደርጉታል።

ዛሬ ላይ አለም ስብሰባ የሚባለውን ነገር በብዙ መልኩ እየቀየረው ነው።ቴክኖሎጂ የሰውን በአካል መገናኘት በጣም ቀንሶታል።ኢሜይል ፤ ቴሌግራም፤ ዙም እና መሰል ቴክኖሎጂዎች ሰዎች ቢሮአቸው ውስጥ ሆነው ስራቸውን እየሰሩ እንዲሰበሰቡ የሚያደርግ ዘመን ላይ ደርሰናል።ስብሰባዎች ላይ የሚጠሩት ሰዎች የሚመለከታቸው ብቻ ሆነዋል።ስብሰባው የሚወያይበት አጀንዳ ተመርጦ የሚደረግበት ሰአትም ተመጥኖ ፤ ግቡም ታውቆ ነው የሚካሄደው።ከሁሉም በላይ የስብሰባ ልማዳቸው የጉልበት ተግባር እንዲቀር አድርጓል ፤ ህዝባቸውም በቋሚነት ለወጥ ውስጥ እንዲኖር አድርጓል።

እኛ ጋር ነገሩ በተቀራኒው ነው። አብዛኞቹ ስብሰባዎች አዲስ አጀንዳ የላቸውም። የዛሬ አመት ያወራንበት አጀንዳ ዘንድሮም አለ። አምና ከስብሰባው በኋላ ያቋቋምነው ኮሚቴ ከሸፎ ዘንድሮም ሌላ ኮሚቴ እናቋቁማለን። አምና ስብሰባው ላይ መካሄዱን አድንቀው አስተያየት የሰጡ ሰዎች ዘንድሮም ስብሰባው መዘጋጀቱ በጣም ጠቃሚ እንደሆነ ይናገራሉ። አምና ስብሰባው ላይ ሲያንቀላፉ የነበሩ ሰዎች ዘንድሮም እያንቀላፉ ነው። ከአምናው የተለየ አንድ አዲስ ነገር ቢኖር አምና ለስብሰባ ከወጣው ገንዘብ ዘንድሮ የሚወጣው መብለጡ ብቻ ነው።

የምር የስብሰባ ባህላችን መልሶ መከለስ አለበት። የሆነ ጊዜ እንደውም ህግ ሊወጣለት ነው ሲባል ደስ ብሎኝ ነበር፤ ኋላ ላይ ግን ወሬውም ቀረ። ስብሰባ ግን በአዲስ መልኩ መቃኘት አለበት። ስብሰባዎቻችን በቀናት እና በሰአታት ሳይሆን በደቂቃዎች መለካት አለባቸው። በተሳታፊ ብዛት ሳይሆን በተሳታፊዎች አግባብነት መመዘን አለባቸው። ከወጣበት በጀት እኩል ያስገኘው ግብአት መታየት አለበት። ከተሳታፊ ብዛት ይልቅ የተገኘው ግብአት ዋነኛ ቁምነገር ሊሆን ይገባል።

ከሁሉም በላይ ስብሰባ የህዝብን ችግር በቋሚነት በሰላማዊ መንገድ የመፍታትን ባህል እንድናዳብር ካላገዘ እና ለአበል ብቻ የምንፈልገው ከሆነ፤ ነገር ግን ሁሌም ችግር የምንፈታው በጦርነት ብቻ ከሆነ ችግር ስብሰባዎቻችን ለባህል ለውጥ አልጠቀሙንም ማለት ነው። ስለዚህም ስብሰባዎቻችንን መልሰን መቃኘት አለብን።

# ነፃ ሃሳብ

# አሸባሪው ሕወሓት ሦስተኛውን ዙር ጦርነት እንዴትና ስምን መጀመር ፈለገ?

ማሙሻ ከአቡርሻ

### እንደ መግቢያ

"ኢትዮጵያን ለማፍረስ ሲያልም ቢሆን እንገባለን" ሲል በመጨረሻው የጥፋት ጉዞው ዋዜማ ላይ ቆሞ የመፈጠርና መኖሩን ምክንያት ግልጽ ያደረገው የሕወሓት ቡድን፤ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ሌሊት በተፈጸመው የአገር ክህደት አገር አፍራሽ ተልዕኮ ተሸካሚነቱን ለሁሉም ግልጽ አድርጓል፡፡ ከዚህ የክህደት ተግባሩ ማግስት ጀምሮም በኢትዮጵያ በተለይም በሰሜኑ ክፍል በዚሁ ቡድን አማካኝነት ተደጋጋሚ ጦርነት ተስተውሏል፡፡ አገር አፍራሽነቱን ከሂሳብ አወራራጅነት ስሜቱ ጋር አቀናጅቶ ወደ አፋርና አማራ ክልሎች ለወረራ በተሰማራባቸው ወራትም ከሰው ልጅ የማይጠበቅ ሰይጣንን ያስቀና አረመኔያዊ ተግባራትን ፈጽሞ ጉዞውን በሽንፈት ደምድሞ ተመልሷል፡፡ ክስተቱ ታሪክ የማይዘነጋው በርካታ ሰብዓዊም ቁሳዊም ውድመት አስከትሏል፡፡

ዛሬም ይሄው የጥፋት ተልዕኮ ኑረቱ(የጥፋት አዙሪቱ) አገርሽቶበት በመንግስት በኩል የተዘረጋውን የሰላም እጅ ባለመቀበል ለሦስተኛ ጊዜ በአማራ እና አፋር ክልሎች በኩል ጦርነት ጀምሯል፡፡ ይሄን ተከትሎም ቀድሞ በመከላከያ ሰራዊት ሰሜን እዝ ላይ የፈጸመውን ጥቃት "በአርባ አምስት ደቂቃ ውስጥ መብረቃዊ ጥቃት ፈጽመናል" ብሎ በራሱ ሰዎች አምኖም ጭምር ጥቃት ተከፈተብኝ ሲል እንደነበረው የክህደት ግብሩ ሁሉ፤ አሁንም በበቂ ዝግጅትና እቅድ የጀመረውን ጦርነት "በመንግስት በኩል ወረራ ተፈጸመብኝ፤ ጥቃት ተከፈተብኝ" በሚል የማደናገሪያ ቅጥፈቱ ጥፋተኝነቱን ለመሸፋፈን በብርቱ እየጣረ ነው፡፡ እኔም ይሄን የሽብር ቡድኑን ቅጥፈት በመሰረቱ ለመረዳት ያስችላሉ ያልኳቸውን ጉዳዮች "ዓባይን በጭልፋ" ቢሆንም ጥቂት ለማነሳሳት ፈለግሁ፡፡

### አሸባሪው ሕወሓት ምን ይዞ ጦርነት ጀመረ?

መንግስት የሕወሓትን ሁለተኛ ዙር አገር የማፍረስ ወረራ በቀለበሰ ማግስት ያደረገውን የተናጠል ተኩስ አቁም እና ተደጋጋሚ የሰላም አማራጭ ጥሪን ጆሮ ነፍጎ የቆየው ይህ የሽብር ቡድን፤ በእነዚህ ጊዜያት የሰላም ውይይት ሂደቶችን የሚያደናቅፉ ትርጉም አልባ ምክንያቶችን እየደረደረ ከሰላም ይልቅ ስለ ጦርነት እያሰበና እየተዘጋጀ ቆይቷል፡፡ ይሄንን እንዴት ሊያደርግ ቻለ? የሚል ጥያቄ ቢነሳም፤ የሚከተሉትን ጥቂት ማሳያዎች በማንሳት መመልከትና መረዳቱ ተገቢ ይሆናል፡፡

የመጀመሪያው ጉዳይ፤ መንግስት የሽብር ቡድኑን የጥፋት ጉዞ ከሰሜን ሸዋ ገትቶ ወደ ነበረበት ዋሻ በመለሰው ማግስት ስለ ትግራይ ሕዝብ ሲባል ጦርነት አቁሞ የሰብዓዊ ድጋፍ እንዲገባ ማድረግ እና የሰላም ንግግር መጀመርን ነበር ታሳቢ ያደረገው፡፡ ይሁን እንጂ የሽብር ቡድኑ የሰብዓዊ ድጋፍ መድረሱም ሆነ የሰላም ንግግር ማድረጉን ፈጽሞ አይፈልገውም ነበርና ሁለቱም እንዳይሳኩ በብዙ ለፍቷል፡፡ የሰብዓዊ ርዳታ ኮሪደሮችን በታጣቂዎቹ እንዲዘጋ፤ የሰላም አማራጩም በተደጋጋሚ ትንኮሳ እንዳይሳካ ጥሯል፡፡ ይሄን ተከትሎም መንግስት የትግራይን ሕዝብ ሰብዓዊ ርዳታ እንዲደርሰው ባደረገው ያላሰለሰ ሥራ የሰብዓዊ ርዳታ ማስገቢያ ኮሪደሮች ከሽብር ቡድኑ እንዲጸዱ በማድረግ ከተባባሪ ዓለማቀፍ ግብረሰናይ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በአየርም፤ በየብስም ድጋፍ እንዲደርስ ማድረግ ችሏል፡፡

በዚህም ባለፉት ወራት ብቻ ከአምስት ሺህ 600 በላይ በመኪና /በየብስ ትራንስፖርት/፣ ከ270 በላይ በረራ /በአየር ትራንስፖርት/ ታግዞ የሰብዓዊ ድጋፍ ወደ ክልሉ እንዲገባ ተደርጓል፡፡ ሆኖም የሰብዓዊ ድጋፉ ለሕዝቡ እንዲደርስ ማድረግ እንዳልተቻለ የተለያዩ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህ ለምን ተብሎ ሲጠየቅ ደግሞ፤ ድጋፉን ወደ ሕዝቡ ለማድረስ የሚያስችል ነዳጅ የለም የሚል ምክንያት ይቀርብ ነበር፡፡ ይሄንንም አለም ቀፍ ድርጅቶች ጭምር ሲያስተጋቡት ተስተውሏል፡፡ የሚባለው ነዳጅ ከገባ ቦኋላ ግን ቀጣይ የነበረው ዜና "አሸባሪው ሕወሓት ከዓለም ምግብ ፕሮግራም መጋዘን ነዳጅ ዘረፈ" የሚለው ነው፡፡

ይሄንንም በመንግስታቱ ድርጅት ዋና ጸሐፊ የአንቶኒዮ ጉተሬስ ቃል አቀባይ ስቴፋን ዱጃሪክ በኩል "ሕወሓት መቐለ ከሚገኘው ከዓለም ምግብ ፕሮግራም መጋዘን 12 ታንከር (570 ሺህ ሊትር) ነዳጅ ዘርፏል፤ በቦታው የነበሩ የመንግስታ ድርጅት እርዳታ ሰጪዎች ዝርፊያውን ማስቆም አልቻሉም፤ የነዳጅ ክምችቱም ምግብ፣ ማዳበሪያን እና አስፈላጊ የሰብአዊ እርዳታ ቁሳቁሶችን ለማጓጓዝ የሚውል የነበረ ሲሆን፤ የነዳጁ በሕወሓት ቡድን መዘረፍ ለአካባቢው ማህበረሰብ የሚሰጠውን ሰብአዊ ድጋፍ ይጎዳዋል፤ የተባበሩት መንግስታት ድርጅትም ለሰብዓዊ ስራ ሊውል የነበረው ነዳጅ ላይ የተፈፀመውን ዝርፊያ አጥብቆ ያወግዛል፤" ሲሉ ነበር በራሳቸው አንደበት ያስደመጡት፡፡

ምንም እንኳን በመግለጫው ይሄን ቢባልም፤ ይሄን መሰል ዘረፋና ቅጥፈት ለሽብር ቡድኑ አዲስ ያልሆነና በመንግስትነት ዘመኑ ጭምር ሲፈጽመው የኖረው ነው፡፡ ይሄኛው ድርጊቱ ግን ቡድኑ ምን ያህል በተጠናና በታቀደ መልኩ በውስጥም በውጭ ኃይሎችም እገዛ ለጦርነት ሲዘጋጅ እንደነበር ግልጽ ያደረገ ተግባር ነበር፡፡ ለምሳሌ፣ ይህ ቡድን የሰብዓዊ ድጋፍ ጭነው ወደክልሉ ከገቡ ተሽከርካሪዎች ውስጥ ከአንድ ሺህ በላዩን እዛው ሲያስቀር በፌዴራል መንግስት በኩል ለተነሳው ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት የደፈረ አልነበረም፡፡ ይልቁንም የደርሶ መልስ ነዳጅ ሞልተው የሄዱ ተሽከርካሪዎች "በነዳጅ እጥረት ምክንያት ነው ያልተመለሱት" የሚለውን የሽብር ቡድኑን ነጭ ቅጥፈት ለማስተጋባት ተሞክረዋል፡፡ በዚህም ሰብዓዊ ድጋፍ ጭነው ወደትግራይ ክልል የገቡ ተሽከርካሪዎች እዛው እንዲቀሩ ሆኗል፡፡ ይሄም ተሽከርካሪዎቹን ለጦርነቱ ማሳለጫ የማዋል የራሱ ምክንያትና ዓላማ ነበረው፡፡

ይህ ብቻም አይደለም፡፡ ሕወሓት በህዝቡ ስም ወደክልሉ የሚገቡ የሰብዓዊ ድጋፎች በቀጥታ ለሕዝቡ ከማድረስ ይልቅ ሰብዓዊ ድጋፍን የታጣቂ መመልመያ መንገድ አድርጎ የመጠቀሙን መረጃ ከፌዴራሉ መንግስት በቀር ሊናገረውም፣ ሊያወግዘውም የደፈረ አልነበረም፡፡ ይሄም የሽብር ቡድኑ ለጦርነት ለሚያደርገው ዝግጅት ሰዎች ወድደው ሳይሆን ተገድደው የቤተሰቦቻቸውን ሕይወት ለማትረፍ ሲሉ ወደ ቡድኑ ታጣቂዎች እንዲቀላቀሉ እና የሰው ኃይሉን እንዲያጠናክር እድል እንዲያገኝ ሆን ተብሎ የተሰራ ነበር፡፡

በዚህ መልኩ እህልን በሰው ለውጦ ሃይል በማሰባሰብ ስልታቸው የሚፈልጉትን ያህል የሰው ሃይል ያስገኘላቸው አልነበረም፡፡ እናም ልጅን በሰብዓዊ ድጋፍ እንዲለውጥ ከማስገደድ ባሻገር ሕዝቡን ወደማስፈራራት ገብተዋል፡፡ በዚህም ሕወሓት በሚያካሂደው አገር የማፍረስ ጦርነት የማይሳተፍ ሰው በትግራይ ውስጥ ቦታ የለውም ሲሉ የሽብር ቡድኑ መሪ ደብረጽዮን በአደባባይ ሲያስፈራሩና ሲፎክሩ ተደምጠዋል፡፡ ይሄም ሕዝቡ ተስፋ ቆርጦ አብሯቸው እንዲሆን እና በጦርነት ሂደት የሕዝብ ማዕበልን እንደ አንድ የጦር ስልት ለመጠቀም ያላቸውን እቅድ ለማሳካት የሚያስችል የሰው ሃይል ለማሰለፍ እንዲችሉ ሆን ተብሎ የተሰራ ነበር፡፡ አሁን ላይ ሕጻናትና አረጋውያን ሳይቀሩ በሕዝብ ማዕበል እየተገፉ የሚገቡበትን አካሄድ ለተመለከተም የዚሁ ሥራቸው ውጤት መሆኑን መረዳት አያዳግተውም፡፡

ይህ ሁሉ የሆነው ግን በእቅድና ለታለመ ጦርነት ለሚውል ዝግጅት በሚል መሆኑ ግልጽ የወጣው ሕወሓት ሦስተኛ ዙር ጦርነት መክፈቱን ተከትሎ ነው፡፡ ምክንያቱም አሸባሪው ሕወሓት ተደጋጋሚ የሰላም ጥሪዎችን ሲገፋ እና ምክንያት ሲደረድር የኖረው የተራዘመ ጦርነት ውስጥ የመግባት እና ሦስተኛውን ዙር ጦርነት የመቀስቀስ ድብቅ ምኞቱን ለማሳካት ጊዜ እንዲያገኝ በማሰብ ነበር፡፡

ከዚህ ጋር አያይዞ ቡድኑ ምን ይዞና ተማምኖ ይሄንን ጦርነት ጀመረ? የሚለውን ለመመልከት አራት ነገሮችን ማንሳቱ በቂ ነው፡፡ አንደኛ የሰው ሃይሉን አደራጅቷል፡፡ ለዚህ ደግሞ ቀድሞውንም የሱን እኩይ ዓላማ እንዲሸከሙ የተደረጉ ሃይሎች በወዶ ገብነት ተመልምለው በቂ ስልጠና ተሰጥቷቸው ተዘጋጅተዋል፤ በመቀጠልም ለቤተሰቦቻቸው ሕልውና ሲሉ በሰብዓዊ ርዳታ ምግብ ተለውጠው ለእኩይ ዓላማው የተመለመሉና የተዘጋጁ ኃይሎች አሉ፤ በሶስተኛ ደረጃ፣ በትግራይ ውስጥ ቦታ እንዲኖራቸው ሲሉ በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ተገድደው በገፍ እንዲቀላቀሉ የታጨቁ ቡድኖች አሉ፡፡ የእነዚህ ድምር ውጤት ቡድኑ በሰው ሃይል ተደራጅቶ ጦርነት እንዲጀምር አድርገውታል፡፡

ሁለተኛው ዝግጅቱ ለታጣቂዎቹ የሚያውለው ምግብ ነው፡፡ ይሄም በሰብዓዊ ድጋፍ ስም ወደክልሉ የገባው ምግብና መድሃኒት ለህዝቡ ሳይደርስ በመጋዘን እንዲቆይ በመደረጉ በቀጥታ ለታጣቂው ሬሽን አውሎታል፡፡ ሌላው የተማመነበት አቅም ሎጀስቲክስ ነው፡፡ ይህ ትጥቅና መጓጓዣን ይመለከታል፡፡ በዚህ ረገድ ከአንድ ሺህ በላይ ርዳታ ጭነው የገቡ ተሽከርካሪዎች እዛው እንዲቀሩ አድርጓል፤ ለእነዚህ ማንቀሳቀሻ የሚውል ነዳጅም ደብቆም፣ ዘርፎም አዘጋጅቷል፡፡ በዚህ በኩልም በቀላሉ ያሰባሰባቸውን ታጣቂዎች ለማንቀሳቀስ የሚያስችለውን በቂ ዝግጅት አድርጓል፡፡ በትጥቅ በኩል ደግሞ፣ አንድም በመንግስትነት ዘመኑ በየዋሻውና በመሬት ውስጥ የቀበራቸው፤ ሁለተኛም ከሰሜን እዝ ላይ የወሰዳቸውና በኋላም በወረራው ወቅት የሰበሰባቸው ከነፍስ ወከፍ እስከ ሜካናይዝድ ትጥቆች አሉት፡፡

ከዚህ ባለፈም በተለያየ ጊዜ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት በመጋፋት ጭምር መሳሪያ ሊያቀብሉ የሞከሩ ታሪካዊ ጠላቶች አሉ፡፡ ለዚህ አንዱ ማሳያ ደግሞ በአየር ኃይል ተመትቶ የወደቀው ትጥቅ የጫነ አንቶኖቭ ነው፡፡ በዚህ መልኩ በትጥቅ በኩል አቅም ፈጥሯል፡፡ የመገናኛና ቴክኖሎጂ ውጤቶችንም በዚሁ አግባብ ተለግሷል፤ የፕሮፓጋንዳና የሚዲያ ጦሩንም በውጪም፣ በውስጥም አስቀድሞ አሰማርቷል፡፡ በመሆኑም ቡድኑ የሰላም ጥሪውን በምክንያት እየገፋና ጊዜ እየገዛ ከርሞ በዚህ መልኩ በሰው ሃይልም በሎጀስቲክስም ራሱን በማደራጀት ነው ሶስተኛውን ዙር ጦርነት የጀመረው፡፡

### ስምን ዓላማ ጦርነቱን ጀመረ?

ይህ ጦርነት ለማንም የማይጠቅም ይልቁንም ለሀገርም ሆነ ለህዝብ ከፍ ያለ ኪሳራን የሚያስከትል መሆኑ ቢታወቅም፤ የሽብር ቡድኑ ግን ሕልውናዬ በጦርነት ውስጥ ይረጋገጣል ብሎ ስላመነ፤ እንዲሁም የጥፋት ተልዕኮውን ለመፈጸም ሲል ጀምሮታል፡፡ ምክንያቱም በአንድ በኩል በዘመናት ሂደት ውስጥ በወንጀልና ሌብነት፣ እንዲሁም የትግራይን ወጣት ላልተገባ እልቂት እየዳረገ የኖረ በመሆኑ ከትግራይ ሕዝብ የሚነሳበትን ጥያቄ የመመለስ አቅም የሌለው በመሆኑ፤ በሌላ በኩል ከተለያዩ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች የተሰጠውን ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያውያንን የመበታተን ተልዕኮ በወጉ ሰርቶ ባለማጠናቁ ይሄንኑ የማድረግ ግዴታ የገባ በመሆኑ ነው፡፡ ሃሳቡን ግልጽ ለማድረግ አንዱን ማሳያ ላንሳ፡፡

እንደሚታወቀው የትግራይ ሕዝብ ለሃምሳ ዓመታት የሚጠጋ ጊዜን በነጻነትና ልማት ስም በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ልጆቹን ገብሯል፤ ዛሬም በነጻነት ስም እየገበረ ይገኛል፡፡ ሆኖም በእነዚህ ዓመታት ልጆቹን ለሞት ከመዳረግ የዘለለ የሚጠበቀው ነጻነትም ሆነ ልማት እውን አልሆነለትም፡፡ ይባስ ብሎ እንደ መዥገር ተጣብቆ ደሙን እየመጠጠ የራሱን ህልውና የሚያዘልቅ ቡድን ሰላሙን፣ ነጻነቱን፣ በሕይወት የመኖር ሰብዓዊ መብቱንና በልቶ የማደር ሕልውናውን ነጥቆታል፡፡ እንደ አገር በተለይም በትግራይ ክልል ሰላም ከሰፈነ የትግራይ ሕዝብ ዛሬ ልጆቼ የት አሉ? ነጻነቴስ? በልቶ የማደር ዋስትናዬና በሕይወት የመኖር ሰብዓዊ መብቴ ወደየት ሄዱ? ብሎ መጠየቁ አይቀርም፡፡

ይሄ ከሆነ ደግሞ ሕወሓቶች ለሕዝቡ የሚሰጡት መልስ ስለሌላቸው ሕዝቡ ለተቃውሞ መነሳቱ፤ ቡድኑንም ተጠያቂ ማድረጉ አይቀርም፡፡ ስለዚህ ይህ ከመሆኑ በፊት ሕዝቡን አስጨንቆና በዙሪያው የጠላት ምስል ፈጥሮ በጦርነት ውስጥ እንዲኖር፤ በልቶ የማደር ሕልውናው በቡድኑ ላይ እንዲመሰረት፤ ለማያባራ ጦርነት ልጆቹን እየገበረ የሰቀቀንና ሃዘን ኑሮን እንዲገፋ ማድረግን መርጦለታል፡፡

ቡድኑ በአንድ በኩል ከትግራይ ሕዝብ ጥያቄ ለመዳን፤ በሌላ በኩል ከተልዕኮ አቀባዮቹ የላቀ ክብርና ሞገስን የሚያስገኝነትን ኢትዮጵያን የማፍረስ ሕልሙን ለማሳካት ሲል የትግራይን ታዳጊዎች በሕዝባዊ ማዕበል ለእሳት ለመማገድ ባልጠነከረ ክንዳቸው ብረት በማሸከም ከህዝቡ ላይ የዕለት ጉርሱን ነጥቆ ጦር ሰብቆ እሳት ለኩሷል ፡፡ ዳግም አገርን የማፍረስ፣ ወገንን የማጎሳቆል፣ ሃብት ንብረት የማውደምና የመዝረፍ፣ ሴቶችን በቡድን የመድፈር፣... የአውሬነት ፍላጎቱን ሁሉ ለመፈጸም ያስችለኛል ያለውን ጦርነት ጀምሯል፡፡

### ለማስታወስ ያህል

ይህ ቡድን የትግራይ ወጣቶችን ጭዳ አድርጎ ከጫካ አራት ኪሎ ቤተመንግስት ሲገባም ሆነ በ27 ዓመታት የመንግስትነት ቆይታው ዓላማው ኢትዮጵያን ከፍ አድርጎ ማስተዳደር፤ ኢትዮጵያውያንን በአንድነት ሰንሰለት ማስተሳሰር አልነበረም፡፡ ይልቁንም የቡድን ፍላጎቱን አግዝፎ፣ የተልዕኮ አስፈጻሚነቱን አስቀድሞ በዘረፋ፣ በሰብዓዊ መብት ጥሰት፣ በሴራና አፈና ተግባር ላይ ተጠምዶ የኖረ ነው፡፡

አፈናና ጭቆና የመረረው ሕዝብ ከስልጣን ካወረደው በኋላም፤ ቡድኑ እኔ ያልመራኋት አገር ልትኖር አይገባም በሚል ወደ ትግራይ ክልል ተመልሶ ለሌላ ጥፋት ራሱን ሲያደራጅ፤ ኢትዮጵያን ለማፍረስ ሲኦልም ቢሆን እንወርዳለን ብሎ ይሄንኑ ብሂሉን እውን ለማድረግ በመከላከያ ሰራዊት የሰሜን እዝ ላይ በውድቅት ከጀርባው ጥቃት የፈጸመ የባንዳ ስብስብ መሆኑ በተግባር አረጋግጧል፡፡

ይህ የጥፋት ቡድን ሂሳብ አወራርዳለሁ፣ ኢትዮጵያንም አፈርሳለሁ ብሎ በአፋርና አማራ ክልሎች በኩል ወረራ ፈጽሞ እስከ ሰሜን ሸዋ ሲዘልቅ መልከ ብዙ ነበር፡፡ በአንድ በኩል በደረሰበት ሁሉ ሃብት ንብረት ሲያወድም፣ ሲዘርፍና ሲያቃጥል፤ ንጹሃንን በግፍ ሲገድል፣ በጅምላ (በማይካድራ፣ ንፋስ መውጫ፣ ጋሊኮማ፣...) በጅምላ ሲጨፈጭፍ፣ አካል ሲያጎድል፣ የስነልቡና ጥቃት ሲፈጽም፣ ሴቶችን (ከህጻን እስከ አዛውንትና መነኮሳትን ሳይቀር) በቡድን ሲደፍር፣ ቤተ እምነቶችን ሲያቃጥልና ሲያወድም፣ ትምህርት ቤቶችንና ጤና ተቋማትን ጨምሮ ሲያቀጥልና ሲያወድም፣ የዓለም የምግብ ፕሮግራም መጋዘኖችን ሲዘርፍ፣... ወረራው ዓላማ የለሽና የጥፋት መሆኑን በተግባር ገልጿል፡፡

በሌላ በኩል ድል የቀናው መስሏቸው የሚፈጽመው ግፍና ጥፋት እንኳን ሳይታያቸው፣ ይልቁንም ግፍና ጥፋቱን በሚሸፍንለት መልኩ በዲፕሎማሲውም፣ በሚዲያ ፕሮፖጋንዳውም፣ በፈጠራ ዜናውም፣... ሲደግፉት የነበሩ በርካታ የውስጥም የውጭም አገር ጠሎች፣ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ነበሩ፡፡

ይህ ህልማቸው ቅዠት ሆኖ ሲቀር እና ኢትዮጵያውያን በተባበረ ክንዳቸው ወረራውን ቀልብሰው ስለ ሰላም የማይደክም እጃቸውን ዳግም ዘርግተው የሰላም ውይይት እናድርግ ማለታቸው፤ ሕልምና ምኞቱ አገር ማፍረስ፣ በጦርነት ውስጥ ተደብቆ ከትግራይ ሕዝብ ተጠያቂነት ማምለጥ ለሆነው የሕወሓት ቡድን የሚመች አልሆነም፡፡እናም ዘርፎም አስፈራርቶም ለተልዕኮው የሚሰጠውን ምንዳ ቃርሞም ራሱን በሙላት አደራጅቶ የተዘረጋውን የሰላም እጅ ገፍቶ ሦስተኛውን ዙር ወረራና ጦርነት ጀምሯል። ይህ ሃቅ እንዳለ ቢሆንም ዛሬም አሸባሪው ሕወሓት ጦርነት ከፍቶ ተከፈተብኝ፣ ወርሮ ተወረርኩኝ፣ ዘርፎ ተዘረፍኩኝ፣... የኖረ የቅጥፈት ትርክቱን ማስተጋባቱን አላቆመም፡፡

### እንደ መውጫ

የእብሪት መጨረሻው ውድቀትና ጥፋት ነው፡፡ የአሸባሪው ሕወሓት እውነትም ይሄው ነው፡፡ በእብሪት አገር ለማፍረስ ሲያል እወርዳለሁ፣ በአማራ ላይ ሂሳብ አወራርዳለሁ፣... ብሎ ለወረራ ተሰማርቶ መጨረሻው ምን እንደሆነ ታይቷል፡፡ አሁንም በመሰል እብሪት ሌላ ጦርነት ከፍቷል፤ በዚህም መጠነ ሰፊ ጥቃትና ወረራ ለመፈጸም አቅዶ የተነሳ ቢሆንም የሚፈልገውን ማግኘት እንደማይችል ከወዲሁ የተገነዘበ ይመስላል፡፡ እናም በአንድ አፍ ሁለት ምላስ ሆኖ "ከአማራ የማወራርደው ሂሳብ አለ"፣ "ከአማራ ሕዝብ የሱዳን ሕዝብ ይሻለኛል"፣ ኢትዮጵያ ስትፈርስ ማየት ሕልማችን ነው"፣... ሲል የነበረ አንደበታቸው፤ ዛሬ ላይ የአማራ ወንድም ሕዝብ፣ የኢትዮጵያ ወገኖች፣... የሚል የቅጥፈት መደለያ ቃላትን ማዥጎድጎድ ይዘዋል፤ የገፉትን የሰላም መድረክ ዳግም ለማግኘት የፈለጉ በመምሰል ሌላ የማሰቢያና የዝግጅት ጊዜ ለማግኘት ለሰላም ዝግጁ ነን ትርክት ማሰማት ይዘዋል፡፡

ይሄን መሰል እርስ በእርሱ የተምታታ መግለጫና አቤቱታ የሽብር ቡድኑ የኖረበት ባህሪው ነው፡፡ ርግብ ለቅቆ መተኮስ፣ አቅፎ መውጋት፣ ስሞ መንከስ፣ የታመነ መስሎ መክዳት፣... የኖረበት ግብሩ ሆኖ በዘመናት ውስጥ ታይቷል፡፡ አሁንም ሦስተኛውን ዙር ጦርነት በአማራ እና አፋር ክልሎች በኩል ሲጀምር ይሄንኑ የጥፋት፣ የክፋትና የክህደት ጥሙን ለማርካት እንጂ ሌላ ምንም መልካም ነገር ኖሮት አይደለም፡፡

በመሆኑም ሁሉም ኢትዮጵያዊ ይሄን ተገንዝቦ በየተሰማረበት መስክ ሁሉ ስለ ኢትዮጵያ ዘብ ሊቆም፤ ስለ ኢትዮጵያ ሊታገልና ኢትዮጵያ አሸናፊ ሆና እንድትወጣ የሚቻለውን ሁሉ ማበርከት ይኖርበታል፡፡ የትግራይ ሕዝብም ቢሆን በዚህ ቡድን ምክንያት ግማሽ ምዕተ ዓመት ልጆቹን ሲገብር፣ ሲራብና ሲጨቆን የኖረበት ጊዜ ይበቃዋልና ከዚህ በኋላ የሽብር ቡድኑን በቃህ ብሎ ከኢትዮጵያውያን እህት ወንድሞቹ ጎን በመሆን ልጆቹን ከጉያው ሳይነጥል የሚያሳድግበት፣ ነጻነቱን አግኝቶና ሰላሙን አረጋግጦ ልማቱን የሚያፋጥንበት ጊዜ እውን እንዲሆን የድርሻውን መወጣት ይኖርበታል፡፡

ኢኮኖሚ

# ግብርና

## ኩታ ገጠም የአመራረት ዘዴና የሜካናይዜሽን አጠቃቀም ለምርታማነት

**ስምስም መንግሥቱ**



ሜካናይዜሽን ለምርትና ምርታማነት እድገት፤

በሬ ጠምዶና የክረምት ወቅትን ብቻ ጠብቆ የሚከናወነውን የግብርና ሥራ ለማዘመን እንደሀገር በየጊዜው ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል፡፡ይሁን እንጂ ሙሉ ለሙሉ ከኋላቀር የአመራረት ዘዴ የመውጣቱ ተግባር ዛሬም የቤት ሥራ ሆኖ ቀጥሏል፡፡በኋላቀር የአመራረት ዘዴና ወቅትን ጠብቆ በሚከናወን የግብርና ሥራ የሚገኘው የምርት መጠን ሀገራዊ የኢኮኖሚ እድገት ላይ ለውጥ ለማምጣት ቀርቶ ዋጋው እየናረ የመጣውን የእርሻ በሬ አርሶአደሩ ለመግዛትም ሆነ የተለያዩ የግብርና መሳሪያዎችን ለማሟላት አቅሙን የሚፈትን ሆኗል፡፡የግብርና ሥራው ምርትና ምርታማነትን በሚጨምር የተለያዩ የአመራረት ዘዴዎች እንዲታገዝ፣የእርሻ ሥራውም ቴክኖሎጂ ባፈራቸው የእርሻ መሳሪያዎች እንዲከናወን እንዲሁም ክረምት ከበጋ የሰብል፣የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት እንዲከናወን እንደሀገር አቅጣጫ ተይዞ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በተለይም ባለፉት ሶስት አመታት ከክረምት እስከ በጋ ልማት እንዲከናወን በተያዘው የግብርና ሥራ የቆላ ስንዴ እና ጎን ለጎን ደግሞ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ዓለም በተለያየ የኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ በሚገኝበትና እንደሀገር የውጭ ምንዛሪ እጥረት በከፍተኛ ሁኔታ ባጋጠመበት በዚህ ወቅት የምግብ ፍጆታን ከውጭ በማስገባት ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ አቅም የለም፡፡የሚታሰብም አይደለም፡፡በዩክሬይንና በሩሲያ መካከል በተፈጠረው ጦርነት ምክንያት በስንዴና የስንዴ ውጤቶች ላይ ያጋጠመውን እጥረትና የዋጋ መናር መጥቀስ ይቻላል፡፡እነዚህ ሁሉ የሚያሳዩት በግብርናው ላይ ጠንክሮ መሥራት አማራጭ የሌለው መፍትሄ መሆኑን ነው።

ከውጭ ጠባቂ ከመሆን ለመላቀቅና በምግብ እህል እራስን ለመቻል እየተደረገ ባለው ጥረት የግብርናውን ዘርፍ ለማዘመን እየተወሰዱ ካሉ እርምጃዎች ውስጥ ኩታገጠም የአስተራረስ ዘዴ ይጠቀሳል፡፡ይህ ዘዴ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎችን የሚያስገኝ ስለመሆኑ የዘርፉ ባለሙያዎች ደጋግመው አንስተዋል፡፡አርሶአደሩ በአንድ አካባቢ ያለውን የተበጣጠሰ ማሳ ተመሳሳይ የአስተራረስ ዘዴ፣ተመሳሳይ ግብዓትና የግብርና ሜካናይዜሽን መሳሪያዎችን በመጠቀም ጥራቱን የጠበቀ ምርት ለማምረት እንደሚያስችለውና ምርታማነቱም እንዲጨምር ዕድል ይፈጥርለታል፡፡በአመራረት ሂደት ውስጥ የሚያጋጥም ብክነትንም ያስቀራል፡፡

በአጠቃላይ የሰብል ምርትን በጥራት ለማሳደግ ዋነኛው አማራጭ ነው፡፡በጥራትና በብዛት ምርት ሲኖር ደግሞ አርሶአደሩ በብዛት ገበያ በማቅረብ የተሻለ ገቢ ለማግኘት ያስችለዋል፡፡ገቢ ሲያገኝ ኑሮው ይለወጣል። ሸማቹም በተመጣጣኝ ዋጋ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ እንዲህ ያለው የገበያ ሥርአት ሲፈጠር የዋጋ መናርን በማስቀረት በሸማች በኩል የሚቀርበውን ቅሬታ ያስቀራል፡፡አርሶአደሩም የልፋቱ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

ከግብርና ሚኒስቴር ድረገጽ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው፣አርሶአደሩ በአርሶአደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ተሞክረው ውጤታማ ሆኑ ምርጥ ዘሮችን በማባዛት በኩታገጠም የአስተራረስ ዘዴ እያለማ ሲሆን፣የተለያዩ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን በማላመድ ወደ አርሶአደሩ በማስፋት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት የአርሶአደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ፡፡ሚኒስቴሩ ለአብነት ከሶስት አመት በፊት በደቡብ ክልል ሲዳማ ዞን ማልጋ ወረዳ ውስጥ የተከናወነውን ተሞክሮው በድረገጹ በማሳያነት አቅርቧል፡፡በማልጋ ወረዳ የተለያዩ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን በማላመድ ወደ አርሶአደሩ በማስፋት ኩታገጠም ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ለቤት ፍጆታ ከማዋል ባሻገር አርሶአደሩ በገበያ ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን አምርቶ በምርቱ ተጠቃሚ ለመሆን ችሏል፡፡በማልጋ ወረዳ በኩታገጠም እየለሙ ካሉ ሰብሎች አንዱና ዋነኛው የቢራ ገብስ ሲሆን፣በሁለት ኩንታል መስራች ዘር በአንድ ቀበሌ የአርሶአደር ማሰልጠኛ ማዕከል የተጀመረውን የቢራ ገብስ ዘር ብዜት በማስፋት በ13 የወረዳው ቀበሌዎች መልማት መቻሉን ነው ያስረዳው፡፡ይህ ማሳያ የሆነው የአካባቢው ተሞክሮ የኩታገጠም የአስተራረስ ዘዴ በውጭ ምንዛሪ ተገዝቶ ጥቅም ላይ እየዋለ ያለውን የቦራገብስ በሀገር ውስጥ በመተካት ወጪን ማዳን ይቻላል፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የሰብል ልማት ዳይሬክተር አቶ ሲሳይ ለማ፤በደቡብ ክልል ሲዳማ ዞን ማልጋ ወረዳ ውስጥ በኩታገጠም በቢራ ገብስ ላይ የተከናወነው ልማት በሀገር ውስጥ በመተካት አርሶአደሩን ተጠቃሚ ከማድረጉ በተጨማሪ የሀገር ወጭን በማዳንም ከፍ ያለ ፋይዳ እንደሚኖረውና በአሁኑ ጊዜም በተለያዩ አካባቢዎች እየተከናወነ ያለው የቢራ ገብስ ልማት ጥሩ በሚባል ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

አቶ ኢሳያስ በተያዘው የመኸር ግብርና በኩታገጠም የግብርና ዘዴ ስላለው እንቅስቃሴና የልማቱ ሥራ የሚገኝበትንም እንዳስረዱት፣በተወሰኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች ካልሆነ በስተቀር የእርሻ ሥራው በመጠናቀቅ ላይ ነው፡፡92 በመቶ የሚሆነው ማሳ በዘር ተሸፍኗል፡፡ለምርትዘመኑ የግብርና ሥራ የሜካናይዝሽን የግብርና ዘዴ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡በዚሁ መሠረት በአማራ፣በደቡብ፣በደቡብ ምዕራብ፣በሶማሌ ክልሎች ጥሩ አፈጻፀም ተመዝግቧል፡፡በሜካናይዜሽን የግብርና ዘዴ ለመጠቀም ከተያዘው አጠቃላይ እቅድ 91 በመቶ ማሳካት ተችሏል፡፡በሜካናይዜሽን የመጠቀም ልምዱ ከአመት አመት መሻሻል እየታየ ሲሆን፣በማህበር ተደራጅቶ ለመጠቀም ያለው ተነሳሽነት፣ባለሀብቱም በኪራይ በማቅረብ እንዲሁም መንግሥት በሚያመቻቸው የብድር አገልግሎት በመጠቀም የመግዛት አቅም መፈጠሩ፣ከቀረጥ ነጻ እንዲገባም በተፈጠረ ምቹ ሁኔታና በፖሊሲም መደገፉ፣የሜካናይዜሽን ጥቅምን የመረዳት ግንዛቤ ማደግ የተሻለ አፈፃፀም እንዲመዘገብ አስችሏል፡፡ ሜካናይዜሽንን መጠቀም ከሚያስገኘው ዘርፈብዙ ጥቅሞች ለምርታማነት የተሻለ የመሬት ዝግጅት እንዲኖር ከማስቻሉ በተጨማሪ የአረም መጠን እንዲቀንስ በማድረግ፣ጥሩ ተክል እንዲኖር ያግዛል ያሉት አቶ ሲሳይ ጥሩ ተክል ሲኖር ጥሩ ምርት እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡እንደ አቶ ሲሳይ ማብራሪያ በሜካናይዜሽን ተጠቅሞ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እየተከናወነ ያለው ተግባር አበረታች ቢሆንም የበለጠ በመስራት የበለጠ ተጠቃሚ ለመሆን ጠንክሮ መሥራት ይጠበቃል፡፡

ግብርናው በቴክኖሎጂ እንዲታገዝ ጥረቶቹ ቢኖሩም የተስተካከለ ዝናብና ምቹ የአየር ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡ለሰብሎች ስጋት የሆኑ ነገሮች አለመፈጠራቸውንም በክትትልና ድጋፍ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ከዚህ አንጻር ስላለው አቶ ሲሳይ እንደተናገሩት፤ እስካሁን ያለው የአየር ፀባዩና ዝናቡ ለግብርና ሥራው ተስማሚ ነው፡፡በኢትዮጵያ ብሄራዊ ሚቲዮሮሎጂ መረጃ መሠረት ዝናቡ በመደበኛ መሠረት እንደሚወጣ ነው የሚጠበቀው፡፡ዝናቡ በመደበኛ ሁኔታ ከወጣ የምርት ዘመኑ እቅድ የተሳካ ይሆናል፡፡ለሰብል ስጋት የሚሆኑ በሽታዎችና ተባይ በተመለከተም በክትትልና ቁጥጥር እየተሰራ ነው፡፡ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

ሌላው ለግብርናው መዘመን የሚጠቀሰው ሜካናይዜሽን ነው፡፡ሜካናይዜሽን ለኩታገጠም የግብርና ሥራ ምቹ እንደሆነም በአስተያየት ይነሳል፡፡በዚህ ላይ በግብርና ሚኒስቴር የግብርና ሜካናይዜሽን ዳይሬክተር አቶ በረከት ፎርሲዶ እንደሚከተለው ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ሜካናይዜሽን ለኩታገጠም ምቹ ነው የሚያስብለው በአንድ ጉዳይ ብቻ ነው፡፡በተቆራረጠ ማሳ ላይ ሜካናይዜሽንን ለመተግባር ከአንዱ ማሳ ወደሌላው ማሳ መሸጋገር ይጠይቃል፡፡እንዲህ ያለው እንቅስቃሴ ደግሞ የጊዜ ብክነትን ከማስከተሉ በተጨማሪ ነዳጅና ሌላ ወጭዎችን ለመቆጠብ አያስችልም፡፡በመሆኑም የመሠረተልማት ምቹነትን ይፈልጋል፡፡የግብርና ሥራው በሚከናወንባቸው አካባቢዎች ምቹ መንገድ፣የመስኖ ግድቦች፣ለማሽኑ የሚውል የነዳጅ ማደያና የማሽን ጥገና አገልግሎት ተሟልቶ ሲገኝ በመካናይዜሽን መጠቀም የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ ይቻላል፡፡በሌላ በኩልም የኩታገጠም የግብርና ዘዴ ማዳበሪያን ጨምሮ የግብርና ግብአቶችን በወቅቱ ለማድረስ ምቹ ነው፡፡

ሜካናይዜሽን መሬትን በዘመናዊ የእርሻ መሳሪያ ከማረስ ጋር ብቻ በማያያዝ ሀሳብ ለሚሰጡ ሰዎችም አቶ በረከት እንዲህ አስረድተዋል፣ሜካናይዜሽን ከመሬት ዝግጅት ጀምሮ ተጠቃሚው ጋር ለግብይት እስኪደርስ ያለውን ሂደት ያካትታል፡፡ከመሬት ምንጣሮ ጀምሮ መሬት የማረሱ፣በመሳሪያ ተጠቅሞ ውሃ ለእርሻው ማዳረስ ወይንም የመስኖ ቴክኖሎጂ መጠቀም፣ዘር መዝራት፣የመኮትኮቻ መሳሪያን ጥቅም ላይ ማዋል፣አረም ማረምና ፀረተባይ ርጭት በአውሮፕላን፣በድሮን ወይንም በጀርባ በሚታዘል መሳሪያ ማከናወን፣የማጨዱ፣የመውቃቱ፣ምርቱን ሰብስቦ ጎተራ ወይንም ማከማቻ ውስጥ ማስገባቱ የሜካናይዜሽን አካል ነው፡፡ምርቱ ከደረሰ በኃላም አሽጎና አዘጋጅቶ ለገበያ ማውጣቱ የዚሁ የመካናይዜሽን አካል ነው፡፡ይህ ሁሉ የሚከናወነው አቅምን ማዕከል ባደረገ የሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ ነው፡፡

ልክ እንደሰብል ልማቱ ሁሉ ሜካናይዜሽን ለአሳና ለእንስሳት ሀብት ልማት ጥቅም ይውላል፡፡ለእንስሳቱ የሚሆን መኖ በትራክተር ይለማል፡፡ከማልማቱ ጀምሮ ለእንስሳው መመገብ በሚያስችል መልኩ አዘጋጅቶና ከሌሎች ጠቃሚ ነገሮች ጋር አዋህዶ ምቹ በማድረግ ቴክኖሎጂው ያግዛል፡፡የወተት ማለቢያና ማቀነባበሪያ ቴክኖሎጂም የዚሁ የሜካናይዜሽን አካል ነው፡፡ ሜካናይዜሽን እጅግ ሰፊና ጥቅሙም ከፍተኛ ነው፡፡ አጠቃላይ በግብርናው ዘርፍ በኢትዮጵያ ሜካናይዜሽን እንዲያድግ እየተሰራ ይገኛል፡፡

ዘርፉ በሰለጠነ የሰው ኃይል እንዲመራ ሥራዎች በመሰራት ላይ እንደሆነም አቶ በረከት ነግረውናል፡፡እርሳቸው እንዳሉት አላጌ፣አርዳይታ ላይ ስልጠና በመስጠት ሚኒስቴሩ ሰፊ ሥራ እየሰራ ይገኛል፡፡ በሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ የሰለጠነ ባለሙያ ለማፍራት እንዲቻል ሚኒስቴሩ ሥርአተ ትምህርት ቀረጻ ላይ ይገኛል፡፡እንዲህ ያሉ ተግባራትንም እየተወጣ ያለው ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ነው። ፍላጎት ያለው በሙያው እንዲሰለጥን ምቹ ሁኔታ ከመፍጠር ጎን ለጎን አርሶአደሩ አጫጭር ስልጠናዎችን እንዲያገኝም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች አመቻችቷል፡፡

ቴክኖሎጂውን ተግባራዊ ለማደረግ ከማን ምን ይጠበቃል ለሚለው ጥያቄም አቶ በረከት በሰጡት ምላሽ፤አነስተኛ ቴክኖሎጂን የሚያመርቱ የሀገር ውስጥ አምራቾች እየተፈጠሩ ቢሆንም ቴክኖሎጂው በአብዛኛው ከውጭ ነው የሚገባው፡፡የካፖታል ወይንም የገንዘብ አቅም የሚፈልግ በመሆኑ ገዝቶ ለመጠቀም ለማይችለው አገልግሎት ሰጭዎች ተደራጅተው ስልጠና እንዲወስዱና የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ ማሽን ገዝተው በኪራይ አገልግሎት የሚሰጡበት ሁኔታ ነው የተመቻቸው፡፡በዚህ መልኩ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር አቅም ያለው አርሶአደር እየተከራየ እንዲጠቀም የተደረገ ነው፡፡መንግሥት እነዚህን ጨምሮ ማሽኖች ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ በማድረግ ከፍተኛ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል፡፡እነዚህ ሁሉ ድጋፎች አርሶአደሩ ላይ መነቃቃት እንዲፈጠር አድርገዋል፡፡አሁን ላይ በበሬ ከማረስ በትራክተር ማረስ ተመራጭ የሆነበት ጊዜ ላይ ተደርሰዋል፡፡ኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ ስምንትሺ ትራክተሮች በሥራ ላይ ይገኛሉ፡፡እንዲህ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም በመንግሥት የተያዘው ምርትና ምርታማነት የማሳደግ አቅጣጫ ተጠናክሮ ከቀጠለ ውጤታማ በመሆን ከውጭ ጠባቂነት መላቀቅ ይቻላል።

ሜካናይዜሽን ሰፋፊ የእርሻ ቦታዎች ላይ ካልሆነ በአነስተኛ እርሻ ላይ አይተገበርም የሚሉ አስተሳሰቦች እንዳሉ ያነሱት አቶ በረከት፤ ይህን ሀሳብ የሚያቀርቡ ሰዎች መስሏቸው እንጂ ቴክኖሎጂው ለቆላ፣ለሜዳማ፣ለእያንዳንዱ ሥነምህዳር ተስማሚ የሆነና በመሬት መጠኑ ልክ የሚፈለገው አይነት የሰውን ጉልበት መተካት የሚችል አቅርቦት አለ ብለዋል፡፡

ቴክኖሎጂውን ለመጠቀም አስፈላጊ ስለሚባሉ ቅድመሁኔታዎችም አቶ በረከት ሲመልሱ፤ አሁን ላይ በአነስተኛ ደረጃ በሀገር ውስጥ አምራቾች እየተፈጠሩ ቢሆንም ቴክኖሎጂው ከውጭ የሚገባ በመሆኑ ምክንያት የገንዘብ እጥረት ተፈጥሯል።ይህን ችግር ለመቅረፍም አገልግሎት ሰጪዎች እንዲደራጁና ብድርና ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡

ማህበራዊ

# አስኳላ

# ‹‹አዳሪና ልዩ ትምህርት ቤቶች የጎበዝ ተማሪዎች መፍለቂያ ናቸው››

*-ዶክተር ቶላ በሪሶ*
*የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ኃላፊ*

ጽጌረዳ ጫንያለው



**እንደ አገር የትምህርት ተደራሽነቱ የሰፋ ቢሆንም የጥራቱ ጉዳይ ግን ሁሉንም እያሳሰበ ከመጣ ሰነባብቷል፡፡ ችግሩን የተረዳው የትምህርት ሚኒስቴርም የተለያዩ ሥራዎችን ማከናወን ጀምሯል፡፡ ከእነዚህ መካከልም የትምህርት ጥራትን ሊያመጣ ይችላል የተባለለትና በብዙ መልኩ ለውጦችን እያስመዘገበ ያለው የአዳሪ ትምህርት ቤቶች ግንባታ በዋናነት የሚጠቀስ ነው፡፡ ይህንን ሥራ በስፋት ከከወኑ ክልሎች መካከል ደግሞ የኦሮሚያ ክልል አንዱ ነው፡፡ ስለሆነም ደረጃውን የጠበቀውን ትምህርት ቤት በመገንባት ውስጥ ምን አይነት ችግሮች ነበሩ፣ ውጤቶቹስ እንዴት ይታያሉና መሰል ጉዳዮችን በማንሳት የክልሉን ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ቶላ በሪሶን አነጋግረናል፡፡ እርሳቸው ያሉንንም እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡ መልካም ንባብ፡፡**

**አዲስ ዘመን፡-እንደ ክልል በአዳሪ ትምህርት ቤቶች ላይ የምታደርጉት እንቅስቃሴ ለብዙዎች ትምህርት የሚሰጥ እንደሆነ ይነገራል፡፡ ለመሆኑ ከሌሎቹ አዳሪ ትምህርትቤቶች የእናንተን ምን ይለየዋል?**

**ዶክተር ቶላ፡-** በክልሉ ያለው አዳሪ ትምህርት ቤት አንዱ የሚለይበት ምክንያት በፊት የነበሩ ትምህርት ቤቶች ችግር ምን ነበር የሚለውን በሚገባ አጥንቶ ዳግመኛ ችግሩን ላለመድገም የተሰራበት መሆኑ ነው፡፡ ተማሪዎቹ በአዳሪ ትምህርት ቤት ቆይታቸው ምን አገኙና ምን ሊጨመርበት ይገባል የሚለውንም ለይቷል፡፡ በዚህም መሰረት ቀለም ላይ ብቻ ሳይሆን ሙያም እንዲቀስሙ ተደርጎ እንዲማሩ የሚያስችል አሰራር ተዘርግቷል፡፡ በስነምግባር የተገሩና አርአያ የሚሆኑ ተማሪዎች የሚወጡበት ተቋም እንዲሆንም የምክር አገልግሎት እንዲሰጣቸው ሁሉ ጭምር ተደርጎ ተዘጋጅቷል።

**አዲስ ዘመን፡- እንደ ክልል ልዩ ትምህርትቤት የሚባልም እንደፈጠራችሁ ሰምተናል፡፡ ምን ማለት ነው፣ ምን አይነት ተማሪዎችንስ ይቀበላል?**

ዶክተር ቶላ፡- በጣም ጥሩ ጥያቄ ነው፡፡ እንደምናውቀው አዳሪ ትምህርት ቤት ማለት መኖሪያቸውም እዚያው ትምህርት ቤት ውስጥ የሆነ ነው፡፡ ልዩ ተማሪዎች የሚባሉት ግን ማደሪያቸው ቤተሰባቸው ጋር የሆነ ነገር ግን ትምህርቱ እንደ አዳሪ ተማሪዎች በልዩ ሁኔታ የሚሰጣቸው ተማሪዎች ናቸው፡፡ የሚገቡት ተማሪዎችም ልክ እንደ አዳሪ ትምህርት ቤቱ ጎበዝ የሆኑ ናቸው፡፡ ልዩነቱ አዳሪ ትምህርት ቤቱ ላይ በጣም ጎበዝ ሲሆኑ፣ ሁሉንም በአዳሪ ትምህርት ቤቱ ማካተት ስለማይቻል ያላካተቱትን በመያዝ የሚያስተምር ነው፡፡ ይህ ማለት አዳሪ ትምህርት ቤቱን የሚያግዝ ትምህርት ቤት ነው፡፡

አዳሪ ትምህርት ቤቶቹ የሚቀበሉት ተማሪ በዛ ከተባለ 280 ነው፡፡ ይህ ደግሞ ብዙ ጎበዝ ተማሪዎች በቦታ ውስንነት ምክንያት ዕድሉን እንዳያገኙ ያደርጋቸዋል፡፡ ስለሆነም ብዙ አቅም ያለው ተማሪ ለማፍራት ያግዝ ዘንድ ይህ ትምህርት ቤት ሊከፈት ችሏል፡፡ ትልቅ ውጤት እንደሚመጣበትም ይታመናል፡፡ አሁን ላይ 33 የሚሆኑ ልዩ ትምህርት ቤቶች የተገነቡ ሲሆን፣ ከ5ሺ700 በላይ ተማሪዎችን አካቶ ያስተምራል፡፡ እነዚህንም በሚቀጥለው ዓመት እጥፍ የምናደርግ ይሆናል፡፡ በዚህም 10 ሺህ የሚጠጉ ጎበዝ ተማሪዎችን የማፍራት እቅድ ተይዟል፡፡

የአዳሪ ትምህርት ቤቶችና ልዩ ትምህርት ቤቶች መስፋፋታቸው እንደችግር የሚነሳበት አጋጣሚ ይኖራል። ከአሉት አጠቃላይ ተማሪ የተወሰኑትን ብቻ መልምሎ ማስገባቱ ሌሎችን ለመጉዳት ታስቦ እንዳልሆነም ይታሰባል። ነገር ግን አስተሳሰቡ ትክክል አይደለም።ከዚህ አንጻር ግቡን ማወቅ ከምንም በላይ አስፈላጊ ነው።ዋና ግቡ ሁለት ነው፡፡ የመጀመሪያው ጎበዝ ተማሪዎች አንድ ላይ ሲሆኑ የመረዳዳትና የተሻለ የመሆን ነገርን ያመጣሉ፡፡ይህ ደግሞ ለአገር አስተዋትኦ እንዲያበረክቱ ያደርጋቸዋል፡፡

ሁለተኛው ደግሞ አዳሪ ወይም ልዩ ትምህርት ቤት ለመግባት የሚደረገው የተማሪዎች ፉክክር ሲሆን፣ በሁሉም ትምህርት ቤቶች ላይ ያለው ውጤታማ የመሆን አቅም ያሳድጋል።ይህ ፉክክር ለተማሪው ብቻ ሳይሆን ለመምህሩ ጭምር የሚሆን ነው፡፡ ምክንያቱም ሁለቱ ትምህርት ቤቶች ላይ የሚገቡ መምህራን የተመረጡና አቅም ያላቸው መሆን ይገባቸዋል፡፡ እናም መምህራን ሌሎችን በማገዝ ውስጥ ከፍ ሲሉ ተማሪዎችም የተሻለ አቅም እየፈጠሩ እንዲመጡ ያደርጋል፡፡ ይህ እድል ደግሞ ልዩና አዳሪ ትምህርት ቤቶች ላይ የሚገባ ተማሪን ቁጥር ከፍ ያደርጋል፡፡ ከዚያም አልፎ ሰራተኛ ትውልድ በሁሉም መስክ እንዲፈጠር ያግዛል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት በኦሮሚያ ክልል ምን ያህል አዳሪ ትምህርት ቤቶች አሉ፣?**

**ዶክተር ቶላ፡-** ቀደም ሲል በክልሉ የኦሮሚያ ልማት ማህበር የመሰረታቸው ሁለት አዳሪ ትምህርት ቤቶች ብቻ ነበሩ፡፡ እነርሱም ቢሆኑ በርካታ ችግሮች ነበሩባቸው። ለአብነት ከፍተኛ ውጤት የሚመጣባቸው ተቋማት አለመሆናቸው አንዱ ነው፡፡ እንደውም አንድ ተማሪ ብቻ ነበር ከፍተኛ ውጤት የሚያስመዘግበው፡፡ እናም በአዲስ መልኩ እንዲቃኙ ለማድረግ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል። ለምሳሌ፡- የመማር ማስተማር ሥርዓቱን እንዲከለስና ለዚያ የሚመጥን ተደርጎ እንዲቀረጽ ማድረጉ አንዱ ነበር። በተመሳሳይ የትምህርት ቤቶቹ ሁኔታ እጅግ አስቸጋሪ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የተሻሉ ትምህርት ቤቶች እንዲኖሩ ግንባታዎች ተደርገዋል፡፡ በተጨማሪነት ሰባት ትምህር ቤቶች ተገንብተው ለ2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመንም ዝግጁ ሆነዋል፡፡ ለአብነት ዶዶላ፣ ሐረምያ፣ ነገሌ ቦረና፣ ያቤሎ፣ በደሌ የመሳሰሉት ላይ የተጀመሩትም ያለቁትም በዚህ ዓመት ቢሆንም ለማስተማር ግን ዝግጁ ናቸው፡፡

አዳሪ ትምህርት ቤቶች ላይ የሚኖረው ውጤት እንደ አገር ጭምር አርአያነት ያለውና ለአገር ትልቅ አበርክቶን የሚያደርግ እንደሆነ ከእነዊንጌት መረዳት ይቻላል፡፡ ብዙ ሚኒስትሮች የተማሩበት ተቋም ነው፡፡ አሁንም ቢሆን ከፍተኛ ውጤቶችን የምንመለከተው ከዚያ በወጡ ተማሪዎች ነው። በዚያ ላይ ውጪ የትምህርት እድል አግኝተው እንኳን አገራቸውን ማስጠራት የሚችሉት ከእነዚህ ተቋማት ውስጥ የወጡ እንደሆነ ነጋሪ አያሻውም፡፡ እናም እንደ ኦሮሚያ የአዳሪ ትምህርት ቤቶች መስፋት ብዙ ከፍተኛ ውጤት የሚያመጡ ተማሪዎችን ማፍራት ነው ተብሎ ይታመናልና ትልቅ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

እነዚህ ትምህርት ቤቶች የቋንቋ ቤተሙከራ ሳይቀር የተሟላላቸው ናቸው፡፡ የትምህርት አቀባበላቸው ከፍ ያለ ስለሆነ የትምህርት ስርዓታቸው የተለየ እንዲሁም የመጻሐፍት ዝግጅቱ ሳይቀር ልዩ ተደርጎ ተዘጋጅቷል። በዚያ ላይ የቤተሰብን ወጪ ሙሉ ለሙሉ የሚያስቀር ነው፡፡ እንደ አገር ትምህረት ሚኒስቴር 50 የሚሆኑ አዳሪ ትምህርትቤቶችን በየክልሉ ለመስራት አስቦ ቦታዎቹ ተመርጠዋል፡፡ 13ቱ እየተሄደበቸውም ነው፡፡ ለዚህ ግብዓት መሆን መቻል ደግሞ እጅግ የሚያስደስተን ነው፡፡

የአዳሪ ትምህርት ቤት መኖር በርካታ ጠቀሜታን እንደአገር ይሰጣል፡፡ በተማሪም ላይ የውድድር ስሜት የሚፈጥር ነው፡፡ ምክንያቱም ወደዚያ የሚገቡት በክልሉ ከሁሉም ቦታዎች ላይ ተወዳድረው ጎበዝ የሆኑት ናቸው። ስለዚህም የበለጠ ጎበዝ ለመፍጠርና በእውቀት የተሻሉ ተማሪዎችን ለማፍራት ምቹ ሁኔታን ያድላል፡፡ የማንበብ ልምዳቸውም በዚያው ልክ ይጨምራልና የፈጠራ አቅማቸውን ያሳድግላቸዋል፡፡ ለዚህም ማሳያው ቀደም ብለው በሁለቱ አዳሪ ትምህርትቤቶች ብቻ ብዙ ተግባራት በመከናወናቸው በየዓመቱ የውጤት ልዩነት እየታየ መጥቷል፡፡

ከዓመት ከትትልና መሻሻል ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ውጤት የሚያመጡ ተማሪዎች ቁጥርም ወደ ስድስት እንዲያድግ ሆኗል፡፡ በቀጣዩ ዓመት ደግሞ ዘጠኝ መድረስ ችሏል። ዘንድሮ 266 ደርሷል።ሰባቶቹ ሲጨመሩ ደግሞ ምን ያህል ከፍተኛ ውጤት የሚያመጡ ተማሪዎች እንደሚኖሩ መገመት አያዳግትም፡፡ እንደውም አዳሪ ትምህርትቤቶችን የማስፋት ዘመቻ የተጀመረውም ይህንን ውጤት ከአየን በኋላም ነው፡፡ ስለዚህም አሁን በአዲስ መልክ የተገነቡትን ሰባቱን ጨምሮ ዘጠኝ አዳሪ ትምህርትቤቶች ላይ የደረስን ሲሆን፣ እያንዳንዳቸው 250 በላይ ተማሪ ይዘው ትምህርቱን የሚጀምሩ ይሆናልም፡፡

በአጠቃላይ አሁን ላይ በዘጠኙም አዳሪ ትምህርት ቤቶች ውስጥ 1ሺ522 ተማሪ የሚገኙ ሲሆን፣ በቀጣይ ዓመት ግን ይህንን እጥፍ ለማድረግ ታስቧል፡፡ በአራት ዓመት ውስጥም በእያንዳንዳቸው 1000 ሺህ ተማሪዎችን መቀበል እንደሚኖርብን ታምኖበታል፡፡ ይህ ማለት 10 ሺህ ተማሪዎችንም እንደ ክልል በአዳሪ ትምህርት ቤት ብቻ አካተን የምናስተምር ይሆናል።ነገር ግን ትምህርት ሚኒስቴር ከሚገነባው ውጪ ትምህርት ቤት የመገንባት አላማ የለንም።

**አዲስ ዘመን፡- ክረምት ከገባ ጀምሮ በርካታ የአዳሪ ትምህርት ቤቶችን እያስመረቃችሁ እንደሆነም ይታያል፡፡ ይህ የትምህርት ቤት ምረቃ ከደረጃውን የጠበቀ ትምህርት ቤት ግንባታ ፕሮጀክት ጋር ይተሳሰራል ወይስ ለብቻው የሚከናወን ተግባር ነው?**

**ዶክተር ቶላ፡-** ሁሉም የትምህርት ቤት ግንባታ ደረጃውን የጠበቀ ከሚለው ፕሮጀክት ጋር ይተሳሰራል፡፡ ደረጃ መጠበቅ ሲባል ደግሞ የትምህርት ቤቱን ጥራት ብቻ አይደለም፡፡ ቀጣይ ለሚሰራው ሥራ የሚያግዙ ነገሮችን ጭምር የሚያካትት ነው፡፡ ማለትም ኮንትራክተር መረጣ፣ የሥራ እድል ፈጠራ፣ የአማካሪዎች አቅምን ሁሉ ያማከለ ደረጃ የመለየት ጉዳይን የያዘ ነው፡፡

አዲስ ዘመን፡- ወደ አዳሪ ትምህርት ቤቶች የሚገቡ ተማሪዎች በምን መስፈርት የተመለመሉ ናቸው?

ዶክተር ቶላ፡- እንደ ሀገር ያሉ መስፈርቶችን ተይዞ ነው ምልመላው የሚደረገው፡፡ እነዚህን መስፈርቶች ያሟሉ የዕድሉ ተጠቃሚዎች ይሆናሉ። የመጀመሪያው ነገር ውጤት ነው፡፡ በእርግጥ ይህ ትክክል ነወይ ከተባለ መሻሻል እንዳለበት አስባለሁ፡፡ ምክንያቱም የሌሎች አገራት ተሞክሮ እንደሚያሳየው ተማሪዎች እነዚህ አይነት ትምህርት ቤቶችን የሚቀላቀሉት በውጤት ብቻ ሳይሆን በአላቸው ችሎታም ጭምር ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለአገራቸው የተሻለ ነገርን ከማበርከት አኳያ የማይተካ ሚና ይኖረዋል፡፡ ያልተማሩ ግን ልምድ ያላቸው ጭምር የሚያበረክቱት ነገር እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ እኛ ጋር ግን ይህንን ለማድረግ ብዙ ሥራንና በጀትን ይጠይቃል፡፡ ስለሆነም ይህንን ማድረግ አልተቻለም፡ ፡ በቀጣይ ግን የሚታሰብበት ይመስለኛል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- አዳሪ ትምህርት ቤቶችንና ልዩ የተባሉትን ትምህርት ቤቶች ስትገነቡ ያጋጠሙ ችግሮች ምን ምን ነበሩ?**

**ዶክተር ቶላ፡-** ችግሩ ሰፊ ነው፡፡ ዋናው ግን እነርሱን የሚቀበል ዩኒቨርሲቲ በአገር ደረጃ አለመገንባቱ ነው። እናም እንደ ሀገር ይህ ነገር ታሳቢ ካልተደረገ ማስተማሩ በራሱ ዋጋ አይኖረውም፡፡ በውጪ የትምህርት እድል ብቻ ይህንን ማሳካት ይቻላል ተብሎም አይታመንም፡፡ እናም በየሙያው መስከ መሥራት ይገባል፡፡ ይህም እንደሚሆን ትምህርት ሚኒስቴር አምኖበት እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡ እኛም እንደ ኦሮምያ ክልል የልማት ማህበሩ እነዚህን ሊያስገነባ የሚችልበትን አቋም ፈጥረን ተንቀሳቅሰን ነበር፡፡ ነገር ግን በብዙ መንገዶች ሳይሳካ ቀርቷል፡፡ አይሆንም ብለን አናሳብምና አሁንም እንቀጥልበታለን።

**አዲስ ዘመን፡- በአጠቃላይ የአዳሪ ትምህርት ቤቶችን ተመራጭ የሚደርጋቸው ምንድን ነው?**

**ዶክተር ቶላ፡-** ባለፈው ዓመት 52 ነጥብ ስምንት በመቶ ተማሪ ከክልሉ በማለፉ ብዙ ጫጫታ ነበር፡፡ ለዚህ ደግሞ ችግሩ እኩል መሥራት አለመቻል ነው፡፡ እንደ አገር አዳሪና ልዩ ትምህርት ቤቶች ሁልጊዜ ከፍ ያደርጉናል ተብሎ የማመኑ ምጣኔ በክልሎች ላይ ክፍተት ይታያል፡፡ እንደ ኦሮሚያ ክልል ግን ይህ ልዩ ትኩረት የተሰጠውና ወደፊትም በትልቁ የሚሰራበት ነው፡፡ እንደ ክልል ችግሮች ቢኖሩም ከችግሩ ጎን ለጎን የትምህርት ዘርፉን ማሳደግ ላይ ይሰራል፣ እየተሰራም ነው፡፡ አሁን ባለንበት ሁኔታ የምንቀጥልና እንደ ኦሮሚያ ክልል እየሰሩ መራመድ ካልተቻለ አሁንም ልዩነቱ መጉላቱ አይቀሬ ነው፡፡

የአዳሪም ሆነ የልዩ ትምህርት ቤቶች አበርክቶ በአንድ ክልል ሥራ የሚወጣም የሚታይም አይሆንም፡፡ ሁሉም ተሞክሮውን በመውሰድ በተቻለው ልክ መንቀሳቀስ ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን ብዙዎች ለመስራት የሚፈልጉ አይመስልም፡፡ ምክንያቱም በዚህ ዓመት ብቻ ሰባቱን አዳሪ ትምህርትቤቶች ስናስመርቅ ከሦስት ክልሎች በላይ መገኘት አልቻሉ፡፡ ይህ የሚያሳየው ደግሞ መንፈሳዊ ቅናት ኖሮባቸው ክልሎች በዚህ ልክ አስበው መንቀሳቀስ እንደማይፈልጉ ነው። እናም መልዕክቴ የሚሆነው ለሀገራችን እድገት ሁላችንም እየተመካከርን እንራመድ፣ እንስራ ነው።ለዚህ ደግሞ እንደ ክልል ድጋፋችንን ለሚፈልግ ሁሉ በራችን ክፍት ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡ ስለሰጡን ማብራሪያ እናመሰግናለን፡፡**

**ዶክተር ቶላ፡-** እኔም እንግዳ ስላደረጋችሁኝና የተቋማችንን ሥራ እንድገልጽ እድሉን ስለሰጣችሁኝ አመሰግናለሁ፡፡

# የ10ኛው የበጎ ሰው ሽልማት ተሸላሚዎች - ነሐሴ 29 ቀን 2014 ዓ.ም



ፎቶ፡ ሃዲስ አብርሐ

**የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ክብርት ሳህለወርቅ ዘውዴ በተገኙበት የዓመቱ 'የበጎ ሰው' የዕውቅና እና ሽልማት ዓመታዊ መርሃ ግብር ለአሥረኛ ጊዜ በተለያዩ ዘርፎች ለሃገርና ለሕዝብ ውለታ ያበረከቱ ሰዎችን ዕውቅናና ሽልማት በመስጠት ትናንት ተካሂዷል። «በጎ ሰዎችን በመሸለምና ዕውቅና በመስጠት ሌሎች በጎ ሰዎችን እናፍራ» በሚል መሪ ሃሳብ ሳለፉት ዘጠኝ ዓመታት ሲካሄድ የቆየው የዓመቱ 'በጎ ሰው' ሽልማት ዘንድሮ በቂ ጥቆማ ያልቀረበባቸውን ዘርፎች በመቀነስ በዘጠኝ ዘርፎች እንዲሁም አንድ ልዩ ተሸላሚ በማከል ነው የተካሄደው። የ10ኛው የበጎ ሰው ሽልማት ተሸላሚዎች አጭር ግለ ታሪክ (ፕሮፋይል) እንደሚከተለው ቀርቧል።**

### የመምህርነት ዘርፍ አሸናፊ
### ዶ/ር ኢንጂኒየር ውብሸት ዝቅአለ

የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በሲቪል ኢንጂነሪንግ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና በሕግ ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በተልዕኮ ትምህርት፣ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በስትራክቸራል ኢንጂነሪንግ ከእንግሊዝ፣ የሦስተኛ ዲግሪያቸውን በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ማኔጅመንት አግኝተዋል። በሥራው ዓለምም ለ34 ዓመታት በመምህርነት፣ በመንግሥትና በግል የኮንስትራክሽን ድርጅቶች ውስጥ አገልግለዋል። የመጀመሪያው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ማኔጅመንት ዶክተርም ናቸው።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከሌክቸረርነት እስከ ረዳት ፕሮፌሰርነት ሲያገለግሉ በማስተማር፣ በምርምር ከ200 በላይ የማስተርስና የፒ.ኤች.ዲ መመረቂያ ምርምሮችን በማማከር፣ በመገምገም እንደሁም በዩኒቨርሲቲዎች የሚሠሩ የማማከር አገልግሎቶችን በፕሮጀክት መሪነትና በባለሞያነት በማገልገል ላይ ይገኛሉ።

በቀድሞው የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር ውስጥ የኮንስትራክሽን ዘርፍ አቅም ግንባታ ዳይሬክተር ሆነው ለምህንድስና አቅም ግንባታ መርሃግብር ቀረጻ አገራችንን ወክለው ከጀርመን ባለሙያዎች ጋር አብረው ሠርተዋል። እንዲሁም ለሀገራችን የ30 ዓመት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ፍኖተ ካርታና 10 ዓመት ስትራቴጂክ ፕላን ዝግጅት የመሩና በስራው እንደባለሙያ የተሣተፉ ናቸው።

በተጨማሪም የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት 18 የእውቀት መስኮች የፈጠሩ በመሆናቸውና ለሀገራችን እንዲዘጋጁ በመምራትና በባለሙያነት አስተዋፅኦ በማበርከታቸው፣ ለኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ከሚታወቁት 13 የዕውቀት መስኮች በተጨማሪ ስምንት የዕውቀት መስኮች ለዓለምአቀፍ አገልግሎት ግብአት እንዲሆኑ በማድረጋቸው፣ ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አዲሱ ህንፃ ግንባታ የቴክኒክ አማካሪ ቡድን አባል በመሆን አስተዋፅኦ በማበርከታቸው ይታወቃሉ።

በማስተማር ሥራቸው ወቅት ተማሪዎችን ለመርዳትና ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽዖ በማድረግም ይታወቃሉ። ከቤተሰብ ርቀው ወደ አዲስ አበባ የሚመደቡ የተለያዩ ክልል ተማሪዎችን እንደ ወላጅ በመቅረብ በገንዘብ በመደጎም፤ ተመርቀው ሲወጡም አንዳንድ ወጪዎቻቸውን በመሸፈንና ሥራ አፈላልጎ በማስቀጠር የተማሪዎቻቸውን ሕይወት የተቃና እንዲሆን ያግዛሉ።

### የበጎ አድራጎት ዘርፍ አሸናፊ
### ወ/ሮ ክብራ ከበደ

ወ/ሮ ክብራ ከበደ የተወለደችው በትግራይ ክልል በጉሎማከዳ ወረዳ ሲሆን በደብረዘይት ግብርና ኮሌጅ ዲፕሎማዋን ከተቀበለች በኋላ በጅማ፣ ዴዶ ወረዳ ለሦስት ዓመታት፤በቀድሞው የልማት ፕሮጀክት ጥናት ባለስልጣን ለሦስት ዓመታት አገልግሎት ከሰጠች በኋላ ወደ ኖርዌይ በማቅናት በአካባቢ ጥበቃ ሃብት አስተዳደር የድህረ ምረቃ ጥናትና ትምህርት አጠናቃለች።

ከኖርዌይ እንደተመለሰች በማህበር ልምአት ትግራይ (ግብረ ሰናይ ድርጅት) መረዳጃ ማህበር ምክትል የፕሮጀክት አስተባባሪነት በራሷ ፈቃድ ከስራ በመልቀቅ ህመም እስኪሰማት ድረስ በግል አማካሪነት ሰርታለች። ህመሙ መጀመሪያ ላይ በስራ ጫና ምክንያት ውጥረት እንደሆነ ገምታለች፤ ነገር ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየባሰ ሄዶ እንቅስቃሴዋን በትክክል እንዳትቆጣጠር አድርጓታል።

ከሁለት አመታት በላይ በነርቭ ሐኪሞች ታይታለች፤ ባህላዊ ህክምናዎችን ሁሉ ሞክራለች ነገር ግን መንቀሳቀስ አለመቻሏ እየባሰ ሲሄድም ቤት ውስጥ ለመቅረት ተገደደች። በመጨረሻ በ1993 ዓ.ም ወደ አሜሪካ ሄዳ የጤና ችግሯ ከፓርኪንሰን በሽታ ጋር የተያያዘና የማይድንና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እንደሚሄድ ትገነዘባለች። በመድኃኒት እርዳታም የተወሰነ እንቅስቃሴ ማድረግ ብትችልም ቤተሰቧንና ሀገሯን የማገልገል ህልሟ መና እንደቀረ በማሰብ በህዘን ተሞልታ ነበር። ይሁን እንጂ ከጊዜ በኋላ እውነታውን በመቀበል ራሷን በማሳመን ለችግሯ እፎይታ አግኝታለች።

የፓርኪንሰን ህመምተኛ መሆኗን ካወቀች ጊዜ ጀምሮ በሽታው በኢትዮጵያ ትኩረት አለማግኘቱና ለህመምተኞች የሚሰጠው አገልግሎት ደካማ መሆኑን በመገንዘብ ሁለት ሕሙማንንና ደጋፊዎችን በማሰባሰብ "የፓርኪንሰን ሕመምተኞች ድጋፍ ድርጅት" በ2003 ዓ.ም መሰረተች።

የፓርኪንሰን ህሙማንን ለማየት ሆስፒታሎችን ስትጎበኝ ሦስት ታማሚዎችን ብቻ ነበር ማግኘት የቻለችው። ይህም አብዛኞቹ ታማሚዎች በቤት ውስጥ ተደብቀው እንደሚገኙ እንድትገነዘብ አድርጓታል። የነርቭ ሐኪሞች ቁጥርም በጣም አነስተኛ ነበር። ዛሬ የፓርኪንሰን ሕመምተኞች ድጋፍ ድርጅት በርካታ አባላትን አፍርቷል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ህሙማን መጥተው ጭንቀታቸውን የሚገልጹበት፣ መገለልን፣ ብቸኝነትንና አድልዎ የሚሸሹበት መድረክ ሆኗል። ክብራ በዱላ ታግዛ ትንቀሳቀስ ነበር። አሁን በዊልቼር ላይ ነች። ሌሎችን የሚጠቅም ስራ እየሰራች የፓርኪንሰን ህመምተኞችን ለመርዳት ትልቅ ህልም ሰንቃለች።

### የቅርስና ባሕል ዘርፍ አሸናፊ
### ሸኽ ሙሐመድ አወል ሐምዛ መዕሩፍ

ሸኽ ሙሐመድ አወል ሐምዛ በወሎ ክ/ሀገር፤ ጎሴ ተብላ በምትታወቅ መንደር በዓመተ ሂጅራ አቆጣጠር በ1370ዎቹ መወለዳቸውን በግምት ይናገራሉ። አባታቸው ሸኽ ሐምዛ መዕሩፍ ታላቅ የሃይማኖት ሰውና የአላህን መላክተኛ (የነብዩን) ውዳሴ በሚያምር ድምፅ የማንጎራጎር ተሰጥኦ ነበራቸው። የብዙ የሐበሻ ዐሊሞች የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎችን በእጃቸው ጽፈው በቤታቸው በማስቀመጥ በአሁኑ ሰዓት መረጃ የሚፈልግ ሰው በፎቶ ኮፒ እያባዛ እንዲጠቀም በማድረግ አኩሪ ሥራ ሠርተዋል።

ሸኽ ሙሐመድ አወል የመጀመሪያ እስላማዊ ዕውቀታቸውን ከወላጅ አባታቸው ከቀሰሙ በኋላ ቀሪ እስላማዊ ትምህርቶችን በጊዜው ከነበሩ ታላላቅ ዑለማዎች ገብይተዋል። ወደ ግብጽ በመሄድ ተምረዋል። በሳዑዲ ዐረቢያም የተወሰነ ጊዜ የቆዩ ሲሆን በጥቅሉ 27 ዓመታትን በውጪ አሳልፈዋል።

ሸኽ ሙሐመድ አወልም የታወቁበት አንጋፋው ሥራቸው ይህንን የታላላቆቹንና የደጋጎቹን ብርቅዬ ትውፊታዊ የመንዙማ ኦሪጅናል ሥራዎች ከዚያው ከምንጩ እንደወረደ ለትውልዳችን እጅግ በጣም ውብ፣ ማራኪና አስድማሚ በሆነ ድምፃቸው በማስተላለፍ በገጠር ሐሪማዎችና ዛውያዎች ብቻ ተገድቦ የነበረውን ሀብት ለመላው ኢትዮጵያውያን ተደራሽ እንዲሆን በማድረግ ፋና ወጊና ድልድይ በመሆን ዘመን የማይሽረው አስተዋጽዖ አበርክተዋል። በተለምዶ ዐጀሚ የሥነ-ጽሑፍ ተብሎ የሚታወቀው የሀገር በቀል ቋንቋዎችን የዐረብኛውን ፊደል ተጠቅሞ መጻፍ ሲሆን ይህን የአጻጻፍ ዘዴ በመጠቀም ብዛት ያላቸው የሀገራችን ዑለማዎች ኦሪጂናል ሥራዎቻቸውን ለትውልድ አስተላልፈዋል።

በተጨማሪም ዘርፈ-ብዙ በሆኑ ሀይማኖታዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ እሴቶች ላይ ያተኮሩ ሥራዎችን በካሴትና በሲዲ ለህዝብ ተደራሽ በማድረግ በህዝበ ሙስሊሙና ጥበብ አፍቃሪ በሆኑ ሙስሊም ባልሆነው የሕብረተሰቡ ክፍል ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ መፍጠር ችለዋል።

በዚህ ዓይነት ለግማሽ ምዕተ-ዓመታት በዘለቀ ያበረከቷቸው ሥራዎች የየዘመኑን ነባራዊ፣ ሀይማኖታዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ ሁነቶችን የዳሰሱና ማኅበረሰቡን በማስተማር ላይ ያተኮሩ እንደነበሩ ሥራዎቻቸው ይመሰክራሉ። የድምፃቸውን ውበት፣ ለዛና ጣዕማቸውን በተመለከተ አንድ ባለሙያ «... እፅዋቱና እንሰሳቱ ሁሉ የሚመሰጡ ይመስለኛል» በማለት ገልጾታል።

### በኪነጥበብ - ፊልም ዳይሬክቲንግ ዘርፍ አሸናፊ
### ዓለምፀሐይ በቀለ

ዓለምፀሐይ በቀለ የተወለደቸው በአዲስ አበባ ሲሆን ተማሪ ሳለች በትያትር ዕድገት ክበብ የሙያዋን ሀሁ ቆጥራለች። የእጩ ተዋናዮች ኮርስ ተካፍላም ፈተናውን በማለፍ አዲስ ተከፍቶ በነበረው ራስ ትያትር ስራዋን ጀመረች። በመቀጠልም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ትያትር የመማር ዕድል ስላገኘች በትያትር ጥበብ፣ በሲኒማ ፕሮዳክሽንና ጥበብ ውስጥ የተለያዩ አጫጭር ኮርሶች፣ የተለያዩ የጥበብ ስልጠናዎችን ወስዳለች። በቴአትር ጥበብም ዲፕሎማ አግኝታለች።

የቴአትር ጅማሮዋን ለራስ ቴአትር መክፈቻ "አንድ ለአንድ " በሚል ቴአትር የጀመረች ሲሆን አስከትላም "ሁለት ክፍል ግብዣ" የሚል የሙሉ ጊዜ ቴአትር ሰርታለች። ከ30 ዓመታት በላይ በቴአትር ዘርፉ ስትቆይ ከ 35 እስከ 40 የሚደርሱ ቴአትሮችን በመሪ ተዋናይነት ተውናለች።

ዓለም ፀሐይ ወደ ፊልሙ ዓለም በመግባት በአዲስ አበባ መስተዳድር ቴሌቪዥን የሚታዩ አጫጭር ድራማዎችን በድርሰትና በዳይሬክተርነት ሰርታለች። በርካታ የቴሌቪዥን ተከታታይ ድራማዎችን ዳይሬክት አድርጋለች። የጥላሁን ጉግሳን "ቤቶች" የተሰኘው ተከታታይ ሲትኮም ላይ በረ/አዘጋጅነትና በአዘጋጅነት ተሳትፋለች። በተለያዩ የቴሌቪዥን ድራማዎችና በፊልም ስራዎች ላይ በዳይሬክቲንግ፣ በረ/አዘጋጅነት፣ በማማከር፣ ስክሪፕት ላይ በመሳተፍ (በመጻፍ) ሰርታለች። ስራዎቿም ዋና ዋናዎቹ፤ ገመና ቁጥር 1 ላይ በዋና የቴሌቪዥን ድራማ ተዋናይ፣ ሁለት ክፍል ግብዣ፣ የቴዎድሮስ እንባ፣ ማክቤል፣ የሉሊት ዲፕሎማ፣ የመሸበት ይቅርታ፣ ላጤ፣ የዋርካ ስር ምኞት፣ ማለዳ፣ አሻራ፣ ቁርጥ ቀን፣ ትንታግ፣ አማች፣ የአና ማስታዎሻ፣ የመሀን ቱርፋት ይጠቀሳሉ።

በዳይሬክተርነትና በትወና የተሳተፈችባቸው ደግሞ ቁርጥ ቀን፣ መርካቶ፣ ወርቃማ ፍሬ፣ እልፍ፣ ወንድ አይገባም ናቸው። አጫጭር የቴሌቪዥን ድራማዎች ላይ በዳይሬክተርነት የሰራች ሲሆን እነርሱም፤ አፋልጉኝ፣ ቪዛው፣ ገበያ ማሞቂያ፣ የሱፍ፣ እናትና ሌሎችም ይገኛሉ። በረዳት ዳይሬክተርነት እና በዳይሬክተርነት የባህር በር፣ ባለታክሲው፣ ቅብብልና ፎዚያ ይገኙበታል።

"ፍርሃት" እና "ድንገተኛ" የተሰኙ የቴሌቪዥን ድራማዎችን ስክሪፕቶችን ጽፋለች። አራት ትምህርታዊ የሆኑ የቴሌቪዥን ድራማዎች ላይ በዳይሬክተርነት ሰርታለች። እነሱም፤ አተርፍ ባይ ፣ ፍርሃት፣ መደበቂያውና ተጓዳኞቹ ናቸው። በሴቶች ላይ ያተኮሩ አስተማሪ ድራማዎችንም በሙያዋ አበርክታለች። ከነሱም መሐል፤ ክስተት፣ የኔ ብቻ፣ የሴም ወርቅና እንቆጳ የተሰኙት የሙሉ ጊዜ የፊልም ስራዎች ይጠቀሳሉ። የፊልም ሙያ ከፍተኛ ፍቅር ላደረባቸውና ለቀረቧት ኹሉ እውቀቷን በመለገስ የምትታወቅ ከመኾኗ ባሻገር በተለይም ሴት የፊልም ዳይሬክተሮች የዳይሬክተርነትን ሙያ ራሳቸው ፕሮዲዩስ ማድረግ ሳይጠበቅባቸው በሙያቸው ብቻ የሚጠሩ እንዲሆኑ ራሷ ግንባር ቀደም አርዓያ በመኾን ከፊት መቅደሟን የሙያ አጋሮቿ ይመሰክሩላታል።

### የመንግሥታዊ የሥራ ሐላፊነት ዘርፍ አሸናፊ
### አቶ ግርማ ዋቄ

አቶ ግርማ ወቄ የተወለዱት ሰኔ 16 ቀን 1935 ዓመተ ምህረት ሲሆን በወጣትነታቸው ወደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ በመግባት እዚያው ተምረውና አድገው በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ለ34 ዓመታት አገልግለዋል። በመካከል ወደ መካከለኛው ምስራቅ ሄደው የገልፍ አየር መንገድንና ዲኤ ኤች ኤል ኩባንያን በሐላፊነት አገልግለዋል። እ.ኤ.አ በ2004 ዓ.ም የኢትዮጵያ መንግስት ያቀረበላቸውን ጥሪ ተቀበለው የኢትዮጵያ አየር መንገድን ለሰባት አመታት

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

በዋና ሥራ አስፈጻሚነት መርተዋል። ከኢትዮጵያ አየር መንገድ በጡረታ ከተሰናበቱ በኋላ የሩዋንዳ አየር መንገድ የቦርድ ሊቀመንበር፤ የሩዋንዳ የትራንስፖርት ሚኒስትር የአቪየሺን ጉዳዮች አማካሪ በመሆን አገልግለዋል። በአጠቃላይ በአቪዬሽን ኢንደስትሪ ውስጥ የ50 ዓመታት ልምድ አካብተዋል። በአፍሪካ የአቪዬሽን መድረኮችና በባለሙያዎቹ የአፍሪካ አቪዬሽን አባት በመባል ይጠራሉ። በስማቸውም የሽልማት ድርጅት ተቋቁሟል።

በዚህ የሥራ ጊዜያቸው ውስጥ አየር መንገዱን በመወከል በጋና የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሃላፊ፤ በታንዛኒያ የአየር መንገዱ የሀገሩ ወኪልና ሃላፊ ከዚያም በምእራብ አውሮፓ የጀርመን፣ የፈረንሳይ፣ የኔዘርላንድስ፣ የሉክዘምበርግ፣ የቤልጂየም እንዲሁም የሩሲያ ሀገራትን የሽያጭ ስራ መርተዋል። በሥራቸው ታታሪና ለመማርም ፈጣን አእምሮ ያላቸው አቶ ግርማ ዋቄ የትምህርት እድል አግኝተው በውጭ ሀገራት የተለያዩ ኮርሶችን ተካፍለው በጥሩ ውጤት አጠናቀው ተመልሰዋል። የአየር መንገዱን የካርጎ ክፍል በዘመናዊ መንገድ መስርተው አሁን ላለበት ደረጃ መሰረት ጥለዋል።

አቶ ግርማ ዋቄ እኤአ በ2004 ወደ ሀገር ተመልሰው ሲገቡ ባዘጋጁት የአምስት ዓመት እቅድ አየር መንገዱ በዓመት ያስተናግድ የነበረውን የመንገደኞች ቁጥር ከ1.2 ሚሊዮን ወደ 3.2 ሚሊዮን፤ ዓመታዊ ገቢውን ከ390 ሚሊዮን ዶላር ወደ 1.2 ቢሊዮን ዶላር፤ ትርፉን ከ31 ሚሊዮን ዶላር ወደ 101 ሚሊዮን ዶላር፤ ከ47 መዳረሻዎች ወደ 55፤ የአውሮፕላኖችን ቁጥር ከ22 ወደ 33፤ የሠራተኞችን ብዛት ከ4600 ወደ 6200 አድርሰዋል። በሠራተኛውና በአስተዳደሩ መካከል የነበረውን ግንኙነት አሻሽለዋል። በአሁኑ ወቅትም የአየር መንገዱ የቦርድ ሰብሳቢ ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ።

### የንግድና ስራ ፈጠራ ዘርፍ አሸናፊ
### አቶ ሰዒድ መሀመድብርሃን

አቶ ሰዒድ መሀመድብርሃን በትግራይ ክልል ሽሬ እንዳሥላሴ አውራጃ በአዲደእሮ በሚባል አካባቢ በ1954 ዓ.ም በግብርና ከሚተዳደሩት እናትና አባታቸው ሁለተኛና የመጨረሻ ልጅ ሆነው ተወለዱ። መደበኛ ትምህርታቸውን ለመከታተል የ45 ደቂቃ መንገድ በእግራቸው በመጓዝ ይማሩ የነበረ ሲሆን በወቅቱ በነበረው ጦርነት ሳቢያ ትምህርታቸውን መቀጠል አልቻሉም። አባታቸው ለወንድማቸው በከፈቱት ሱቅ ጥብቆ መቀምቀም፣ ገምባሌና ቁምጣ መስፋት ጀመሩ።

ጥቂት ጊዜ ያኔ በእጃቸው የነበረችውን 200 ብር ይዘው ወደ ኩኻ ከተማ አቀኑና የልብስ ስፌት መኪና ተከራይተው ሥራ ጀመሩ። በአብዛኛው የወታደሮች ዩኒፎርም በማጥበብና አንዳንድ ጥቃቅን ስራዎችን በመስራት ለ11 ወራት ያህል ሠርተው ብርቱ ዓላማ ነበራቸውና ወጪያቸውን ችለው ለባለስፌት መኪናውም የሚገባቸውን ከፍለው 3 ሺህ ብር ማጠራቀም ቻሉ። ያቺን ይዘው የተሻለ ነገር ለመስራት ወደ መቀሌ ሄደው ለዛሬው የልብስ ስፌት ኢንዱስትሪያቸው መሰረት ጣሉ።

የ19 ዓመቱ ሰዒድ በአንዲት ማሽናቸው በአብዛኛው የወታደሮችን አለፍ ሲልም የአካባቢውን ነዋሪ ልብስ እየጠቀሙ ገቢ ማግኘት ጀመሩ፣ ሳይሰለቹ ሰሩ። ጥሪት ቋጠሩ። ትህትናቸውና ለደንበኞቻቸው የሚሰጡት አገልግሎት ብዙዎችን ወደ እኚህ ልብስ ሰፊ ይስባቸዋል። የልብስ ስፌት ቤታቸውን ከአንድ ወደ ሁለት አሳደጉ። ናሽናል ልብስ ስፌትና አሁንም ድረስ አጎታቸው ስያሜውን ወስደው የሚሰሩበት መርካቶ ልብስ ስፌት ቤት የወጣቱ ሰዒድ መንትያ ሱቆች ሆኑ።

በ1981 ዓ.ም አራት የልብስ መስፊያ መኪናቸውንና 21ሺህ ብር ይዘው ወደ አዲስ አበባ የመጡት አቶ ሰዒድ መጀመሪያ መርካቶ ከዚያም በ1990 ዓ.ም ገርጂ በሚገኘው ሬዲሜድ ማስ ፕሮዳክሽን እየሰሩ አምባሳደር ልብስ ስፌትን አሁን የደረሰበት ደረጃ አደረሱት። በከፍተኛ የስራ ትጋትና ዲሲፕሊን በአሁኑ ሰዓት በሺዎች የሚቆጠሩ ሰራተኞች ያሉትና ከፍተኛ ሀብት የሚያንቀሳቅሱ ድርጅቶችን እውን አድርገዋል። አምባሳደር ልብስ ስፌት፤ አምባሳደር ሆቴል፤ አምባሳደር ሪል እስቴትና ሞል አቶ ሰዒድ የረጅም ዘመን የስራ ትጋት ውጤቶች ናቸው።

በበጎ አድራጎት ሥራም በሽሬ እንደሥላሴ አካባቢ ትምህርት ቤት፣ የወጣቶች መዝናኛ ማዕከል እንዲሁም የሀይማኖት ተቋማትን አስገንብተዋል።

### በሚዲያና ጋዜጠኛነት ዘርፍ አሸናፊ
### አቶ ሰለሞን ገብረሥላሴ

አቶ ሰለሞን ገብረሥላሴ በ1934 ዓ.ም ተወልደው ያደጉት አዲስ አበባ ውስጥ ነው። በ11 ዓመታቸው በአጋጠማቸው አደጋ በአካላቸው ላይ ጉዳት የደረሰባቸው ሲሆን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በአሰላ ስዊዲሽ ሚሽን ትምህርት ቤት፤ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በሐረር ስዊዲሽ ሚሽን ትምህርት ቤት ተከታትለዋል። በመቀጠል በ1949 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ በመመለስ በኮከበ ጽብሃ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ በመምህርነት ሙያ በከፍተኛ ውጤት በመመረቅ ከቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ እጅ የምስክር ወረቀታቸውን ተቀብለዋል።

አቶ ሰለሞን ገብረሥላሴ ከ1950 እስከ 1956 በአሰላ ራስ ዳርጌ በ1ኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፤ ከ1957 እስከ 1959 በአዲስ አበባ በአርበኞች 1ኛ እና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በአስተማሪነት አገልግለዋል። ከ1959 ጀምሮ በጋዜጠኝነት ሙያ በየምስራች ድምጽ ብስራተ ወንጌል ዓለም አቀፍ ሬድዮ ጣቢያ በመቀጠር፤ በልጆች ክፍለ ጊዜ፣ ሰዎችና ሥራቸው፣ ህብረተሰባችንን እንይ እና ባህላዊ ሙዚቃዎች በተሰኙ የሬዲዮ ፕሮግራሞች ከአዘጋጅነት እስከ ከፍተኛ ዋና አዘጋጅነት ሠርተዋል።

ከዚያም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ሬዲዮ የአማርኛ ፕሮግራም ተጠባባቂ ኃላፊና በዓለም አቀፍ የአማርኛ ፕሮግራም ዋና ኃላፊ በመሆን እስከ 1986 በጡረታ እስኪገለሉ ድረስ አገልግለዋል። በጡረታ ከተገለሉም በኋላ በ1987 እንደገና ወደሙያው በመመለስ እስከ 2006 ዓ/ም ድረስ በየምስራች ድምጽ ተዘጋጅቶ በደቡብ አፍሪካ ትራንስ ወርልድ ሬዲዮ የሚተላለፉ ተመሳሳይ ፕሮግራሞችን በዋና አዘጋጅነት አገልግለዋል።

በ1967 ዓ.ም የምስራች ድምጽን ደርግ ሲወርሰውና አንዳንድ ባለሙያዎች ከስራ ሲሰናበቱ አቶ ሰለሞን ግን እንዲቀጥሉ ተደርጎ ነበር። በዚህ ጊዜ ውስጥ አቶ ሰለሞን ለብዙ ዓመታት የልጆች ፕሮግራም አዘጋጅ ሆነው ለበርካታዎች መታነጽ ምክንያት ሆነዋል። ከ40 ዓመታት በላይ ከልጆች ዓለምን ሲያዘጋጁ ለትውልድ አንድ ትልቅ መሰረት አስቀምጥዋል። ከሬድዮ አድማጮች ባሻገር ከእርሳቸው ጋር ሆነው ፕሮግራሙን የሚሰሩት ልጆችንም ቀርፀዋል።

በሙያቸው፣ በልጆች ክፍለ ጊዜ ህጻናት ጥሩ የስነምግባር መሰረት ይዘው እንዲያድጉ ጥረት በማድረጋቸው በተደጋጋሚ ከወላጆች ምስጋና ይቀርብላቸው ነበር። በጊዜው የህጻናት ፕሮግራም ይሰሩ ከነበሩት መካከል አሁን በሳል ጋዜጠኞች የሆኑትን እንደነ አስካለ ተስፋዬ (ኢትዮጵያ ቴሌቪዥን) ብርሃኑ ገ/ማሪያም (የሬዲዮ ጋዜጠኛ) የመሳሰሉትን ወደ ጋዜጠኝነት ሙያ፤ እንደነ እመቤት ወ/ገብርኤል፤ ተክሌ ደስታ የመሳሰሉትን ደግሞ ወደ አርቲስትነት ሙያ እንዲመጡ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አበርክተዋል። በማህበራዊ ነክ ፕሮግራሞች፤ በህይወት ተምሳሌትነታቸው፤ በትምህርታቸውና በሙያቸው ምሳሌ የሚሆኑትን ታዋቂ ሰዎች በማነጋገር ለማህበረሰቡ ምሳሌ እንዲሆኑ ጥረት አድርገዋል።

### የሳይንስ ዘርፍ አሸናፊዎች
### ኤመሬትስ ፕሮፌሰር ረዳ ተክለሃይማኖት

የሕክምና ትምህርታቸውን በእስራኤል በሚገኘው ሂብሩ ዩኒቨርሲቲ በ1960 ዓ.ም አጠናቀቁ። ለሁለት ዓመት በኡጋንዳ በሐኪምነት አገልግለው ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱ በኋላ በወንጂ ስኳር ፋብሪካ ተቀጥረው በሕክምና እንዲሁም በሜዲካል ዳይሬክተርነት ለአምስት ዓመታት አገልግለዋል። በወንጂ በቆዩበት ጊዜ ፍሎራይድ በሚያስከትለው የጤና ችግሮችና በቢልሃርዝያ ላይ ሰፊ ጥናት በማድረግ ብዙ የጥናት ወረቀቶችን ለኅትመት አብቅተዋል።

በጥቁር አንበሳ ለሁለት ዓመት ካገለገሉ በኋላ በካናዳ ከሚገኘው McGill university Hospital በneurology ስፔሻላይዝ አድርገው ወደ ኢትዮጵያ በመመለስ የመጀመሪያው neurologist ሆነዋል። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኒውሮሎጂ መምህር ሆነውም ብዙ የሕክምና ባለሞያዎችን አፍርተዋል። በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል በመምህርነትና በጥናቶቻቸው የፕሮፌሰር ማዕረግን አግኝተዋል።

ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በጡረታ ከተገለሉ በኋላ ግራር ቤት ተሐድሶ ማህበርን በ1997 በቡታጅራ አቋቋሙ። ግራር ቤት በመጀመሪያ የኒውሮሎጂና የሚጥል በሽታ ለማከም እንዲሁም የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው የተሐድሶ ማዕከል ሆኖ ቢቋቋምም በጊዜው በተሠራው ጥናት የዓይን ችግር ያለባቸው ታካሚዎች ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ ፕሮፌሰር ረዳ የዓይን፣ የጆሮና የመስማት ችግር ሕክምናን እንዲሁም ለአካል ጉዳተኞች የሞያ ሥልጠና በመጨመር ወደ ሕክምናና ተሐድሶ ማዕከል እንዲያድግ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርገዋል።

የዓይን ሕክምናውን ወደ ኦሮሚያ ክልል በማስፋፋት በባቱ/ዝዋይ ሁለተኛ የዓይን ህክምና ማዕከል ከመነጽር ማምረቻ ጋር አቋቁመዋል። ባለፉት 25 ዓመታት በሁለቱ የሕክምና ተቋማትና በመስክ አገልግሎት፣ ከሁለት ሚሊዮን ሕዝብ በላይ የዓይን ታካሚዎች ተጠቃሚ ለማድረግ ተችሏል። ከ20,000 በላይ የሞራ ግርዶሽ ታካሚዎችን የዓይን የቀዶ ጥገና ሕክምና እንዲሁም ከ110,000 በላይ በመነጽር የሚስተካከል የዓይን ችግር ላለባቸው የመነጽር እደላ ተደርጓል። አካል ጉዳተኞችን በማደራጀት ከ2000 በላይ ለሆኑ የሞያ ሥልጠና እንዲሁም መነሻ ካፒታል በማመቻቸት የራሳቸው ገቢ እንዲኖራቸው ማድረግ ተችሏል።

ፕሮፌሰር ረዳ በዓለም የጤና ድርጅት በአፍሪካ ሪጅናል ኮሚሽን በፖሊዮ ማጥፋት ዘመቻ ውስጥ የአፍሪካና የምሥራቅ ሜዲትራንያን ውስጥ ም/ሊቀመንበር ሆነው ፖሊዮን ለማጥፋት ለአምስት ዓመታት አገልግለዋል።

### ለኢትዮጵያ በጎ ያደረጉ ትውልደ
### ኢትዮጵያውያን ዘርፍ
### ዶ/ር ርብቃ ጌታቸው

ዶ/ር ርብቃ ጌታቸው ገና በ11 ዓመት እድሜዋ ከቤተሰቧ ጋር በስደት ወደ አሜሪካ ተጉዛ ኑሮዋና ትምህርቷን እንዲሁም ሥራዋን በዚያው አድርጋለች። የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ካጠናቀቀች በኋላ ከዊልያምስ ኮሌጅ በሕግ የመጀመሪያ ዲግሪዋን እንዲሁም ከእውቁ የሐርቫርድ የህግ ትምህርት ቤት የዶክትሬት ዲግሪዋን አግኝታለች። በዚሁ ዩኒቨርሲቲ የሚታተመው የሕግ ጆርናል አዘጋጅ እስከመሆን የደረሰ አካዳሚያዊ አገልግሎት ሰጥታለች።

ዶ/ር ርብቃ በአሜሪካ የሕግ አማካሪና ጠበቃ፣ የፋይናንስ ጉዳዮች አማካሪና የበርካታ በጎ አድራጎት ተቋማት አማካሪና የቦርድ አባል በመሆኑ ሰርታለች። ከ25 ዓመታት የውጭ ሀገር ኑሮ በኋላ ወደ ትውልድ ሀገሯ በመመለስ በትምህርት ዘርፍ ለኢትዮጵያውያን ወጣቶች አይተኬ የበጎ አድራጎት ተግባር በመከወን ላይ ትገኛለች።

የኢትዮጵያን ልጆች በትምህርት ለማገዝ በማሰብ እ.ኤ.አ. በ2016 ዓ.ም Ethiopian Education Initiatives (EEI) የተሰኘ ምግባረ ሰናይ ድርጅት አቋቋመች። ከቤተሰቦቿና ከወዳጆቿ ጋር በመሆን የዚህ ድርጅት ቀዳሚ ውጤት የሆነውን "ኃይሌ ማናስ አካዳሚ"ን በደብረ ብርሃን ከተማ አቅራቢያ ከሃያ ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጪ በማድረግ ግንባታውን በአምስት ዓመታት በማጠናቀቅ በ2013 ዓ.ም የመጀመሪያዎቹን 35 ተማሪዎች በመቀበል ሥራ አስጀምራለች።

በስምንት ሄክታር መሬት ላይ ያረፈው ኃይሌ ማናስ አካዳሚ የተማሪዎችና የመምህራን መኖሪያ፣ የተማሪዎች መማሪያ ክፍሎች፣ ጂምናዝየም፣ የአትክልት ስፍራ፣ ቤትመጻሕፍትና ቤተ ሙከራዎች የተሟሉለት በዓለም ላይ ያሉ ምርጥ የትምህርት ማዕከላት ሊያሟሉት የሚገባውን ሁሉም መመዘኛ አሟልቶ የያዘ ነው። በየዓመቱም 100 በትምህርታቸው ከፍተኛ ውጤት ያላቸውን ኢትዮጵያውያን ተማሪዎችን ተቀብሎ ከዘጠነኛ ክፍል ጀምሮ ያስተምራል።

አካዳሚው ራሱን ለመደጎም ከፍለው መማር ለሚችሉ ተማሪዎች ትምህርት በክፍያ ይሰጣል። ከፍለው መማር የማይችሉት ደግሞ በርብቃ ኃይሌ አስተባባሪነት በሚሰበሰብ ገንዘብ ትምህርታቸውን በነጻ ይከታተላሉ። ትምህርት ቤቱ በ2013 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ የተቀበላቸውን 35 ተማሪዎች በዚሁ ማዕቀፍ ሁሉም የነጻ ትምህርት እድል ተጠቃሚዎች ናቸው። መክፈል ከሚችሉ ተማሪዎች የሚገኘው ገቢም ቢሆን ትምህርት ቤቱ አገልግሎቱን እንዲቀጥል እንጂ ለትርፍ የሚሰበሰብ ገቢ አይደለም።

### የ10ኛው የበጎ ሰው ሽልማት ልዩ ተሸላሚ

በባህሪዋ ፈጣን፤ ንቁና ቀልጣፋ እንዲሁም በጣም ደፋር፤ ከተነካችም ለድብድብም ቢሆን ወደኋላ እንደማትል ይነገርላታል። የተሰጣትን ሐላፊነት ለመፈጸም ወደ ኋላ የማትል፣ ላመነችበት ነገር ታጥቃ የምትነሳ፤ ከቢሮ እስከ የዓለም መድረክ ማንነቷን ያሳየች፤ የቁርጠኝነት ተምሳሌት ናት።

ደግሞም እናት ናት፤ የልጆቿ ብቻ ሳይሆን የብዙዎች። እቅፍ ድግፍ አድርጋ ለሀገራዊ ድል የምታበቃ። ህግ ሲጣስ፣ ሰው ሲበደል፣ ስልጣን ያለቦታው ሲውል አትወድም። በዚህ ጊዜ ህዝብ የሚያውቀው ሳቋ ይጠፋና እልህ ይተናነቃታል። ለእውነትና ላመነችበት ነገር መቆምን አሳይታለች።

ስሟ በዓለም ከገነነው የትውልድ መንደሯ ከብት ከማገድ፣ ከትምህርትና ከፈረስ ግልቢያ ተነስታ ገና በ18 ዓመቷ በኖርዌይ በስድስት ኪሎ ሜትር የዓለም ሀገር አቋራጭ ውድድር ተሳትፋ 23ኛ በመውጣት ጉዞዋን ጀመረች። በዚያው ዓመት በተመሳሳይ የስድስት ኪሎ ሜትር ውድድር የወርቅ ሜዳሊያ በማግኘት አሸናፊ ሆነች። በ1980ዎቹ አለም አቀፍ ዕውቅናና ዝና እያገኘች ሄዳ ካገኘቻቸው ድሎች መካከል በቡልጋሪያ በ10,000 ሜትር ሩጫ ላይ ሪከርድ ሰብራ በአሸናፊነት ያስመዘገበችውና ካይሮ ላይም በተመሳሳይ ርቀት ያሸነፈቻቸው ውድድሮች ይጠቀሳሉ።

ይህችን ድንቅ ኢትዮጵያዊት እኛም ዓለምም በደንብ ያወቅናት በባርሴሎና በተካሄደው ኦሎምፒክ በ10,000 ሜትር ውድድር ላይ በታሪክ ውስጥ የመጀመሪያዋ አፍሪካዊት ሴት የወርቅ ሜዳልያ አሸናፊ በመሆን ለሀገሯና ለአፍሪካ ፈር ቀዳጅ የሆነውን ውጤት ባስመዘገበችበት እለት ነበር። ይህ ብቻ አይደለም። የወርቅ ሜዳሊያዋን አጥልቃ ብሔራዊ መዝሙራችንን በድል ስታዘምር ያፈሰሰችው እንባ ትርጉሙ ስለሚገባን በህዝብ ልብ ውስጥ በክብር ተቀምጣለች።

በተከታዮቹ ዓመታት በእንግሊዝ - ዱርሀም በተደረገው የዓለም አገር አቋራጭ ውድድር የወርቅና የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና በ10,000 ሜትር በፌማንዳ ሪቤሮ ተቀድማ የብር ሜዳልያ ባለቤት ሆናለች። ለሁለተኛ ጊዜም በሲድኒ ኦሊምፒክ በ10,000 ሜትር ለሀገሯ የወርቅ ሜዳልያ አስገኝታለች። ክስተቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ በአለም ይህንን ያደረገች ብቸኛዋ ሴት እንድትባል አድርጓል። በዚህ ሳታበቃ በዓለም አገር አቋራጭ ሻምፒዮና ውድድር ለ3ኛ ጊዜ፤ በ1993 ዓ.ም በኤድሜንተን በተደረገው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና በ10,000 ሜትር የወርቅ ሜዳልያ ባለቤት ሆናለች።

ወደ ማራቶን በመሸጋገር በለንደንና ቶኪዮ ማራቶን ውድድሮች በአሸናፊነት ተሸላሚ ሆናለች። በ1997 ዓ.ም በተካሄደው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ውድድር 4ኛ በመሆን የራሷን ምርጥ ሰዓት ማስመዝገብ ችላለች። በፖርቹጋል ሊዝበን ግማሽ ማራቶን ለሁለት ጊዜ አሸንፋለች። ከሁሉም በላይ ኒውዮርክ ከተማ ላይ በተደረገ የማራቶን ውድድር ታዋቂዎቹን ፓውላ ራድክሊፍን፤ ሊዱሚላ ፔትሮቫን እና ሳሊና ኮስጊን በማስከተል ታሪክ ሠርታለች። ከዚህ በኋላም በአቴንስ ኦሊምፒክ በ10,000 ሜትር በ3ኛነት የነሐስ ሜዳልያ ባለቤት ሆና አጠናቃለች። የመጨረሻ የማራቶን ውድድሯን በ2003 ዓ.ም ጃፓን - ዮኮሃማ ውስጥ አድርጋለች። ይህች ጀግና በሩጫ ታሪኳ 35 ወርቅ፣ 12 ብር እና 15 የነሃስ ሜዳሊያዎችን ለህዝቧና ለሀገሯ አበርክታለች።

ከአትሌቲክሱ በተጨማሪም በልዩ ልዩ የኢንቨስትመንት ሥራዎች ላይ ከመሰማራቷም በላይ በበጎ አድራጎት ተግባሯ በሰፊው ትታወቃለች። ከዚህም ባሻገር በአሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንን በፕሬዚዳንትነት፣ የምሥራቅ አፍሪካ አትሌቲክስ ሪጅንን በም/ፕሬዚዳንትነትና በአፍሪ አትሌቲክስ ኮንግረስ ደግሞ ኢትዮጵያን ወክላ የካውንስሉ አባል በመሆን በአትሌቲክሱ ዘርፍ አገሯንና አፍሪካን በማገልገል የበኩሏን ሚና እያበረከተች ትገኛለች።

ከሁሉም በላይ እሷ የጽናት ተምሳሌት ነች። ከልጅነቷ ጀምሮ የነበረው የደፋርነት፣ የአይበገሬነትና የጽናት ባህሪዋ እስካሁን ዘልቆ የሀገር አርማና አርአያ ሆናለች። ሀገራችን ጦርነት ላይ በነበረችበት ወቅት አትሌቶች ጽናት ኖሯቸው ራሳቸውን እንዲያበቁና በዓለም የውድድር መድረክ ሰንደቅ ዓላማችንን በክብር እንዲያውለበልቡ ግንባር ቀደሙን የመሪነት ሚና ተጫውታለች።

ስፖርት የሰላም፣ የፍቅር፣ የአንድነትና ከሁሉም በላይ ደግሞ የሀገር መገለጫ እንደመሆኑ የፖለቲካ አቋምና በወቅቱ የነበረው ግጭት ሳይበግራት በዓለም አትሌቲክስ ውድድር በ5000 ሜትር ውድድር ሪከርድ በመስበር ጭምር ያሸነፈችውን አትሌት ለተሰንበት ግደይ መቀሌ ድረስ ይዛ በመሄድ ፍቅርንና ኢትዮጵያዊ አንድነትን ያሳየች ጀግና ናት።

በከፍተኛ ትጋትና ቁርጠኝነት ረጅም ጊዜዋን ከአትሌቶች ጋር በማሳለፍ፣ አብራቸው በመዋልና በማምሸት፣ በግል አቅርባ በማነጋገርና በመምከር፣ ቤተሰባዊ ስሜት እንዲሰማቸው በማድረግ፣ ችግር ሲያጋጥማቸው ከማንም በፊት ቀድማ በመድረስ፣ ያለምንም መሰልቸት ውጤታማ የሀገር ቡድን እንዲፈጠር የተጋች የአትሌቶች እናት ነች። ለዚህም በቅርቡ በተለያዩ የዓለም የአትሌቲክስ ውድድሮች የተገኙት ውጤቶች ማስረጃዎች ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪ ባገኘችው መድረክ ላይ ሁሉ ሀገራችን ሰላም እንድትሆንና የወንድማማቾች ግጭትና እልቂት እንዲቆም እንደ እናትም፤ እንደ ሐላፊም፣ እንደ ዜግነቷም ቀጥተኛ በሆነ ንግግር ጥልቅ መልዕክት የምታስተላልፍ ተምሳሌት ናት። ይህቺ የሀገር ፈርጥ፤ በሁለገብ አስተዋጽኦዋና አርአያነቷ የ10ኛው የበጎ ሰው ሽልማት ልዩ ተሸላሚ እንድትሆን በበጎ ሰው ሽልማት ድርጅት ቦርድ ተወስኗል። የዚህ ዓመት የበጎ ሰው ሽልማት ልዩ ተሸላሚ አትሌት ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ።

# ዓለም አቀፍ




## ስድስት ሩሲያውያን ተራራ ወጪዎች በእሳተ ገሞራ ላይ ወድቀው ሞቱ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በምሥራቅ ሩሲያ በምትገኘው ምሥራቃዊ ካምቻትካ ግዛት በእሳተ ገሞራ የተፈጠረ ተራራ ለመውጣት የሞከሩ ቢያንስ ስድስት ተራራ ወጪዎች ሕይወታቸው ማለፉን መገናኛ ብዙኃን ዘግበዋል።

በመጥፎ የአየር ጠባይ ምክንያት የነፍስ አድን ሠራተኞች ስድስቱን ተራራ ወጪዎች ማዳን አልቻልንም ብለዋል።

ሁለቱ ሰዎች ከባህር ወለል በላይ በሦስት ሺህ 300 ሜትር ከፍታ ላይ የነበሩ ሲሆን ሌሎቹ አራት ደግሞ በአራት ሺህ ሜትር ከፍታ ላይ እንደደነበሩ ይታመናል። ሁሉም ግለሰቦች የሩሲያ ዜጎች ናቸው ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

ሁለት አስጎብኚዎችን ጨምሮ አስራ ሁለት ግለሰቦችን ያካተተው ቡድን ማክሰኞ ዕለት ነበር ወደ አራት ሺህ 754 ሜትር ከፍታ ተራራ ለመውጣት ጉዞ የጀመረው።

ከአራት ቀናት በኋላ ከአራት ሺህ ሜትር ከፍታ የወደቁት አራት ተራራ ወጪዎች ወዲያውኑ ሕይወታቸው አልፏል ተብሎ ይታመናል። ሌሎች ሁለት ተራራ ወጪዎችም ብዙም ሳይቆዩ ሞተዋል።

ከአስጎብኚዎቹ አንዱ እግሩን እንደተሰበረ የተነገረ ሲሆን የቀሩት ሰዎች ሁኔታ ግን በውል አልታወቀም።

ክልዩቼቭስካያ ሶፕካ በዩኔስኮ የዓለም ቅርስነት የተመዘገበው የካምቻትካ የተፈጥሮ እሳተ ገሞራዎች አካል ነው። እሳተ ገሞራው በአንዳንድ የአገሬው ተወላጆች ዘንድ እንደ ቅዱስ ስፍራ ይቆጠራል።

## የዩኬ ፖሊስ ከሰባ አመት በፊት 'በስህተት ገድየዋለሁ' ላለው ሶማሊያዊ ቤተሰብ ይቅርታ ጠየቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በዩናይትድ ኪንግደም በግድያ ወንጀል ተከሶ በስህተት የተፈረደበት ሶማሊያዊ አባት ከተገደለ ከሰባ አመት በኋላ ፖሊስ ይቅርታ ጠየቀ። ግለሰቡ በማይሆን ክስ ምክንያት የፍትህ እጦት ሰለባ መሆኑን ነው የተጠቆመው።

የዩኬና ሶማሊያ ጥምር ዜግነት የነበረው ማህሙድ ማታን የተባለው ግለሰብ ካርዲፍ በሚገኝ የሱቅ ባለቤት የነበረችውን ሊሊ ቮልፖርት ገድሏል በሚልም ነበር በአውሮፓውያኑ 1952 በስቅላት የተገደለው።



ግለሰቡ የቀድሞ ባህር ሠራተኛ እንደነበር ተገልጿል። የጥፋተኝነት ውሳኔው በአውሮፓውያኑ 1988 ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የቀረበ ሲሆን በዚህም የወንጀል ጉዳይ ገምጋሚ ኮሚሽኑ ውሳኔውን ሽሮታል።

የደቡብ ዌልስ ፖሊስ ፍርዱ ጉድለት የተሞላበት መሆኑን አምኖ ይቅርታ ጠይቋል።«ይህ ፍርድ ከጊዜው ጋር የሚሄድ ነው። ዘረኝነት አድልዎ እና ጭፍን ጥላቻ የወንጀል ፍትህ ሥርዓቱን ጨምሮ በመላው ኅብረተሰቡ ተስፋፍቶ ነበር» ሲል የፖሊስ ኃላፊ ጄረሚ ቮን ተናግረዋል።

«ማህሙድ ማታን በማይሆን ክስ ምክንያት የፍትህ እጦት ሰለባ እንደነበሩ ምንም ጥርጥር የለውም፣ ፖሊስም የዚህ አንዱ አካል ነው» ብለዋል።

«ከ70 ዓመታት በፊት በግለሰቡ ላይ ለተፈጸመው በደልና አሰቃቂ ስቃይ ቤተሰቡን እና በዚህ አደጋ ለተጎዱት ሁሉ ለዓመታት ለደረሰው ግፍ ፖሊስን በመወከል ይቅርታ መጠየቁ ትክክል እና ተገቢ ነው» በማለት አስረድተዋል።

የማህሙድ ማታን ባለቤት ላውራ እና ሦስት ልጆቻቸው ዴቪድ፣ ኦማር እና ኤዲ በመባል የሚታወቀው ሜርቪን ስሙ ከግድያ ወንጀል ነፃ እንዲባል ለ46 ዓመታት የቆየ ረዥም የዘመቻ ትግል አድርገው ነበር።

ሁሉም ቤተሰቦቹ የሞቱ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ፖሊስ ይቅርታ መጠየቁን አስመልክቶ ከስድስት የልጅ ልጆች አንዷ «ቅንነት የጎደለው» ስትል ጠርታዋለች።

«በዚህ በቀጥታ የተጎዱት ሰዎች ከእኛ ጋር ባለመሆናቸው ይቅርታው በጣም ዘግይቷል። በሕይወት የሉም እና ከዚህ አመት በኋላ እናዝናለን የሚል ቃል ሰማን» ስትል ታንያ ማታን ተናግራለች።

## ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም

# በግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለማረም

የኢፌዲሪ ትምህርትና ስልጠና ባለሥልጣን ከግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ባለቤቶች እና አመራሮች ጋር በዘርፉ እየታዩ ያሉ ችግሮች እና መፍትሔዎቻቸው ላይ ያተኮረ የምክክር ውይይት ማካሄዱ ከባስልጣኑ የማህበራዊ ትስስር ገጽ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል። የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አንዱዓለም አድማሴ በምክክሩ ወቅት እንዳሉት፤ በከፍተኛ ትምህርት ጥራት ዙሪያ ከፍተኛ ችግሮች እንዲፈጠሩና ሂደቱ ወደ ኋላ እንዲጎተት ያደረጉትን ምክንያቶች በመለየትና በማጥራት ለሕብረተሰቡ፣ ለመንግሥት እና ለሚዲያ አካላት ተደራሽ በማድረግ ግልጽነት እንዲፈጠር ከማድረግ አኳያ ሰፊ ሥራ ተሰርቷል።

በዘርፉ ያሉትን ችግሮች ለህዝብ ይፋ መደረጉ መንግሥትም ልዩ ትኩረት እንዲሰጠው ማድረጉን የገለጹት ዶክተር አንዱዓለም፤ ለአብነትም በመንግሥት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ሦስት ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች እንዲሾሙ መደረጉን፣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የቦርድ ሥራ አመራር እንዲኖሩት መደረጉ፣ ተቋሙ ከኤጀንሲነት ወደ ባለሥልጣን እንዲያድግ መደረጉ እና አደረጃጀቱ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ሊያረጋግጥ በሚችል መልኩ እንዲደራጅ መደረጉ እንዲሁም የመሳሰሉት ጉዳዮች መንግሥት ለተቋሙ የሰጠውን ልዩ ትኩረት የሚያመለክቱ መሆናቸውን ያነሳሉ።

በዘርፉ ከሚታዩ ችግሮች ስፋትና ጥልቀት አንጻር መንግስት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራቱን የሚቀጥል ይሆናል። ችግሩን ከምንጩ ለይቶ ማድረቅ የማይቻል በመሆኑ የመንግስት ድጋፍ ፣ቁጥጥር እና ክትትል እንደሚቀጥልም ተገልጿል።

ዋና ዳይሬክተሩ በዘርፉ የሚታዩ የመመሪያ ጥሰቶችን ሲገልጹም ፤ባልተፈቀደ ካምፓስ እና ቦታ ማስተማር፣ ሲኦሲ ሌላ ጊዜ ታሟላላችሁ በሚል መስፈርት ያላሟሉ ተመዝጋቢዎችን መቀበል፣ የእውቅና ፈቃድ ባገኙበት ህንጻ አለመገኘት እና እውቅና ፈቃድ ለማግኘት ብቻ ህንጻ የሚከራዩና ኪራዩ በሂደት ለሌላ ህገወጥ ተግባር ውስጥ የሚገቡ እና በመሳሰሉት የመመሪያ ጥሰቶች ወደ ሦስት መቶ 73 ካምፓሶች ላይ የእርምት እርምጃ ተወስዷል።በተጨማሪም ለሕብረተሰቡ በሚዲያ ተቋማት ይፋ መደረጉ እና ይህን ያህል ቁጥር የመመሪያ ጥሰቱ በሀገር ላይ እያደረሰ ያለው ጉዳት አስደንጋጭ ደረጃ ደርሷል።


ዶክተር አንዱዓለም አድማሴ

በመሆኑም ችግሩን ባለበት ለማስቆም የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በማኅበራቸው እንዲደራጁ፣ ሲደራጁ ተደማጭነታቸው እንደሚጨምር እና ህገ ወጥነቱንም ማስቆም እንደሚቻል ዶክተር አንዱዓለም ምክርና ማሳሰቢያም ሰጥተዋል። አክለውም፤ በቀጣይ ህገ ወጥ ሥራ የሠሩ ተቋማት ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ በወንጀልና በፍትሐብሄር ይጠየቁ የሚለው ሐሳብ ሆኗል። ‹‹እኛ በዚህ መልኩ ተጠያቂ ባለማድረጋችን ጥያቄው ወደኛ እየመጣ ነው።›› ሲሉ ያመላክታሉ።

በባለስልጣኑ የኢንስፔክሽንና የትምህርት ማስረጃ ማረጋገጥና ቁጥጥር ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ቸሩጌታ ገነነ በበኩላቸው ፤ ተቋሙ ስለተቋቋመበት ዓላማ፣ ተቋሙ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ስለተሠሩ ሥራዎች ውጤቶች፣ ስላጋጠሙ ተግዳሮቶች እና በቀጣይ ሊሠሩ የታቀዱ ሥራዎችን በተመለከተ ሰፊ ማብራሪያና ገለጻ አድርገዋል።

በምክክሩ ላይ ከተነሱት ሃሳቦች መካል የባለስልጣኑ ተደራሽነትና ጥራትን ያማከለ አሰራር መዘርጋት ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራበት የሚገባ መሆኑም ተነስቷል። በባለሥልጣኑ የእውቅናና ስታንዳርዳይዜሽን ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ዱንኳና ኑጉሳ በበኩላቸው፤ ተቋሙ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱን እና አሁን ያለበት አቋም ላይ መድረሱን ይገልጻሉ።

የኢትዮጵያ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማኅበር ፕሬዚዳንት ዶክተር ሞላ ጺጋዬ፤ ከግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማኅበራቸው በምንም መልኩ ከህገ ወጥ ተቋማት ጎን እንደማይቆም፣ባለሥልጣኑ በህገ ወጥ ተቋማት እርምጃ የመውሰድ ተግባር ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ ፣ ተቋማት የሚፈጽሙትን የህግ ጥሰት አምነው ባለማስተካከላቸው ባለሥልጣኑ ሰርቶም እንዳልተሠራ እየተገለጸ በመሆኑ እኛ የግል ተቋማት በፍጥነት ከዚህ ልንታረም ይገባል ሲሉ አሳስበዋል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
ዘመን
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት:- www.press.et
ፌስቡክ:- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# የዋልያዎቹ የቻን ተሳትፎ ለሦስተኛ ጊዜ ተሳክቷል

**ቦጋለ አበበ**

ኢትዮጵያ ከ31 አመታት በኋላ እኤአ 2013 ላይ በደቡብ አፍሪካ አዘጋጅነት በተካሄደው የአፍሪካ ዋንጫ መሳተፏን ተከትሎ በእግር ኳሱ ከፍተኛ መነቃቃት ነበር። የዚያ ትውልድ ታሪካዊ ተጫዋቾችና የዋልያዎቹ አሰልጣኝ የነበሩት ሰውነት ቢሻው ከአፍሪካ ዋንጫው ማግስት በተመሳሳይ ደቡብ አፍሪካ ላይ በተካሄደው የቻን ዋንጫ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ተሳተፉ። ለዚህ ተሳትፎም የመጨረሻውን የማጣሪያ ጨዋታ ከሩዋንዳ ጋር ከሜዳቸው ውጪ ተፋልመው ማለፋቸው አይዘነጋም። በተለይም በዚያ የመጨረሻ የማጣሪያ ፍልሚያ የዋልያዎቹ ቋሚ ግብ ጠባቂ የነበረው ጀማል ጣሰው ጨዋታው በመለያ ምት እንደሚጠናቀቅ ከአሰልጣኙ ጋር ቀደም ብለው በመግባባት የመለያ ምት የማዳን የተሻለ ብቃት ያለው ግብ ጠባቂ ሲሳይ ባንጫ ተቀይሮ እንዲገባ አደረጉ። ሲሳይም አላሳፈራቸውም። ተቀይሮ ገብቶ ሁለት የመለያ ምቶችን በማዳን ዋልያዎቹን ለመጀመሪያ ጊዜ ለቻን ዋንጫ አበቃቸው።

ከዘጠኝ አመታት በኋላ ዋልያዎቹ በአሰልጣኝ ውበቱ አባተ እየተመሩ በቀጣይ አመት በአልጄሪያ አዘጋጅነት በሚካሄደው የቻን ዋንጫ ለሦስተኛ ጊዜ ለመሳተፍ ባለፈው ቅዳሜ ከሩዋንዳ አቻቸው ጋር የመጨረሻውን የዘጠና ደቂቃ ፍልሚያ ከሜዳቸው ውጪ አደረጉ።



ዋልያዎቹ ሩዋንዳን በሜዳዋ በመርታት ለሦስተኛ ጊዜ በቻን በመሳተፋቸው ደጋፊውን አስደስቷል፣

ዋልያዎቹ ለመጀመሪያ ጊዜ መሳተፍቸውን ያረጋገጡት በተመሳሳይ ሩዋንዳን በሜዳዋ ገጥመው ሲሳይ ባንጫ ባዳናቸው ሁለት የመለያ ምቶች ነበር። ዘንድሮም ዋልያዎቹ የመጀመሪያውን የማጣሪያ ጨዋታ ከሩዋንዳ ጋር አድርገው ካለ ግብ አቻ እንደመለያየታቸው ታሪክ ራሱን ይደግማል የሚል ግምት በብዙዎች ዘንድ አድሮ ነበር።

ዋልያዎቹ በቅዳሜው የሩዋንዳ ወሳኝ ፍልሚያ ወደ መለያ ምት አላመሩም እንጂ ያለፈውን ታሪክ በመድገም ወደ ቻን አምርተዋል። ከቅርብ አመታት ወዲህ በታላላቅ ጨዋታዎች ለዋልያዎቹ ወሳኝ ግቦችን በማስቆጠር ታሪክ እየሠራ ያለው የአጥቂ መስመር ተጫዋች ዳዋ ሆጤሳ ገና በጨዋታው 22ኛ ደቂቃ ላይ ያስቆጠራት ግብ ኢትዮጵያን በቀጣዩ ጥር በአልጄሪያ አስተናጋጅነት ለሚካሄደው የአፍሪካ ሀገራት ቻምፒዮንሺፕ (ቻን) ውድድር ለማሳለፍ በቂ ነበረች።

በመጨረሻው ዙር ማጣሪያ ሩዋንዳን የገጠመው ብሔራዊ ቡድናችን ከሜዳው ውጪ ባሳካው ድል በድምር ውጤት 1-0 አሸንፎ የቻን ማጣሪያ ጉዞውን ምንም ሽንፈት እና ጎል ሳያስተናግድ በድል አጠናቋል።

የፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት እና የጽሕፈት ቤት ኃላፊም በዋልያዎቹ ውጤት የተሰማቸውን ደስታ አጋርተዋል። የፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት አቶ ኢሳይያስ ጂራ «ለመላው ኢትዮጵያውያን በተገኘው ውጤት እንኳን ደስ አለን። ይህ ትውልድ ማኩራቱን ቀጥሏል። በቀጣይ በቻንም ሆነ በሌሎች ውድድሮች ከዚህ የበለጠ ውጤት በማስመዝገብ ማኩራቱን እንደሚቀጥል እምነቴ ከፍ ያለ ነው።» ብለዋል።

ዋና ፀሐፊ አቶ ባሕሩ ጥላሁን በበኩላቸው «ብሔራዊ ቡድናችን ለአልጄሪያው ውድድር በማለፍ ውጤታማ ጉዞውን አስቀጥሏል። ለመላው የቡድናችን አባላት እና ከቡድናችን ጀርባ ሁሌም ለሚገኘው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳን ደስ አለን።» የሚል መልዕክት አስተላልፈዋል።

ዋልያዎቹ ከስድስት አመት በፊትም ለሁለተኛ ጊዜ በቻን ውድድር ላይ በአሰልጣኝ ዮሐንስ ሳህሌ እየተመሩ በጋቦን በተካሄደው ዋንጫ ላይ መሳተፍ ችለዋል። በሁለቱም የተሳትፎ ታሪካቸው ግን ከምድባቸው ሳያልፉ ቀርተዋል።

## ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# ተቋማዊ የሳይበር ደህንነት ማስጠበቂያ መንገዶች

**ይበል ካሳ**

አሁን የምንገኝበት ዘመን ዓለም በከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ እንደደረሰች የሚታሰብበት፣ የሰው ልጅም እጅግ ከፍተኛ በሆነ በተራቀቀ የስልጣኔ ደረጃ ላይ ደርሷል ተብሎ የሚታመንበት ታላቅ የስልጣኔ ዘመን ነው:: ዓለማችን እዚህ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ እንድትደርስና የሰው ልጅም በእንዲህ ዓይነት የስልጣኔ ከፍታ ላይ እንዲቀመጥ ያስቻለው ደግሞ ሳይንስና ቴክኖሎጂ በከፍተኛ ደረጃ እያደገ በመምጣቱ ነው::

በዚህ ረገድ ሁሌም በማያቋርጥ የለውጥ ማዕበል ውስጥ ሆኖ በዓይነት፣ በብዛትና በጥራት በከፍተኛ ደረጃ እያደገ የመጣው ሳይንስና ቴክኖሎጂ በተለይም ከሰው ልጆች ባህሪይና ፍላጎት ጋር ተፈጥሯዊ ቁርኝት ያለው የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ የሰው ልጅ አሁን ላይ ለደረሰበት የስልጣኔ ደረጃና ዓለማችን አሁን ላይ ለምትገኝበት አዲስ ዓይነት ገጽታ የአንበሳውን ድርሻ አበርክቷል:: አሁን የምንገኝበትን አዲስ ምህዳርና የሳይበር ዘመንን የፈጠረውም ማሕበራዊ ትስስርን የማጠናከርና የእርስ በእርስ ግንኙነትን የማሳደግ ይኸው የሰው ልጆች ተፈጥሯዊ ባህሪይ ነው::

በመሆኑም አሁን በምንገኝበት የሳይበር ዘመን የሰው ልጆች ሥራቸው ብቻ ሳይሆን የሥራቸው ብሎም አጠቃላይ የሰብዓዊ ማንነታቸው መሠረት የሆነው አስተሳሰባቸውም እየተለወጠ ይገኛል:: ስለሆነም ግለሰቦች፣ ተቋማት፣ ሀገራት ብሎም ዓለም እንደ ዓለም የሰው ልጆች መኖሪያ ሆና እንድትቀጥል ዘመኑ የፈጠረውን ይህንኑ ምናባዊ ምህዳር መጠቀም ግድ የሚልበት ደረጃ ላይ እየተደረሰ ነው::

ታዲያ ይህ እንኖርበት ዘንድ ከራሳችን ለራሳችን የተሰጠን አዲሱ የዘመናችን ስልጣኔ ደግሞ እንደማንኛውም ዘመን የራሱ አወንታዊና አሉታዊ ገጽታዎች ወይንም በረከቶችና መርገምቶች አሉት:: ከበረከቶቹ ብንጀምር ቀደም ሲል በርካታ ሰዓታትን፣ ቀናትንና ወራትንና ዓመታትን ሳይቀር ይጨርሱ የነበሩ አድካሚና ውስብስብ ሥራዎችን በቀላሉና በፍጥነት ማከናወን የሚቻልበት የዕድገት ደረጃ ላይ ተደርሷል:: በአጭሩ የስልጣኔዎችና ሁሉ መነሻ ምክንያት የሆነውን የሰው ልጆችን ሕይወት የተሻለ የማድረግ ዓላማ አሳክቷል፤ ከምንጊዜውም በላይ የሰው ልጆችን ሕይወት አቅልሏል::

ከመርገምቶቹ መካከል ዋነኛው ደግሞ በአወንታዊ ጎኑ ሕይወትን እንዳቀለለን ሁሉ መጥፊያ መንገዳችንንም እንደዚሁ ቀላል እንዲሆን ማድረጉ ነው:: ይሁን እንጂ በዘመናችን ውስጥ አለመኖር አንችልም:: ምርጫችን የሚሆነው አሉታዊውን ጎን በጥበብ የምናልፍበትን መንገድ መዘየድና በአወንታዊ ገጽታው ውስጥ እንደተመኘነው በምቾትና በደስታ የምንኖርበትን ሁኔታ መፍጠር ነው:: ይህን የምናደርግበት ጥበብም የሳይበር ደህንነት ይባላል:: ዛሬ ተራውን የሰጠነው ለተቋማዊ የሳይበር ደህንነት ነው::

ባለንበት የሳይበር ዘመን የሳይበር ጥቃት ከሚፈጸምባቸው ምክንያቶች መካከል ገንዘብ ለማግኘት፣ የራስን ፖለቲካዊ ግብ ለማሳካት፣ ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ለማድረስ፣ ሀገራዊ ቀውስ ለመፍጠር፣ ጠላቴ የሚሉትን አካል ለመበቀል፣ ጥቂቶቹ ደግሞ ዕውቅናና ዝና ማግኘት ነው:: ተቋማት ደግሞ በእነዚህ በሁሉም ምክንያቶች ተጠቂ ሊሆኑ የሚችሉ በመሆናቸው ዋነኞቹ የሳይበር ጥቃት ኢላማዎች መሆናቸው ይታወቃል:: ስለሆነም ከፍተኛ ጥንቃቄና የሳይበር ደህንነት ሥርዓት በመዘርጋትና በመተግበር ራሳቸውን ከጥቃት መከላከልና መጠበቅ ይገባቸዋል::

ከዚህ አኳያ የመጀመሪያው ነገር እንደ ሀገር የሳይበር ደህንነት ፖሊሲ ማዘጋጀት ሲሆን ኢትዮጵያም ለሳይበር ጥቃት ፈጣን ምላሽ መስጠት የሚያስችልና ዘመኑን የሚመጥን የተሻሻለ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲ ባለፈው ዓመት ማዘጋጀቷ ይታወቃል:: በፖሊሲው ውስጥም ተቋማት ተቋማዊ የአሠራር ሥርዓቶችን በመዘርጋት በራሳቸው መንገድ የሳይበር ጥቃትን እንዲከላከሉ የሚያስችል አሠራር መካተቱን ይታወሳል:: ተቋማት ይህንን ሊተገብሩ ይገባል:: ለዚህ ደግሞ ትልቁና ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ብቁ ተቋማዊ አደረጃጀትና ቁርጠኝነት የተሞላበት አመራር ነው::

> **የሳይበር ደህንነት ፖሊሲ ማዘጋጀት ሲሆን ኢትዮጵያም ለሳይበር ጥቃት ፈጣን ምላሽ መስጠት የሚያስችልና ዘመኑን የሚመጥን የተሻሻለ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲ ባለፈው ዓመት ማዘጋጀቷ ይታወቃል፡፡ በፖሊሲው ውስጥም ተቋማት ተቋማዊ የአሠራር ሥርዓቶችን በመዘርጋት በራሳቸው መንገድ የሳይበር ጥቃትን እንዲከላከሉ የሚያስችል አሠራር መካተቱ ይታወሳል**

በመሆኑም ተቋማት ራሳቸውን ከሳይበር ጥቃት ለመከላከል ከምንም በላይ ቁርጠኝነት ሊኖራቸው ይገባል:: ለዚህም አስፈላጊውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ማሟላትና በቂ በጀት መመደብ ይኖርባቸዋል::

የራሳቸውን የሳይበር ደህንነት አመራርና አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት ይጠበቅባቸዋል:: ይህም ማለት ተቋማት እንደየባህሪያቸውና መጠናቸው የሳይበር ደህንነት የሥራ ክፍሎች፣ በቂ የሰለጠነ ባለሙያና አመራር ሊኖራቸው ይገባል:: ከዚህ በተጨማሪም ተቋማዊ የሳይበር ደህንነት ማስጠበቅያ ፖሊሲ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ሥርዓት ሊዘረጉ ይገባል:: ከዚህ በተጨማሪም ተቋማት የሳይበር ደህንነት ማስጠበቂያ ቴክኖሎጂዎችን መታጠቅ እና መጠቀም ይጠበቅባቸዋል:: ለዚህም ተቋሙን ከሳይበር ጥቃት ለመከላከል የተዘጋጁ የሳይበር ደህንነት ማስጠበቂያ ቴክኖሎጂዎችን መታጠቅ፣ የሳይበር ደህንነት ማስጠበቅያ ቴክኖሎጂዎችን ከመታጠቅ አልፎ መጠቀምና በየጊዜው ማዘመንም ይኖርባቸዋል::

ተቋማት ብሔራዊ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂን በመከተልና የራሳቸውን የሳይበር ደህንነት ማስጠበቂያ የአሠራር ማዕቀፍና ስትራቴጂ መዘርጋትና ለአተገባበሩም ቁርጠኛ መሆን ከቻሉ ከ80 እስከ 90 በመቶ የሚሆኑ ሊደርስባቸው የሚችሉ የሳይበር ጥቃቶችን ቀድመው መከላከል ይችላሉ::

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ